# ታላቁ አሳዛኝ ክስተት እና የእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ

# “በመጨረሻው ዘመን መልእክት” ብርሃን ውስጥ

# ታላቁ አሳዛኝ ክስተት እና የእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ “በመጨረሻው ዘመን መልእክት” ብርሃን ውስጥ

በዚህ ማብራሪያ ውስጥ ስለ ሰማይና ምድር ያሉ አስፈላጊ መረጃዎችን እንመለከታለን። ከመጀመሪያው ጀምሮ የሰው ልጆች ስለ ዕጣ ፈንታቸው አስበዋል። ይህ መጽሐፍ ገና ያልተወገደዉን የታላቁን አሳዛኝ ክስተት ምክኒያት ብቻ ሳይሆን ፣ የዚህን ጥንታዊ ችግር መፍትሔ በተሳካ ሁኔታ እንደሚያሳይና እንደ መመሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል እናምናለን።

የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጆች የዚህን ዓለም ብርሃን ያዩት ከስድስት ሺህ ዓመታት በፊት ነው። እ.ኤ.አ በጥቅምት 12 ቀን 1999 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃ መሠረት የዓለም ሕዝብ ቁጥር ስድስት ቢሊዮን ደርሷል። እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም. በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገሩ ታላላቅ ክስተቶች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይፈጸሙ እንደሆነ መጠየቅ ተገቢ ነው። የሚጠበቁ ነገሮች በሁሉም ረገድ በጣም ከፍተኛ ናቸው። በምድር ላይ ሁለት ከተሞች ትኩረት ውስጥ ናቸው፣ እነርሱም እየሩሳሌም እና ሮም ናቸው። እየሩሳሌም የሦስቱ የዓለም ሃይማኖቶች፣ ይሁዲነት፣ ክርስትና እና እስልምና የትውልድ ቦታ ተደርጋ ትታያለች፣ ምንም እንኳን ሙሐመድ ሃይማኖቱን በ632 ዓ.ም. በአረቢያ በመካና መዲና እንጂ በእየሩሳሌም ባይመሰርትም። ሮም ለ“ቅዱስ ዓመት 2000” ተዘጋጅታለች። “ቅዱስ ዓመቱን” ምክንያት በማድረግ የቫቲካን ወርቃማ በር በጳጳስ ጆን ፖል II ተከፈተ፣ የእየሩሳሌም ከተማ ግድግዳ ላይ ያለው ወርቃማ በር ግን ለአሁኑ ዝግ ነው። ሆኖም፣ የእኛ አሳሳቢ ጉዳይ በሰዎች የሚከናወኑ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች አይደሉም፣ ብቸኛው ቅዱስ እግዚአብሔር፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ምን እያደረገ እንደሆነ ማወቅ ነው።

ባለፉት መቶ ዘመናት፣ ወንዶችና ሴቶች ለተወሰኑ ዓመታት ልዩ ክስተቶችን ተንብየዋል። “የተለየ” ከመሆኑ የተነሳ፣ የ2000 ዓ.ም. የትኩረት ማዕከል ሆኗል። ነገር ግን ልክ እንደ ማንኛውም ሌላ ዓመት ነው ፤ ስለሆነም ራሳቸውን የሾሙ ነቢያትና ነብይት የተነበዩት ነገሮች አይፈጸሙም። <u>ያልተለመደው የሚሆነው እግዚአብሔር ራሱ ሲያደርገው ብቻ ነው</u>። በእርግጥም፣ እኛ ታሪካዊ የመዞሪያ ነጥብ ላይ ነን፣ እናም ነገሮች እንደሚፈጸሙ መጠበቅ እንችላለን። አሁን እያንዳንዱ ዓመት “ታላቁ የዮቤልዩ ዓመት” ሊሆን ይችላል። በእርግጥ ማንም ቀን መወሰን አይችልም፣ ነገር ግን የጊዜ ምልክቶች እየጨመረ በሚሄድ ግልጽነት ወደ እሱ ይጠቁማሉ። ከአዳም 2000 ዓመታት ከአለፈ በኋላ እግዚአብሔር<u> በተስፋዎች(ቃል በመግባት) ላይ በመመሥረት</u> ከአብርሃም ጋር ጉልህ ቃል ኪዳን አደረገ። ሌላ 2000 ዓመታት ካለፉ በኋላ፣ እግዚአብሔር <u>ተስፋዎችን(ቃል የተገቡትን) በመፈጸም</u>፣ አዲስ ኪዳንን በማቋቋም አዲስ ጅማሬ አደረገ። በመካከልም የሕግና የነቢያት ዘመናት ነበሩ። ሕጉ ከብዙ ትእዛዞቹ ጋር የወደቁ የሰው ልጆች በደላቸውን እንዲያምኑ ተሰጥቶ ነበር። ነቢያት ደግሞ **በድነት ዕቅድ** ሂደት ውስጥ እስከ ፍጻሜው ድረስ የሚፈጸሙትን ክስተቶች የማስታወቅ ተግባር ነበራቸው።

አሁን የዚህን የ2000 ዓመት የጸጋ ዘመን መጨረሻ ላይ ደርሰናል። በእርግጥም በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የተገለጹ ታላላቅ ክስተቶች እንደሚፈጸሙ ልንተማመን እንችላለን። “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ወስኖአል፣ የሚያስጥለዉስ ማን ነዉ? እጁም ተዘርግታለች የሚመልሳታስ ማን ነዉ?” (ኢሳ. 14:27)። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሰባተኛው ሺህ ዓመት የክርስቶስ የሺህ ዓመት ግዛት ሊሆን ብቻ ሳይሆን ይሆናል እና መሆንም አለበት። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለዚህ ተስፋዎች አሉን፣ በተለይም በራእይ 20:6 ላይ እንደምናየው፦ “በመጀመሪያው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ በእነዚህ ላይ ሁለተኛው ሞት ሥልጣን የለውም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፤ ከእርሱም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።” ስለ አንድ የተወሰነ ትንቢታዊ የጊዜ ወቅት ከተነገረ፣ ጥቅሱ ይሠራል፦ “አንድ ቀን ከጌታ ዘንድ እንደ ሺህ ዓመት ነው፣ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን ነው” (2 ጴጥ. 3:8)። እግዚአብሔር በሰባተኛው ሺህ ዓመት የማዳን ሥራውን ያጠናቅቃል፣ ልክ በሰባተኛው ቀን የፍጥረት ሥራውን እንዳጠናቀቀ እና ከሥራው ሁሉ እንደ አረፈ (ዘፍ. 2:1-3)።

በዘመን መጨረሻ ላይ፣ ፍትሐዊው ፍርድ በነጩ ዙፋን ላይ ይሰጣል (ራእይ 20:11-15) እና ሁሉም ሰው ከመጨረሻ መዳረሻው ይደርሳል። ሁሉም በራሳቸው ምርጫ ቦታ ላይ ይሆናሉ። “ምርጫው ሰፋ ባለ ቁጥር፣ ችግሩም ይተልቃል” የሚለውን አባባል እናውቃለን። ዘላለማዊነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ትክክለኛውን ምርጫ የሚያደርግ ሁሉ ችግርን ያስወግዳል ማለት እንችላለን። ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ፣ ጊዜ ያበቃል እና ወደ ዘላለማዊነት ይቀላቀላል። የማይታወቀ ደስታ እና ማይቋረጥ ሰማያዊ ስምምነት ያለው አዲስ ጅምሬ ይጀምራል። “እነሆ፣ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፤ የቀድሞውም አይታሰብም፣ ወይም ወደ አእምሮ አይመጣም” (ኢሳ. 65:17)። “ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን” (2 ጴጥ. 3:13)። “አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርንም አየሁ፤ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛው ምድር አልፈዋልና…” (ራእይ 21:1)።

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑ ክርስቲያኖች የዓለም ፍጻሜን አይጠብቁም፣ ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስን የመመለስ የተስፋ ቃል ይጠብቃሉ። በ“አርማጌዶን-ገሃነም” የፍርሃት ስሜት አይፈጥሩም። ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በአዳኛቸው በኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ 14:1-3 በተሰጠዉ ተስፋ መሠረት ወደ ቤታቸው ለመወሰድ ሲጠብቁ ቆይተዋል። በእርግጥም፣ እግዚአብሔር ብቻ ቀኑንና ሰዓቱን እንደሚያውቅ ተጽፏል። ኢየሱስና ሐዋርያት የክርስቶስን መመለስ ሲያበስሩ አልተሳሳቱም። ሐዋርያው ጴጥሮስ በዘመናት መጨረሻ ላይ ዘባቾች በተለይ ይህንን ነጥብ “የመምጣቱ ተስፋ ወዴት ነው?… ሁሉ ከመጀመሪያው ጀምሮ እንደነበረው ቀጥሏል…” (2 ጴጥ. 3:4) በማለት እንደሚያፌዙ ተንብዮአል። እስከ ትክክለኛው ፍጻሜ ድረስ፣ “ጌታ ስለ ተስፋው አይዘገይም… ነገር ግን በእኛ ላይ ይታገሣል…” (2 ጴጥ. 3:9) ተብሎ እንደተጻፈው እውነት ነው። መለኮታዊው ትዕግስት በመጨረሻ ያበቃል፣ ልክ በኖኅ ዘመን እንደነበረው (ማቴ. 24:39) ፣ እና ይህ በማንኛውም ጊዜ ሊሆን ይችላል።

ከድነት ዕቅድ ጋር የተያያዙ ክስተቶች ሁልጊዜ የሚፈጸሙት እንደ እግዚአብሔር ምክርና የጊዜ ዕቅድ ጊዜው ሲፈጸም ነው ። "ሥራውን ይፈጽማልና፣ በጽድቅም ያሳጥረዋል፤ ጌታ አጭር ሥራን በምድር ላይ ይሠራልና" (ሮሜ 9:28)።

# የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ፍጥረት

እንዴት ተጀመረ?

እንዴትስ ያበቃል?

እግዚአብሔር ያደረገው እያንዳንዱ ጅምር እጅግ በጣም ጥሩ፣ ፍጹምም ነበር። ነገር ግን ተቃዋሚው ሁልጊዜ ዕቅዱን ለማበላሸት ሞክሯል። ሁሉም ነገር በሰማይ ተጀምሮ በምድር ላይ ቀጠለ። ያ **ታላቅ አሳዛኝ ክስተት** ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በሚያስደንቅ እና ፍጹም በሆነ መንገድ ፈጥሯል። ነገር ግን በሆነ ወቅት ሉሲፈር በሰማይ ላይ በእርሱ ላይ ተቃዉሞ ተነሳ። ከዚያ በኋላ፣ በገነት ውስጥ የመጀመሪያዎችን ባልና ሚስት አሳሳተ። ጠላት ምንም ነገር መጀመሪያ እንደነበረው አልተወም። ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ዋሽቷል፣ አሳስቷል እና አጥፊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ሰላም የለቀቀው ጋብቻ የለም፣ ያልተናወጠ ቤተሰብ የለም። በእርግጥም ማንንም ሰው፣ ጎሳን፣ ሕዝብን፣ አገርን ብቻውን አልተወም። ለማጥፋት ቀርጦ ነበር። የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ዕቅዶች ከእስራኤል ጋር ከዚያም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለማበላሸት ሞክሯል። ያከበረው አንድም መነቃቃት(ሪቫይቫል) አልነበረም። የእግዚአብሔር መንፈስ በሚሠራበት ቦታ እንኳን፣ አለመግባባትን ለመዝራት፣ ግራ መጋባትንና መለያየትን ለማምጣት መጥቷል። በእርሱ ተጽዕኖ ሥር፣ በሃይማኖታዊዉ መስክም ነገሮች ተሳስተዋል እና አሁን የማታለል እውነተኛው ቁንጮ ግልጽ ነው።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ስለ ሁሉም ነገር፣ በሰማይና በምድር ጭምር ምን ስህተት እንደተሰራ ተነግሮናል። ስላለፈው ነገር ማስተዋልን፣ በአሁኑ ጊዜ ስለሚከናወነው ነገር መረዳትን እና ስለወደፊቱ ጊዜ ግንዛቤን እናገኛለን። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ፍጹም በሆነ መንገድ እንደፈጠረ እና ከሰው ልጅ ጋር የፍቅርና የሰላም ዓላማ ብቻ እንዳለዉ እርግጠኛ እንደሆነዉ ፣ ጠላትም ጉዳትን ለማድረስ እንደሚሰራ እርግጥ ነዉ። እግዚአብሔር በቃሉ በእርግጠኝነት እንደተናገረ ሁሉ፣ ጠላትም የተነገረውን እንደሚያጣምም እርግጥ ነው። ሰይጣን አምላክ የለም የሚል አይደለም፣ በእግዚአብሔር ያምናል ይንቀጠቀጣልም (ያዕቆብ 2:19)። በዚህ ዉስጥ ማታለለ አለበት። እርሱ በእግዚአብሔር ስም ቃልን ተጠቅሞ ያሳስታል ያታልላል፣ እርሱም እርሱንና ቃሉን ጠንቅቆ ያውቃልና! ያለምንም ማመንታት "የሁሉም ሃይማኖቶች ዋና የነገረ መለኮት ምሁር" የሚል ማዕረግ ሊሰጠው ይችላል። ተቃዋሚ ሆኖ፣ እውነት በሆነው ነገር ሁሉ ላይ የጥያቄ ምልክት ያደርጋል እና በምቀኝነትና በውሸት ይተካዋል። በዚህም ሃይማኖታዊ ቃላትን በመጠቀም ጥርጣሬን በመዝራት እና የሰውን ልጅ ወደ አለማመን በመሳብ ሁልጊዜ ተሳክቶለታል።

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ተፈጥሯዊው እና ስለ መንፈሳዊው ፍጥረት፣ ስለ መጀመሪያውና ስለ ሁለተኛው አዳም ይናገራሉ (1 ቆሮ. 15:45-49)። የፍጥረት ሥራ ሲጠናቀቅ እንዲህ ተነግሮናል ፡- “እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ።” በተመሳሳይ መንገድ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የድነት ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ በግርማዉ ቀኝ ተቀመጠ (ኤፌ. 1:20 እና ሌሎች) እና በብዓለ ኃምሳ ቀን ቤተ ክርስቲያኑን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሞላት (ሐዋ. 2)። ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ የመንፈስ ቅዱስ ንጹህ ውጤት ነበረች። እርስዋም የራሱ የእውነት ምሰሶና መሠረት ነበረች (1 ጢሞ. 3:15)። ከዚያ ክብር የተሞላበት ጅምር በኋላ፣ ሰይጣን አጥፊ ሥራውን ጀመረ፣ ልክ ከዚህ ቀደም በተፈጥሯዊ ፍጥረት እንዳደረገው።

በመጀመሪያ፣ ወደ ሰማይ መመልከት እንፈልጋለን፣ ምክንያቱም ታላቁ አሳዛኝ ክስተት በዚያ በሉሲፈር፣ ከከፍተኛ መላእክት ዉስጥ አንዱ በሆነው፣ ብርሃን የተሸከሚ የተቀባ በነበረዉ፣ “የማለዳ ኮከብ” ተብሎ በሚጠራው ተጀመረ። እሱ ከፍተኛ ተጽዕኖ ባለው የመሪነት ቦታ ላይ ነበር። ነገር ግን በድንገት ልንረዳው የማንችለው ነገር ተፈጸመ፣ እና በምድር ላይ በገነት ዉስጥ ቀጠለ። በራሱ መንገድ፣ ምናልባት መልካም አስቦ ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ስለተፈጠረ፣ በእርሱ ውስጥ ምንም ክፋት ሊኖር አይችልም። ክፉው የመጣው ራሱን ከጥሩው ካስወጣበት ቅጽበት ጀምሮ ነው። በውስጡ የነበረው ጨለማ የመጣው ከብርሃን በመውጣቱ ነው። የራሱ ፍላጎት ከእግዚአብሔር ፈቃድ አወጣው። ሁሉም ነገር በመለኮታዊ ስምምነት ሊኖር የሚችለው በቅደም ተከተል በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እስከቀጠለ ድረስ ብቻ ነው ። በከፊል በተመዘገበው ዘገባ ውስጥ ምን እንደተፈጠረ አሁንም ማየት እንችላለን። በድንገት ሉሲፈር ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን አቆመ፣ ይልቁንም ከራሱ ጋር ይነጋገር ጀመር፣ ይህም እንደሚከተለው ተመዝግቧል፡-

> “ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፣
>
> ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፤
>
> በመሰብሰቢያው ተራራም ላይ እቀመጣለሁ… ከደመና ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፣
>
> **በልዑልም እመስላለሁ አልህ**…” (ኢሳ. 14:12-27)።

እነዚህ ሁሉ ሆን ተብለዉ የተነገሩ መግለጫዎች ናቸው፣ ከእግዚአብሔር ያልመጡ በመሆናቸው ከእርሱ መለያየትን፣ እንዲሁም የሉሲፈርን በራስ መደገፍን አስከትለዋል። በዚህም የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ሆነ። ራሱ የተናገረው “እኔ እሆናለሁ…” የሚለው የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረም፣ ስለሆነም በራሱ እግዚአብሔርን ወደ መቃወም ተመርቷል። ከዚያ በፊት፣ ክፉ ወይም ክፉው አልነበሩም።

ወደ እግዚአብሔር እጅግ የቀረበው እርሱ በእርሱ ላይ ተቃዉሞ ቆመ እና ወደቀ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ “ትዕቢት ከውድቀት ይቀድማል” ማለት እንችላለን። የእግዚአብሔር ጠላት አንዳንድ

የመላእክት ፍጡራንን ወደዚህ አስከፊ ውድቀት ነተተ፡፡ በሰማይ ካለው አመፅ ጀምሮ፣ ደጋግሞ መልካም የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን፣ ክፉውም (መልካም የነበረው ሁሉ የጠፋበት) እና ሠራዊቱ አሉ፡፡ የዚህ ዓለም የጨለማ ገዥ ሆኖ፣ በሰው ልጅ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል እና ከእግዚአብሔር ከሆነው ነገር ሁሉ ጋር ይዋጋል (ኤፌ. 6:11-13)፡፡ ይህ በብርሃንና በጨለማ፣ በመልካም እና በክፉ፣ በሕይወትና በሞት መካከል የሚደረግ ትግል ነው፡፡ ሁላችንም በዚህ መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ በመጠኑም ቢሆን እየተፈተንን ነው፡፡ ቀጣዩ ታላቁ ሁለንተናዊ ፍጥጫ የሚሆነው መልአኩ ሚካኤል ከሰይጣንና ከሠራዊቱ ጋር በተቤዠኞች መውጣት ወቅት ሲዋጋ ነው፡፡ “በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ከዘንዶው ጋር ተዋጉ፤ ዘንዶውና መላእክቱም ተዋጉ፣ አልቻሉአቸውም፤ ከእንግዲህም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም፡፡” (ራእይ 12:7-8)፡፡

## ውድቀት እና ወደ ነበረበት መመለስ

በፊታችን የእግዚአብሔር ምስጢራዊ የድነት ዕቅድ ይገለጣል፡፡ በዘፍጥረት 1:27 ላይ እግዚአብሔር ሰውን በመንፈሳዊ አካል በመልኩ ፈጠረው፡፡ በምዕራፍ 2:7 ላይ ደግሞ ጌታ እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር ከሥጋ አካል ፈጠረው፡፡ በቁጥር 18 ላይ እግዚአብሔር፦ “ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እፈጥርለታለሁ” አለ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር አምላክ ሁሉንም ሕያዋን ፍጥረታት፣ ሁሉንም ጥንድ ጥንድ አድርጎ ከምድር ፈጠረ እና አዳምም ለሁሉም ስማቸዉን ሰጣቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ጌታ ከአዳም ጋር የሚስማማውን ረዳት ሊያገኝ ይችል እንደሆነ ለማየት ዙሪያውን ተመለከተ፣ ነገር ግን አላገኘም (ቁ. 20)፡፡ በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር አምላክ ሔዋንን ከአዳም ወሰደና ለእርሱ አቀረባት፡፡ እርሷም ከሥጋው ሥጋ፣ ከአጥንቱም አጥንት ነበረች (ቁ. 21-24)፡፡ እዚህ ላይ ከክርስቶስና ከቤተ ክርስቲያን ጋር በተያያዘ ታላቅ ምሥጢር አለ (ኤፌ. 5:30-32)፡፡ ሔዋን ከአዳም ተወስዳ ለእርሱ እንደቀረበች ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም በክርስቶስ ነበረች እና ንጽሕት ድንግል ሆና እርሱን ለመገናኘት ከእርሱ ወጣች (2 ቆሮ. 11:2፤ ኤፌ. 5:27)፡፡ እርሱ የቃል-ሙሽራው ነው እርሷ ደግሞ የቃል-ሙሽራይቱ ናት፣ እርሱ ራስ ነው እርሷም አካሉ ናት (ቆላ. 1:18 እና ሌሎች)፡፡

በመጀመሪያው፣ ሰማይና ምድር በስምምነት፣ መጠኑን ልንገምተው በማንችለው ደስታና ደስታ ዉስጥ ነበሩ ፡፡ የሰማይ ሠራዊት በዙፋኑ ላይ እግዚአብሔርን አመለኩ፡፡ እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ባልና ሚስት በምሽት ጊዜ በገነት ጎበኘ ከእነርሱም ጋር ህብረት አደረገ፡፡ የሐዘን፣ የሕመም ወይም የሞት ምልክት አልነበረም፡፡ ሉሲፈርም እነርሱን ማግኛ መንገድ ነበረው፣ በሕዝቅኤል 28 ላይ በሚስጥራዊ ሁኔታ እንደተነገረን፦ “…ጥበብን የተሞላህ ዉበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ፡፡ <u>በዔድን፣ በእግዚአብሔር ገነት</u> ነበርክ… የምትሸፍን የተቀባህ ኪሩብ ነህ…” (ቁ. 12-15)፡፡ እርሱ <u>የመጀመሪያዉ የተቀባ ነበር</u> እናም የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ሆነ፡፡ ይህ <u>በመጨረሻው ዘመን ስለተቀቡት</u> ርዕሰ ጉዳይ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡

ከፍተኛ ማዕረግ ያለው መልአክ ተቃዋሚ በመሆን እና በሰማይ ያንን አስከፊ አደጋ በማምጣቱ አልረካም ነበር። እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ እንዲገዛ ባደረገው በልጁ በአዳም ላይ ትኩረት እንደሰጠ አይቶ አልተደሰተም። አዳምና ሔዋን በምድር ላይ እንደ ሉዓላዊ ገዥዎች ይኖሩ ነበር። ከሰማያዊው ሥርዓት የወደቀው ተቃዋሚ በምድር ላይ የነበሩትን የመጀመሪያዎቹን ባልና ሚስት ከመለኮታዊ ሥርዓታቸው አውጥቶ በራሱ ውድቀት ውስጥ ከተታቸው። መንፈሳዊ ፍጡር እንደመሆኑ መጠን ከሰው ጋር እጅግ ቅርብ መመሳሰል የነበረውን እጅግ የላቀና ተንኮለኛ የእንስሳት ዝርያን (ዘፍ. 3:1) ተቆጣጠረ፣ እርሱም ቀጥብሎ የሚሄድና መናገር የሚችል እባብ ነበር።

እባቡ ከሔዋን ጋር ያደረገው ውይይት በደንብ ተመዝግቧል። እርሱ ከተረገመ በኋላ ብቻ (ቁ. 14) ቅርጹን አጥቶ የሚሳብ እንስሳ ሆነ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ እስከ ራእይ መጽሐፍ ድረስ፣ የእግዚአብሔር ጠላት እንደ "ዲያብሎስ፣ ሰይጣን፣ ዘንዶ እና የድሮው እባብ" በሚሉ መጠሪያዎች ይጠራል።

በምድር ላይ የሆነው ነገር በሰማይ ከሆነው የበለጠ አስከፊ ነበር። ሆኖም፣ ኪሩቤልና ሱራፌል፣ በሉሲፈር ያልተነኩ የሰማይ ፍጡራን ሁሉ፣ በመለኮታዊ ሥርዓታቸው፣ በተሰጣቸው የኃላፊነት ቦታ ቀሩ። በምድር ላይ የሰው ልጅ ዘር በሙሉ በሰይጣን አገዛዝ ሥር ሙሉ በሙሉ ተገዝቷል። የመጀመሪያዎቹን ባልና ሚስት እግዚአብሔር የተናገረውን እንዲጠራጠሩ በማድረግ ተሳካለት፡ መልካም እና ክፉን ከሚያሳዉቅ ዛፍ እንዳይበሉ እና የመለኮታዊውን ቅዱስ ትእዛዝ እንዳይተላለፉ፣ ይህም የሞት ቅጣት ያስከትላል። ዓይናቸው እንደሚከፈትና እንደ እግዚአብሔር እንደሚሆኑ ቃል ገባላቸው። ጠላት፡- "በእርግጥ አትሞቱም..." አለ። ይህ እግዚአብሔር ከተናገረው ተቃራኒ ነበር። መጀመሪያ ላይ ሰይጣን መላውን የእንስሳት ዓለም በሥልጣኑ ሥር አደረገ፣ በእባቡ ውስጥ በመግባት። ከዚያ በኋላ ሔዋን ለእርሱ ተጽዕኖ እንድትገዛ አደረገ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ የጥያቄ ምልክት አደረገ እና "ከገነት ዛፍ ሁሉ በነፃ መብላት ትችላላችሁ..." የሚለውን ትእዛዝ ወደ ተቃራኒው ቀየረው፡- "ከገነት ዛፍ ሁሉ አትበሉም" (ምዕራፍ 2:16ን ከምዕራፍ 3:1 ጋር ማወዳደር ያስፈልጋል)። የአንድ ቃል ለውጥ ሞትን ለማምጣት በቂ ነበር። ጠላት ሁልጊዜ ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጉዳዮች ይናገራል፣ ነገር ግን በመጀመሪያው እውነት ውስጥ አይቆይም። ቃሉን አይክድም፣ ያጣምመዋል እንጂ፣ በዚህም ለተነገረው የተለየ ትርጉም ይሰጣል። አማኞችን እንኳን ማለቂያ በሌላቸው ክርክሮች ውስጥ ያሳትፋል እና የእግዚአብሔርን ቃል እምነት ይንዳል።

ፍሬ መብላት ብቻ አልነበረም፤ ያ የተጀመረበት መንገድ ብቻ ነበር። አሁንም ሥጋዊ ምኞትን የሚያመጣ የዓይን ምኞት ነበር። ሔዋንን በክርክር ውስጥ ብቻ አላሳተፈም፣ በእርግጥም አሳታት፣ እናም ይህ ተፈጥሮአዊ መባዛት ከመፈጸሙ በፊት ነበር፣ ጌታ "ብዙ፣ ተባዙ..." ሲል እንዳሰበው። ሴት ከተታለለች ምን ማለት እንደሆነ በተለምዶ ይታወቃል። "በኃጢአት ወደቀ" የሚለው ሐረግ ምን ማለት እንደሆነም ሁሉም ያውቃል። መጽሐፍ ቅዱስ፡- "አንድ ሰው ያልታጨቸዉን ድንግል ቢያስታት፤ ከእርስዋም ጋር ቢተኛ..." (ዘፀ. 22:16) ይላል። እባቡ ሔዋንን ካሳታት በኋላ፣ ከዚህ

ቀደም ከእርሷ ጋር ግንኙነት ላልነበረው አዳም ራሷን ሰጠችው፡፡ እባቡ ዘሩን ትቷል–ማለትም ትዉልዱን፡፡ ቃየን የእርሱ የተፈጥሮ ውጤት ነበር፣ አቤል የአዳም የተፈጥሮ ውጤት እንደነበረው፡፡ በምዕራፍ 3 ላይ በእርግጥ ከተፈጸመ በኋላ፣ በምዕራፍ 4:1-2 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቀ፤ እርስዋም ፀነሰች፣ ቃየንንም ወለደች... ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች።" ሁለት ፍጹም ከተለያዩ ወንዶች ልጆች ተወለዱ፡፡ የምዕራፍ 3 የመጨረሻ ክፍል እና የምዕራፍ 4 የመጀመሪያ ክፍል አንድ ላይ እንደተያያዙ መነበብ አለባቸው፡፡ የመጀመሪያዎች ጥቅሎች በቁጥሮችና በምዕራፎች የተከፋፈሉ አልነበሩም፡፡

በተመሳሳይ ቀን እንደተከሰተ፣ ጌታ በመሸ ጊዜ ሊጠይቃቸው ከመምጣቱ በፊት፣ ለመረዳት ይከብደናል፡፡ ከዚያም ራሳቸውን ደበቁ እና እግዚአብሔር፦ "አዳም፣ ወዴት ነህ?" ብሎ እየተጣራ ነበር፡፡ ወዲያውኑም ኀፍረታቸውን ለመሸፈን የበለስ ቅጠል ልብስ ለብሰዋል፡፡ እግዚአብሔር የተፈጸመውን ነገር በቀጥታ ጠቅሶ ቅጣቱን ወደ ትክክለኛው ቦታ አስቀመጠ፡፡ ዛሬም እዚያው አለ፡፡ ለሔዋን፦ "...በሐዘን ልጆችን ትወልጃለሽ..." አላት፡፡ ማንኛዋም ሴት ፍሬ በመብላቷ ምክንያት ልጅ ወልዳ አታውቅም፣ የመጀመሪያዋም ቢሆን፡፡እግዚአብሔር ይህንን ጥብቅ ትእዛዝ በሕጉ የሰጠበት ካለምክንያት አልነበረም፦ "እንዳትረክስባትም ከእንስሳ ጋር አትተኛ፤ሴት ከእርሱ ጋር ትተኛ ዘንድ ከእንስሳ ፊት አትቁም ፤ ይህ የተጠላ ነውና፡፡" (ዘሌ. 18:23)፡፡ እርሱም፦ "ከማናቸይቱም እንስሳ ጋር የሚተኛ ሁሉ **የተረገመ** ይሁን። ሕዝቡም ሁሉ፦ አሜን ይላሉ" (ዘዳ. 27:21)፡፡

አዳም ለሔዋን ተጽዕኖ ስለተገዛ፣ መተላለፍ እና ውድቀት ተከሰተ፡፡ እግዚአብሔር አዳምን ሲከሰዉ እንዲህ አለዉ ፦ "የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና ..." (ዘፍ. 3:17) ፡፡ ዋናው ጥፋት በአዳም ላይ ነበር፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ ስለ ተላለፈ፣ ስለዚህም፦ "...በአዳም ሁሉም እንደሚሞቱ ሁሉ..." (1 ቆሮ. 15:22) ተብሎ ተጽፏል፡፡ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ጠፋ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ባልና ሚስት ገነትን መልቀቅ ነበረባቸው፡፡ በዚያን ጊዜም እግዚአብሔር በሴቲቱ ዘር ድነትን ተነበየ (ዘፍ. 3:15)፡፡

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን ሲያደርግ፣ "የቃል-ትእዛዝ" በውድቀቱ እንዴት እንደተጣሰ ማስታወሻ እንዲሆንላቸው፣ የእያንዳንዱ ወንድ ሁሉ ሸለፈት እንዲገረዝ ጠየቀ፡፡ "ይህም በእኔና በአንተ መካከል፤ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው፤ ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፡፡" (ዘፍ. 17:10)፡፡ እግዚአብሔር የሥጋን መገረዝ የቃል ኪዳኑ ምልክት አድርጎ አወጀ፦ "በቤትህ የተወለደ፣ በገንዘብህም የተገዛ ሁሉ ፈጽሞ ይገረዝ፤ ቃል ኪዳኔም በሥጋችሁ የዘላለም ቃል ኪዳን ይሆናል። የቁልፈቱን ሥጋ ያልተገረዘም ቆላፍ ሰዉ ሁሉ፣ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ፤ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና፡፡" (ዘፍ. 17:13-14)፡፡ መገረዝ ለእግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊ ስለነበር ሙሴ ልጁን ስላልገረዘ ሊገድለው ፈልጎ ነበር (ዘፀ. 4:24-26)፡፡ በኢያሱ ዘመን እግዚአብሔር ከግብፅ ከወጡ በኋላ ለተወለዱት ወንዶች ልጆች ሁሉ መገረዝን አዘዘ (ምዕራፍ 5)፡፡

አዳኙም በስምንተኛው ቀን ተገረዘ በዚህም መለኮታዊውን መስፈርት ተቀበለ (ሉቃስ 2:21-24)። በቅዱሳት መጻሕፍት እያንዳንዱ ትእዛዝና ስርአት የራሱ ትርጉምና ቦታ አለው።

ጳውሎስ፣ በእግዚአብሔር ሐዋርያና አስተማሪ ሆኖ የተማረው፣ አብርሃምንና መገረዝን አስመልክቶ እንዲህ ሲል ጻፈ፦ "ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘዉ የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዘን ምልክት ተቀበለ፤ ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነዉ ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነወ፤ ..." (ሮሜ 4:11)።

በአዲስ ኪዳን፣ ለውድቀት ማስተሰረያ ከተደረገ በኋላ፣ ለሥጋዊ መገረዝ ምንም ትእዛዝ የለም። አሁን መገረዝ የአለበት ልባችን ነዉ። ክርስቶስ ለተገረዙትም እንዲሁም ላልተገረዙት ሞቷል። እና አሁን ጳውሎስ የጻፈው ይሠራል፦ "በኢየሱስ ክርስቶስ መገረዝ ወይም አለመገረዝ ምንም አይጠቅምም፣ ነገር ግን በፍቅር የሚሠራ እምነት ነው።" (ገላ. 5:6)። "...የሥጋንም ሰዉነት በመገፈፍ ፤በክርስቶስ መገረዝ፤በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ ፤ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ ፤ በጥምቀት ደግሞ ፤ ከሙታን ባስነሳዉ በእግዚአብሔር አሰራር በማመናችሁ ፤ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ" (ቆላ. 2:11-12)።

የሕይወት ዛፍ በገነት መካከል ቆሞ ነበር፣ የእውቀት ዛፍም ከእርሱ አጠገብ ቆሞ ነበር። መታዘዝ እና አለመታዘዝ፣ ሕይወት እና ሞት በጣም ቅርብ ናቸው፣ ነገር ግን አንዱ ሌላዉን ያገላል ። የሕይወት አለመኖር ሞት ነው፣ የብርሃን አለመኖር ጨለማ ነው፣ የእምነት አለመኖር አለማመን ነው፣ እና የመታዘዝ አለመኖር አለመታዘዝ ነው።

## ሁለቱ ዘሮች

እባቡን ከረገመው በኋላ፣ ጌታ እንዲህ አለው፦ "በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘሯም መካከል ጠላትነትን አኖራለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ።" (ዘፍ. 3:15)። እባቡ ዘርን ትቶ ሄዷል፣ እግዚአብሔር ራሱ እንደተናገረው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፣ ዘር ማለት "ትውልድ" ማለት ነው። ጠላትነት ሊፈጠር የሚችለው በሁለት የተለያዩ ዘሮች መካከል ብቻ ነው እናም ወደ ኋላ ወደ ጠላት ይመለሳል። የእግዚአብሔር ቃል የማይሳሳት ነው እናም ማየት ለሚችሉት ምን እንደተባለ እና በትክክል ምን እንደተከናወነ ይገልጻል።

የክርስቶስ ተወዳጅ ደቀ መዝሙር ዮሐንስ እንደጻፈው ቃየን ከክፉው ነበር፦ "...እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል። እንደ ቃየን ግን፣ እርሱ ከክፉው ነበረና..." (1 ዮሐ. 3:12)። አዳም በእርግጥ ክፉው አልነበረም፣ ይልቁንም ክፉዉ ሰይጣን ነበር፣ የተቀረው ቅዱስ ጽሑፍ እንደሚያረጋግጠው (ማቴ. 6:13፤ 1 ዮሐ. 2:13-14) ። ቃየን በብሉይና በአዲስ ኪዳን የዘር ሐረጎች ውስጥ የአዳም ልጅ ሆኖ አልተዘረዘረም። የበኩር ልጅ እንደመሆኑ መጠን የመጀመሪያው የልደት መብት ይኖረው ነበር። አዳም የቃየን አባት እንደሆነ አንድ ጊዜም አልተጠቀሰም። ቢሆን ኖሮ፣ ሄኖክ ከአዳም ሰባተኛው ሊሆን ባልቻለም ነበር (ዘፍ. 5፤ ሉቃስ 3:36-38፤ ይሁዳ 14)። የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ነው፣

ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ምስጢራዊ ቢሆንም። ሔዋን ብቻ የሁሉ ሕያው እናት ነበረች (ዘፍ. 3:20)።

ከወንዶች ልጆች አንዱ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝ፡ አቤል በግ አቀረበ እና በኋላም ራሱ በመጀመሪያው ነፍስ ገዳይ የተገደለ የመጀመሪያው መስዋዕት ሆነ። በቃየን ቅናት፣ ምቀኝነት እና የመግደል ዝንባሌ ነበሩ። እነዚህ ባህሪያት በእርግጥ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከአዳም ከእግዚአብሔር ልጅ አልነበሩም፣ ይልቁንም ከሰይጣን፣ ከመጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ ከሆነው ነበሩ(ዮሐንስ 8:44)።

ቃየንም ሃይማኖተኛ ነበር እና እርሱም ቁርባን አመጣ፣ ነገር ግን ከሜዳው ፍሬዎች ብቻ ነበር። ስለዚህም እርሱ ከትክክለኛው ውድቀት እና ከሚያስፈላገው ድነትና ስርየት ጋር ምንም ግንኙነት እንደ አቤል አልፈጠረም።

ከቃየንና ከሴት የተወለዱት ሁለቱ የተፈጥሮ የዘር መስመሮች እስከ ጥፋት ውሃ ድረስ ነበሩ። አቤል ተገደለ፣ ምንም ዘር አልተወም ነበር። ስለዚህ የእርሱ የቤተሰብ የዘር ሃረግ የለንም። ስለ ኖኅ ዘመን እንዲህ እናነባለን፡- "...የእግዚአብሔርም ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ውብ እንደሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸዉም ሁሉም ሚስቶችን ለራሳቸዉ ወሰዱ ።" እነዚህ ሁለት ዘሮች ከተቀላቀሉ በኋላ፣ እግዚአብሔር፡- "መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፣ እርሱ ሥጋ ነውና... የሥጋ ሁሉ መጨረሻ በፊቴ ደርሷል..." (ዘፍ. 6:2-3+13) አለ። አዳኙ በንጹሕ ዘር በሴት በኩል ሊመጣ ነበር። ዘሮቹም የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠርተዋል፣ ነገር ግን እነርሱም ደግሞ አልታዘዙም። በዚያን ጊዜ የነበረውን እውነተኛ ነቢይ/መልእክተኛ ኖኅን አላመኑም። አሁንም እንደዚያው ነው። ጌታችን በመጨረሻው ዘመን በእግዚአብሔር ልጆች ላይ መንፈሳዊ መደባለቅን ተንብዮአል። በዚያን ጊዜ ታዋቂ የሆኑ አካላዊ ግዙፎች ተወለዱ፣ አሁን ደግሞ በሃይማኖታዊው ዓለም ውስጥ ካሉት ታዋቂ "ታላላቅ ሰዎች" ጋር እየተገናኘን ነው።

ሐዋርያው ይሁዳ የኖኅን ዘመን ከሰዶም ዘመን ጋር አነጻጽሮታል፣ ልክ ጌታችን ኢየሱስ በሉቃስ 17:26-30 እንዳደረገው — እናም የእግዚአብሔር ልጆች የፈለጉትን እንግዳ እና የተለየ ሥጋ ጠቅሷል። በቃየን በኩል እንግዳ የሆነ ዝርያ ተፈጠረ፣ ይህም በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ አልነበረም። ሳይንቲስቶች የየትኞቹን አጽሞች እንዳገኙ ማብራሪያ አልነበራቸውም እና ሙሉ በሙሉ መጻኅፍ ቅዱሳዊ ያልሆነውን የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ-ሐሳብ ለማረጋገጥ ተገደዱ። እና አሁንም "የጎደለውን አገናኝ" ይፈልጋሉ። ሐዋርያው ጴጥሮስም ኃጢአት ስለሠሩት የእግዚአብሔር ልጆች እና በሃጢአት ምክኒያት በጨለማ በሰንሰለት ስለመታሰረቻዉ ይጽፋል (2 ጴጥ. 2:4)። ኢየሱስ በተለይ ዝቅተኛ ቦታዎችን በጎበኘ ጊዜ እነርሱን ጠቅሷል (1 ጴጥ. 3:18-20)። የእግዚአብሔርን መንፈስ ተቃውመዋል፣ አልታዘዙም እና እንግዳ ስጋ ከሆነዉ ከቃየን ዘር ሰዎች ሴቶች ልጆች ጋር ተቀላቅለዋል። እግዚአብሔር አሁን እንኳን መለያየትን ይጠይቃል (2 ቆሮ. 6:14-18)፣ ሰይጣን ሁልጊዜ መደባልቅን ያበረታታል። የእግዚአብሔር ልጆች እንኳን የነቢይን መልእክት ካልሰሙ ባለመስማታቸዉ ምክኒያት በሚመጣዉ መከራ ይሰቃያሉ ።

በሉሲፈር ወደ ውድቀት የተጎተቱት የሰማይ መላእክት በከፍተኛ ቦታዎች (ኤፌ. 6:12) ይገኛሉ እና በጨለማ የታሰሩ አይደሉም። እስከ ዛሬ ድረስ በእርግጥም አንድም መልአክ ከሰማይ ወርዶ በምድር ላይ አላገባም፣ አንዳንድ አስተማሪዎች እንደሚሉት (ማቴ. 22:30)። እንግዳውን ሥጋ ለመግለጽ፣ ጳውሎስ የጻፈውን እናነባለን፦ "ሥጋ ሁሉ አንድ ዓይነት ሥጋ አይደለም፣ ነገር ግን የሰው አንድ ዓይነት ስጋ አለ ፣ የእንስሳትም ሌላ ሥጋ፣ የዓሣም ሌላ፣ የወፎችም ሌላ። ሰማያዊ አካላትም አሉ፣ ምድራዊ አካላትም አሉ፤ ነገር ግን የሰማያዊው ክብር አንድ ነው፣ የምድራዊውም ክብር ሌላ ነው።" (1 ቆሮ. 15:39-40)።

የሰው ልጅ በሙሉ በጥፋት ውሃ ተደምስሷል። ከንጹሕ የአዳም/ሴት ዘር ኖኅ፣ ሚስቱ፣ ሦስቱ ወንዶች ልጆቻቸውና የልጆቻቸዉ ሚስቶች ብቻ ተርፈዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ዘር በሙሉ ወደ ኖኅ ሦስት ወንዶች ልጆች ከዚያም በቀጥታ ወደ አዳም ተመልሶ ይጠቀሳል (ዘፍ. 9:18-19፤ ሐዋ. 17:26)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ሁለቱ መስመሮች፣ ዘሮች እና ልጆች በመንፈሳዊ ብቻ ይኖራሉ። ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጻፈ፦ "በዚህ የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች የተገለጡ ናቸዉ፦ ጽድቅን የማያደርግ እና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።" (1 ዮሐ. 3:10)። ጌታ ኢየሱስ እርሱን ለካዱ ሃይማኖታዊ መሪዎች በግልጽ እንዲህ አለ፦ "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፣ የአባታችሁንም ምኞት ልትፈጽሙ ትወዳላችሁ…" (ዮሐ. 8:44)። እርሱም መልካሙን ዘር የሚዘራ **የሰው ልጅ** እንደሆነ፣ የሚወጣው ዘርም የመንግሥት ልጆች እንደሆኑ አስረዳ። ጠላት ክፉው ነው፣ እርሱም ዘሩን ይዘራል፣ እናም እነርሱ ልጆቹ ናቸው። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈው፦ "እርሻው ዓለም ነው፤ መልካሙ ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳዱ ግን የክፉው ልጆች ናቸው…" (ማቴ. 13:36-43)።

በአንድ በኩል ቃየንን፣ የጠላት የተፈጥሮ ዘርን እናያለን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቶስን፣ መለኮታዊውን ዘርን እናያለን። የማታምነው፣ ያልታዘዘችው እና ሰይጣን በእባቡ በኩል የተናገረውን የሰማችው ሔዋን አለች፤ እዚህ ደግሞ እግዚአብሔር በመልአኩ ገብርኤል በኩል የተናገራትን ያመነችውን፣ የታዘዘችውን ማርያምን እናያለን። በተፈጥሯዊ ፍጥረት መጀመሪያ ላይ የሰይጣን ተጽዕኖ አለ፣ እዚህ ደግሞ በመንፈስ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ፍጥረት መጀመሪያ ላይ የእግዚአብሔር ተጽዕኖ አለ። ሁለቱም በመወለድ ሆነዋል እና በሥጋ ተገልጠዋል።

የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የተስፋው ዘር እንደሆነ (ገላ. 3:16-20 እና ሌሎች)፣ በሴቲቱ፣ በማርያም በኩል እንደመጣ (ገላ. 4:4-7 እና ሌሎች) በአጠቃላይ ይታወቃል። እርሱም መርገምን በራሱ ላይ እንደወሰደ (ገላ. 3:13-14) እና የሞትን መዉጊያ እንደነቀለ (1 ቆሮ. 15:55-57) ይታወቃል። ሞትን አሸነፈ፣ የድሮውን እባብ ራስ ቀጠቀጠ፣ ጠላትነትን ገደለ (ኤፌ. 2:16) እና ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀን (2 ቆሮ. 5:19)። ይህ የወንጌል ማዕከላዊ አዋጅ ነው። "እንግዲህ በአንዱ በደል ምክኒያት ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰዎች ሁሉ እንደ መጣ፣ እንዲሁም በአንዱ ጽድቅ ምክንያት ስጦታዉ ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ።" (ሮሜ 5:18)። ከእግዚአብሔር

ተለያይቶ ሁሉም ነገር ወደ ስህተት አመራ፣ ከእርሱ ጋር ታርቀን ሁሉም ነገር እንደገና መልካም ሆነ። ይህ የእግዚአብሔር ድንቅ የድነት መልእክት ለዓለም ሁሉ ነው።

## ሁሉም መልካም ይሆናል

ሰይጣን መፍጠርም ሆነ መውለድ አይችልም። በማታለል ወደ ሰው ልጅ ዘልቆ ገባ። ከእንስሳት ቤተሰብ አንድን ስለተጠቀመ፣ እግዚአብሔር አቤል ተተኪ አድርጎ ያቀረበውን በግ ተቀበለ በዚህም እግዚአብሔርን አስደሰተ። ሕግን በሠራ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የንጹሕ እንስሳትን መስዋዕት ጠየቀ። በመጨረሻም፣ አዳኙ፣ የእግዚአብሔር በግ በመሆን፣ በሞቱ በሁሉም በቂ የሆነ መስዋዕት አቀረበ። ጠላት የሰው ልጅን ሁሉ ከእግዚአብሔር ለይቶ ፍጥረትን በሙሉ ወደ ሞት ወረወረ። ስለዚህ መፍጠርም መውለድም የሚችለዉ እና የተፈጥሮና መንፈሳዊ ሕይወትን ማምጣት የሚችለዉ ብቸኛው እግዚአብሔር ፣ ከውድቀት እንድንቤዥ በብቸኛ ልጁ ወደ ሰው ልጅ መምጣት ነበረበት። በደል በሥጋና በደም አካል ስለተፈጸመ፣ የሥጋ ሕይወትም በደም ውስጥ ስለሆነ (ዘሌ. 17:11)፣ የድነታችንን የመጨረሻ ዋጋ ለመክፈል የክብር ጌታ ሰው ሆኖ ሥጋና ደም ያለውን አካል መውሰድ ነበረበት ። “ እንግዲህ ልጆች በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ስልጣን ያለዉን በሞት እንዲሽር፤ ይኸዉም ዲያብሎስ ነዉ፣ በሕወታቸዉም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፤ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።” (ዕብ. 2:14-15)። “…ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም።” (ዕብ. 9:22)።

የሚከተለው በክርስቶስ ተፈጽሟል፡- “አንተ ልጄ ነህ፣ እኔ ዛሬ ወለድኩህ።” (መዝ. 2:7፤ ማቴ. 1:18-25፤ ሉቃስ 1:26-38) እናም ኢሳ. 7:14፤ ኢሳ. 9:5-6። በእርሱ በኩል የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሁሉ ከውድቀት፣ ከሰይጣን ሥልጣን ሥር ተወስደው ነፃ ወጥተዋል፣ ጉዲፈቻቸውንም ተቀብለዋል (ገላ. 4:5-7)።

በእርግጥ ከመጀመሪያው ጀምሮ ሁለት ዘሮች፣ ሁለት መስመሮች አሉ፣ ሁለቱም ሃይማኖታዊ ናቸው። ሁለቱም በእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ያምናሉ፣ ሁለቱም መስዋዕታቸውን ያቀርባሉ፣ ሁለቱም ይጸልያሉ፣ ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው፣ ግን እንደገና በመሠረታዊነት የተለያዩ ናቸው። ልዩነቱ የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች እንደ አቤል በድነት አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይደረጋል። አቤል በግ አቀረበ፣ ምክንያቱም ለእርሱ ስለተገለጠለት፣ በዚህም እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ። የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች ድነታቸውን (1 ጴጥ. 1:18-21) እና በጎለጎታ መስቀል ላይ ባለው የመጨረሻና ለዘላለም በቂ በሆነው መስዋዕትነት (ዕብ. 10:12-14) በእምነት ጽድቃቸውን (ሮሜ 5:1) ያገኛሉ። እውነተኛ ያልሆኑ ልጆች በሃይማኖታዊ እምነት መሠረት በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ይሠዋሉ፣ ነገር ግን ከብቸኛው እውነተኛ አምላክ ጋር በብቸኛው አስታራቂ በኢየሱስ ክርስቶስ (1 ጢሞ. 2:5) አማካኝነት ቀጥተኛ ግላዊ ግንኙነትን

ፈጽሞ አያገኙም። ሁልጊዜም በባህላዊ መንገዳቸው፣ በትምህርታቸው መሠረት ይሞክራሉ። ተሸፍነው ይቀራሉ፣ የጠፉ መሆናቸውን ማወቅ አይችሉም፣ ስለዚህም ለምን መዳን እንዳለባቸው አይረዱም። ስለ ድነት ዕቅድ የሚሰብክ ሁሉ ድነትና እርቅ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ አሳማኝ በሆነ መንገድ ማሳየት አለበት። እባቡን የተፈረደበትን መንገድ ከመጀመሪያው ጀምሮ መፈለግ እና የድነትን መንገድ ማሳየት አለብን። “ሙሴም በምድረ በዳ እባቡን እንደ ሰቀለ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል፤ በእርሱ የሚያምን ሁሉ እንዳይጠፋ፣ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው።” (ዮሐ. 3:14-15)።

የተገለጠው ቃል ብርሃን፣ የእግዚአብሔር ሙሉ ምክር የተጻፈበት፣ ከመቼውም ጊዜ በላይ በብሩህ ያበራል። የድነት መንገድ ተገልጦልናል፣ ከውድቀቱ ጀምሮ እስከ እግዚአብሔር የመጨረሻ ድል ድረስ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጠው።

## እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በቃሉ መሠረት ያደርጋል

በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ መረዳት በተለይ አስፈላጊ ነው - ቅዱስ ጽሑፍን በማብራራት ሳይሆን መፈጸሙን በማሳየት። ጌታችን የተናገረው በምድር ሁሉ በየቀኑ ይደገማል፦ “መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፤ በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁና፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው። ሕይወትም እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።” (ዮሐ. 5:39-40)። በመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ መምጣት እና በግል ልምምድ እርሱን ማወቅ አለብን፣ ያለዚያ ግን በነገረ መለኮታዊ ፍልስፍናዎች ጊዜያችንን እናባክናለን (ቆላ. 2:8)።

ከጌታችንና ከአዳኛችን ጋር ቀጥተኛና ቅርብ ግንኙነት ያስፈልገናል። በሉቃስ 24 ላይ እንደተመዘገበው እርሱ ከእኛ ጋር መራመድና መነጋገር ከቻለ ብቻ፣ ሁሉም ነገር ለእኛ ይገለጣል። ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመር ብቻ በቂ አይደለም፤ ይህ በሁሉም ክርስትና ውስጥ የሚደረግ ነው። በተፈጥሮ፣ የሰው ልጅ ሁሉ በራሱ አስተሳሰብ እግዚአብሔርን ይተላለፋል። በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል ጌታ እንዲህ አለ፦ “ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ አይደለምና፣ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለም፣ ይላል እግዚአብሔር።” (ኢሳ. 55:8)። እርሱ የራሳችንን ሐሳቦችና መንገዶች ትተን በቃሉ እንደተገለጸው ለሱ ሐሳብ ልባችን እንድንከፍት ይጠይቀናል። እርሱ ብቻ ቃሉን ለእኛ ሊያሳውቀን እና መንገዱን ሊያሳየን ይችላል።

እስካሁን ድረስ ጠላት የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ በሰዎች አእምሮና አፍ ውስጥ አጣምሞታል። ሐዋርያው ጴጥሮስ በጊዜው እንኳን ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትንም እንዳደረጉት ሁሉ ጳውሎስ የጻፈውንም እንዳጣመሙት ይጽፋል (2 ጴጥ. 3:16)። ጠላት በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጀመሪያ እንደነበረው ምንም ነገር አልተወም። እያንዳንዱ ትምህርትና አሠራር ተለውጧል። ውጤቱም “የባቢሎን ካባ” የተሸፈነ አስከፊ ድብልቅ ነበር። በሮማ ግዛት የመንግስት

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጀመሪያው የክርስትና ድርጅት ተቋቋመ፣ ነገር ግን በውስጡ ከመጀመሪያው ክርስትና ጋር የነበረ ምንም ነገር አልቀረም። በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረት ላይ ከተመሠረተው አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም የጋራ ነገር ያልነበረው ሙሉ በሙሉ የተለየ ቤተ ክርስቲያን ሆነ። በተፈጥሮ ፍጥረት መጀመሪያ ላይ ጠላት ተጽዕኖውን ጀመረ። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ላይ ተመሳሳይ ነገር አደረገ። ማታለልንና ትርጉም መለወጥን ጀመረ እና ክርስትናን ወደ ውድቀቱ ጎተተዉ። ሁላችንም ወደ ታላቁ ሃይማኖታዊ ማታለል ውስጥ ተወልደናል። ማታለሉ የተከናወነው በምሥራቃውያን ሃይማኖቶች ውስጥ አይደለም፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ግላዊ በክርስቶስ ውስጥ መገለጥ አልተቀበሉም እና ምንም መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራቸውም። ማታለሉ የተከሰተው በምዕራባውያን ክርስቲያናዊ ሃይማኖት ውስጥ ነው።

እግዚአብሔር አሁን እንኳን በቃሉ መሠረት የሆነ ነገር ሲያደርግ፣ በተቋቋመው ሃይማኖት እንደ ቀጥተኛ ሁከት ይቆጠራል። የጌታችን አገልግሎት በዚያን ጊዜ ለነበሩት የተቋቋመው እምነት መንፈሳዊ መሪዎች ታላቅ ሁከት ነበር። በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የሐዋርያት አገልግሎትም ተመሳሳይ ነበር። ባለፉት መቶ ክፍለ ዘመናት የነበሩት ሁሉም ተሐድሶ አራማጆች እና ሁሉም የመነቃቃት ሰባኪዎች በዘመናቸው ታላቅ ችግር አስከትለዋል ተብለው ተቆጥረዋል እና በተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት እንደ መናፍቃን ተመድበዋል፤ ተቀባይነት አጥተው ተሰደዱ።

የብሉይ ኪዳን ነቢያትን አስመልክቶ እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል ለአባቶች እንደተናገረ እና ከዚያም መልሱን ባመጣልን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል (ዕብ. 1:1-3) እንደተናገረ ተነግሮናል። “ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ነበሩ፤ ከዚያ ወዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፣ ሁሉም ወደ እርሷ በኃይል ይገቡባታል” (ሉቃስ 16:16)።

ጌታችን፡- “እነሆ፣ ነቢያትንና ጥበበኞችን፣ ጸሐፊዎችንም ወደ እናንተ እልካለሁ…” (ማቴ. 23:34) የሚለውን ቃል ኪዳን ሰጥቷል። ሐዋርያው ጳውሎስ በእርግጥ እንደተፈጸመ አረጋግጧል፡- “እግዚአብሔርም አንዳንዶችን በቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ አስተማሪዎች… ወዘተ አድርጎአል” (1 ቆሮ. 12:28፤ ኤፌ. 4:11)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እና መልእክቶች የሐዋርያዊ እና የትንቢታዊ አገልግሎት የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን አካል መሆኑን ያረጋግጣሉ። <u>እግዚአብሔር ኤልያስን የመሰለ ነቢይ በልዩ ፈታኝ ተልዕኮ ለመላክ እንዳሰበም የተረጋገጠ ነው</u> (ሚል. 4:5-6)። ይህንን በአእምሯችን ልንቀበልና በሙሉ ነፍሳችን ልናምነው ይገባል። ምክንያቱም ይህ በዘመናችን ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከተሰጡ ከዋናዎቹ ተስፋዎች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ታሪክ ሲሠራ እና መጥምቁ ዮሐንስ መሲሑን ሲያስተዋውቅ፣ የተቋቋመው የአይሁድ ቤተ ክርስቲያን እንደ አደረገዉ ሁሉ፣ በእኛ አስተሳሰብ፣ ስብከትና ዝማሬ እግዚአብሔርን መተላለፍ ምንም ትርጉም የለውም። ቅዱስ ጽሑፍ የሚለውን ማመን እና እያንዳንዱን ተስፋ ማክበር አለብን፣ ምክንያቱም የዚያን ጊዜ ብቻ ነው በዚያ በተባረከ ፍጻሜ ልንሳተፍ የምንችለው። እውነተኛ አማኞች የተስፋ ልጆች ናቸው (ገላ. 4:28)፣ የተስፋን ቃል ይቀበላሉ (ሮሜ 9:8-9) እና በተስፋው መንፈስ

ይሞላሉ (ሐዋ. 2:33)። የእውነትን ቃል ካመነና ከተቀበልን በኋላ ብቻ ነው በተስፋው መንፈስ ቅዱስ መታተም የሚፈጸመው (ኤፌ. 1:13፤ 2 ቆሮ. 1:20-22)።

በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ መንግሥት ውስጥ እውነትን ለመስበክ አንድን ሰው ተጠቅሟል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሂደት ውስጥ የተወሰኑ የእግዚአብሔር ሰዎች መታየታቸው በአጠቃላይ የተለመደ ነው። ከተሐድሶ ዘመን ጀምሮ የተከሰቱት የተለያዩ መነቃቃቶችም እንዲሁ በጥሩ ሁኔታ ተመዝግበዋል፣ ባለፈው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የጀመረውና አሁንም የቀጠለው የጴንጤቆስጤ መነቃቃትም ጭምር። በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ክፍል ይህ እንቅስቃሴ ምንም ትርጉም አልነበረውም፣ ውድቅ ተደርጓል፣ ምክንያቱም ከተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት ውጭ ነበር፣ እናም እንኳ አልታወቀም። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በጀመረው ኃያል መነቃቃት አማካይነት የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ በፍጥነት በማደግ ላይ ያለ የሃይማኖት ቤተ እምነት ሆነ። ከሁለተኛው የቫቲካን ምክር ቤት (1962-1965) ጀምሮ፣ ዓለም አቀፍ ተወካዩ ዴቪድ ዱፕሌሲስ፣ “ሚስተር ጴንጤቆስጤ” እየተባለ የሚጠራው፣ እንደ ታዛቢ በተሳተፈበት ወቅት፣ የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ በሮማ ቤተ ክርስቲያን እና በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይሁንታን አገኘ። የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ከሚስተር ዱፕሌሲስን ጋር በግላቸው አንድ ቀን ሐምሌ 1964 ዓ.ም. በሮም ወደ ቫቲካን ለስብሰባ አብረዉ ሄደዋል።

<u>አሁን ጥያቄው ይነሳል፦ እግዚአብሔር በምድር ላይ ከደረሱት ሁሉ ታላቁን ድነትና ፈውስ መንፈሳዊ መነቃቃት ለመጀመር ልዩ ዕቃ አድርጎ የተጠቀመው ማንን ነበር?</u> ብዙዎች ከዓመታት በኋላ ወይም “በሁለተኛው” እና “በሦስተኛው የመነቃቃት ሞገድ” የታወቁትን ብቻ ሰምተዋል፣ ይህም ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት ያካትታል። ነገር ግን በ1946 እንዴት ተጀመረ? እና የመጀመሪያው ግብ ምን ነበር? እንደ ሁልጊዜው፣ ነገሮች ከከበረ ጅምር በኋላ ተበላሹ፣ ነገር ግን እውነቱ ኖረ፣ ከሁሉም ማታለያዎች ባሻገር ። እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ጀምሮ ያወጀው ሁሉ ይፈጽማል። በአራቱ ወንጌሎች ውስጥ ጸሐፊዎቹና ሐዋርያት ሁልጊዜ ወደ መጀመሪያው ተመልሰዉ ይጠቁሙ ነበር። ከሕይወት ቃል ያዩትንና የሰሙትን ጠቅሰዋል (ሐዋ. 1:1-3፤ 2 ጴጥ. 1:16-21፤ 1 ዮሐ. 1:1-4 እና ሌሎች)። <u>በዘመናችን ምስክር ማን ነበር? በዚህ የመጨረሻ መነቃቃት መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር ያደረገውን የተመለከተና የተገኘ ማን ነበር? እግዚአብሔር ቃሉን በማን አፍ ውስጥ አኖረ? እርሱ ራሱ የላከው ማንን ነበር?</u> የራሳቸውን አገልግሎት በኋላ የጀመሩት ሌሎች ከመጀመሪያው መልእክት አፈንግጠው ሊሆን ይችላል ወይም ራሳቸው በወረሷቸዉ ትምህርቶች ቀጥለው ሊሆን ይችላል።

ዋናው ጥያቄ የሚከተለው ነው፦ <u>“ቅዱስ ጽሑፍ ምን ይላል እና በእርሱ ውስጥ ምን ተስፋ ተሰጥቷል?”</u> በአዲስ ኪዳን ዘመን ዉስጥ ያለው እውን መሆን የጀመረው መንገዱን ለማዘጋጀት በተስፋ በተሰጠው ነቢይ አገልግሎት ነው (ሚል. 3:1፤ ኢሳ. 40:3)። እነዚህ ሁለት ጥቅሶች በወንጌሎች ውስጥ፣ በተለይም በማርቆስ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች ውስጥ ተጠቅሰዋል።

የአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሰዎች ሁልጊዜ ነቢያት ወደተናገሩት ይመለሱ ነበር እና ሁሉንም ነገር በቅዱስ ጽሑፍ መሠረት ያደርጉ ነበር። በአጠቃላይ፣ አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን 845 ጊዜ ይጠቅሳል። አሁን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚከናወነውን ሁሉ በቅዱስ ጽሑፉ/Holy scripture/ መሠረት ላይ ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በቃሉ መሠረት ያደርጋል። እውነተኛ እምነት ሊመሠረት የሚችለው በተስፋዎች(ቃል በተገቡ) ላይ ብቻ ነው፣ ይህም ይፈጸማል።

በአሞጽ 3:7 ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፦ "እግዚአብሔር አምላክ ግን ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ሳይገልጥ ምንም አያደርግም።" በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉልህ የሆነ ነገር ሊከናወን በነበረበት ጊዜ ሁሉ፣ እርሱ እውነተኛ ነቢይን በልዩ መልእክት ላከ። እርሱ ኖኅን፣ አብርሃምን፣ ሙሴን፣ ኤልያስንና ሌሎችንም አዘዘ። በአዲስ ኪዳን መጀመሪያ ላይ፣ መጥምቁ ዮሐንስ ለተስፋው መሲሕ መንገድ አዘጋጀ። ጌታ የመጀመሪያዉ ስዓት ሰው የሆነውን ጴጥሮስን አዘዘ፣ ለእርሱም የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፎች ሰጠው፣ በዚህም መለኮታዊ ሥልጣንን አቀረበለት። ጌታ ደግሞም ጳውሎስን በልዩ ተልእኮ የማስተማር አገልግሎት በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ላይ ሾመው። በፓትሞስ ደሴት ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ያለውን ሙሉ መገለጥ በራእይ እንዲያይ ተፈቀደለት፣ ይኸንም በ22 ምዕራፎች ውስጥ መዘገበ። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ነገሮችን በፍጹም ሥርዓት አድርጓል፣ እናም ጠላት ሁልጊዜ መለኮታዊውን ሥርዓት ለማበላሸትና ለማጥፋት ሞክሯል።

## ግልጽ እይታ

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድታገኝ የፈለገው ሁሉ በቃሉ እንደ ተስፋዎች(ቃል እንደተገቡ) ተመዝግቧል። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክስተቶች፣ እንደ ጦርነት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ እና የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ስለሚመጡት ነገሮች ሲናገሩ፣ እኛ ስለ ትንበያዎች እየተነጋገርን ነው። ኤልያስን የመሰለ እውነተኛ ነቢይ ተስፋ ተሰጥቶናል(ቃል ተገብቶልናል)። ብዙዎቹ የሐሰት ነቢያትና ክርስቶሶችም ተተንብየዋል። አሁን የምንኖረው በጸጋ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው እናም እግዚአብሔር ምን ተስፋ እንደሰጠ እና ምን እያደረገ እንደሆነ የማወቅ መብት፣ እንዲያውም ግዴታ አለብን።

ከክርስቶስ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ምጽአት ጋር በተያያዘ የተሰጡትን ሁለቱን ተስፋዎች እንመልከት። ሚልክያስ 3:1 በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ተፈጽሟል። ጌታ ኢየሱስ ራሱ በግልጽ እንዲህ አለ፦ "ነገር ግን ምን ለማየት ወጣችሁ? ነቢይን? አዎ፣ እላችኋለሁ፣ ከነቢይም የሚበልጥ ነው። ስለ እርሱም የተጻፈው ይህ ነውና፦ እነሆ፣ መንገድህን በፊትህ የሚያዘጋጅ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ።" (ማቴ. 11:9-10)። በሁለተኛ ደረጃ፣ "እነሆ፣ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁና…" (ሚል. 4:5) የሚለው ተስፋ አለን። የሚል. 4:5-6 ያለውን ትንቢት ጌታ ኢየሱስ ወደፊት አስቀምጦታል፣ ዮሐንስ

አገልግሎቱን ከጨረሰ በኂላ፣ በማር. 9:12 እና ማቴ. 17:11 ላይ እንደታየው፡- "ኤልያስ በእውነት መጀመሪያ ይመጣል፣ ሁሉንም ነገር ያድሳል::"

ዮሐንስ የድነት ቀን መጀመሪያ ላይ ወደ መድረክ ወጣ:: የመጨረሻው ነቢይ የድነት ቀን መጨረሻ ላይ፣ ፍርዶች ምድርን ከመምታታቸው በፊት፣ ፀሐይ ወደ ጨለማ ከመለወጧ እና ጨረቃ ወደ ደም ከመለወጧ በፊት መታየት አለበት (ኢሳ. 13:6-16፤ ኢዩኤል 2:31፤ ሶፎ. 1:14-18፤ ሐዋ. 2:19-21፤ 1 ተሰ. 5:2፤ 2 ጴጥ. 3:10፤ ራእይ 6:12-17):: ያ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ጌታ እንደዚህ ይላል በሚለው መሠረት ያለው ግልጽ እውነት ነው::

የእግዚአብሔርን ዕቅድ ትንሽም ቢሆን የሚያውቅ ሁሉ የጸጋው ዘመን የድነት ቀን እንደሆነ ያውቃል፣ በብሉይ ኪዳን እንደተነገረው (ኢሳ. 42:6፤ ኢሳ. 49:6-8):: ጌታ የሰራዉ ቀን ነው (መዝ. 118:24)፣ አብርሃም ያየውና በደስታ የሞላበት ቀን ነው (ዮሐ. 8:56):: "በዚያ ቀን እኔ በአብ እንዳለሁ፣ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፣ እኔም በእናንተ እንዳለሁ ታውቃላችሁ::" (ዮሐ. 14:20)::

ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡- "ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው ነበር… እርሱ ስለ ብርሃን ለመመሥከር ምስክር ሆኖ መጣ፣ ሁሉም በእርሱ በኩል እንዲያምኑ::" (ዮሐ. 1:6-7):: የተለያዩ አስተያየቶች ባላቸዉ በብዙ ወንጌላውያን ሳይሆን፣ እንደ ተስፋዉ በእግዚአብሔር በተላከ ሰው አገልግሎትና መልእክት የተነሳ ነው ሁሉም በእውነት ማመን ያለባቸው :: በሁሉም ዘመናት እንዲህ ነበር፣ እናም በዚህ ጊዜም እንዲህ ሆነ:: እግዚአብሔር ቃሉን ወይም መንገዱን አይለውጥም::

በዮሐንስ 1:19 ላይ ተመዝግቦአል፣ ልዑካን ወደ መጥምቁ ዮሐንስ  እርሱ ማን እንደሆነ በግል ለመጠየቅ ተልኮ ነበር :- "መሰከረም አልካደም፤እኔ ክርስቶስ አይድለሁም ብሎ መሰከረ:: እነርሱም፡- እንግዲያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? አሉት:: እርሱም፡- አይደለሁም አለ:: ያ ነቢይ ነህን? እርሱም፡- አይደለሁም ብሎ መለሰ:: እነርሱም፡- ማን ነህ እንግዲያስ? ለላኩን መልስ እንድንሰጥ:: ስለ ራስህ ምን ትላለህ? አሉት::  እርሱም፡- ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለው፡- **የጌታን መንገድ አስተካክሉ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰዉ ድምፅ እኔ ነኝ አለ::** የተላኩትም ከፈሪሳውያን ነበሩና :- እንግዲያስ አንተ ክርስቶስም ወይም ኤልያስም ወይም ያ ነቢይ ካይደለህ፤ ስለምን ታጠምቃለህ? አሉት::" (ቁ. 20-25):: እርሱ ኤልያስ አልነበረም፣ ክርስቶስም አልነበረም፣ ወይም በዘዳግም 18:15-19 የተጠቀሰው ነቢይ አልነበረም:: የኤልያስ ጥያቄ ልክ ክርስቶስ ወይም ነቢይ እንደሆነ እንደተጠየቀው ሁሉ ግልጽ በሆነ መልኩ ተመልሷል:: አገልግሎቱ የድነት ዕቅድ አካል ነበር እናም እርሱ ምን እንደሚሠራ ያውቅ ነበር::

## ትክክለኛ ቦታ አሰጣጥ

አሁን ደግሞ ኢየሱስ ለምን ኤልያስ ብሎ እንደጠራው ወደሚለው ጥያቄ እንሸጋገራለን፣ ምንም እንኳን ይህንን ጥያቄ ግልጽ በሆነ "አይደለሁም!" ብሎ የመለሰዉ ቢሆንም እና መልሱም  መጽሐፍ

ቅዱሳዊ ነበር ። እዚህ ላይ እኛ የምንመለከተው የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን የተለየ ባሕርይን ነው። ብዙ ጊዜ ነገሮች በአንድ ጥቅስ ውስጥ ይገኛሉ፣ ነገር ግን ፍጻሜአቸዉ ሁለት ሺህ ዓመታት ልዩነት ሊኖረዉ ይችላል። በሁሉም ተስፋዎች(ቃል በተገቡ) ውስጥ ማለት ይቻላል፣ ከክርስቶስ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ምጽአት ጋር የተያያዙ ክስተቶች በተመሳሳይ አውድ ውስጥ ተጠቅሰዋል።

መልአኩ ገብርኤል ለዘካርያስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ሲናገር፣ የሚልክያስ 4:5-6 ያለውን የኤልያስ-ተስፋ የመጀመሪያውን ክፍልም ጠቅሷል፦ "እርሱም የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች… ይመልስ ዘንድ… በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል።" (ሉቃስ 1:17)። በዚህ ማግለጫ መሠረት፣ ጌታችን በማቴዎስ 11:14 ላይ፦ "…ይህም ይመጣ ዘንድ የነበረው ኤልያስ ነው" ብሎአል። የሚልክያስ 4:6 ሁለተኛውን ክፍል፦ "…የልጆችንም ልብ ወደ አባቶቻቸው…" መልአኩ ገብርኤል አልጠቀሰም፣ ምክንያቱም አሁን ብቻ ነው ወደ ፍጻሜ የሚመጣው። እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች በነቢያት አማካኝነት ለአባቶች ተናግሯል (ዕብ. 1:1)። ከዚያም የብሉይ ኪዳን አባቶችን ልብ ወደ አዲስ ኪዳን ልጆች የመመለስ ጊዜ መጣ። ሐዋርያው ጳውሎስ፦ "ለአባቶች የተገባላቸውን ተስፋ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ለልጆቻቸው እንደፈጸመ የምሥራችን እንነግራችኋለን…" (ሐዋ. 13:32-33) አስተምሯል። የሚልክያስ 4:5-6 የተሰጠውን ተስፋ በቃሉ መሠረት መወሰድ አለበት ብሎ የሚናገር ሁሉ፣ በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ የካሪዝማቲክ ክበቦች እንደሚደረገው፣ እና ልጆችን ከአባቶች ጋር እና አባቶችን ከልጆች ጋር ለማስታረቅ በቤተሰብ ፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፍ ሁሉ፣ በቀጥታ ከክርስቶስ መመለስ በፊት ካለው የመጨረሻ አገልግሎት ጋር የተገናኘ የዚህን ትንቢት አስፈላጊነት እንኳ አልተረዳም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች በዘፈቀደ መተርጎም የሌለባቸው፣ ነገር ግን በድነት ዕቅድ ውስጥ ባላቸው አቀማመጥ መታወቅ እና እንደ ፍጻሜያቸው በትክክለኛ ቅደም ተከተል መዘጋጀት ያለባቸውን ምክንያት ለማስረዳት የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል።

በኢሳይያስ 35:1-7 ውስጥ፣ ከጌታ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ምጽአት ጋር የተያያዙ ዝርዝሮች ተጠቅሰዋል። በቁጥር 4 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "ልባቸው ፈርቶአልና፦ ብርቱ ሁኑ፣ አትፍሩ፤ እነሆ፣ አምላካችሁ በቀልን ይዞ ይመጣል፣ አምላክም በብድራት ይመጣል፤ እርሱም ይመጣል ያድናችኋል በሉ።" በእርግጥም፣ ጌታ አምላክ ራሱ መጣ እናም ድነታችንን አመጣ። በቁጥሮች 5 እና 6 ላይ አይነ ስዉራን እንደሚያዩ፣ ደንቆሮዎች እንደሚሰሙ፣ አንካሶች እንደሚሄዱ እና ዲዳዎች እንደሚናገሩ ተነግሮአል። ያ ተፈጽሟል፣ ነገር ግን ስለ በቀልና ብድራት ያለው ክፍል ወደፊት ይቀራል።

በኢሳይያስ 61 ውስጥ በአንድና በተመሳሳይ ጥቅስ ውስጥ መሲሑ ተቀባይነት ያለውን የእግዚአብሔር ዓመትና የአምላካችንን የበቀል ቀን እንደሚያውጅ ተነግሮናል። በሉቃስ 4 ላይ ጌታ ኢየሱስ ይህንን ቅዱስ ጽሑፍ በምኩራብ አነበበ፣ ነገር ግን ከመጀመሪያው ክፍል በኋላ አቆመ፦ "…ተቀባይነት ያለውን የእግዚአብሔርን ዓመት ለመስበክ።" (ሉቃስ 4:19)። ከዚያም ጥቅልሉን ዘግቶ

መልሶ ሰጠ። ስለ በቀል ቀን ያለውን ሁለተኛውን ክፍል አልጠቀሰም። አሁንም ወደፊት ነው፣ ያለዚያ፦ "ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጽሟል" (ቁ. 21) ሊል አይችልም ነበር።

በኢዩኤል 2 ውስጥ በጸጋ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ተስፋን እናገኛለን፣ እናም በተመሳሳይ ጥቅስ ውስጥ ስለ አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን ተነግሮናል። "እንዲህም ይሆናል፤ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፤ በጽዮን ተራራም በኢየሩሳሌምም መድኃኒት ይገኛል፣ እግዚአብሔር እንደተናገረ..." (ቁ. 32)። ሐዋርያው ጴጥሮስ በብዓለ ሃምሳ ቀን በስብከቱ ይህንን ጥቅስ ጠቅሷል፦ "እንዲህም ይሆናል፤ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል።" (ሐዋ. 2:21)። እርሱም ደግሞ በቁጥሩ መካከል አቆመ፣ ምክንያቱም በኢየሩሳሌምና በጽዮን ተራራ ስላለው መድኃኒት ያለው ሁለተኛው ክፍል አሕዛብን ጭምር በጸጋ ዘመን አይመለከትም ነበር፣ ይልቁንም ለእስራኤል ለተሰጠው ጊዜ ነው (ሐዋ. 15:13-15፤ ሮሜ 11:25-29 እና ሌሎች)።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ መነዳት በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ መሠረት ምን መከናወን እንዳለበት አውጀዋል። ትክክለኛው አቀማመጥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ላሉት አገልጋዮች ተሰጥቷል፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል እንዴት መከፋፈል እንደሚችሉ የማወቅ ልዩ እድል ላላቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ፈጽሞ መተርጎም የለበትም፣ ነገር ግን በፍጻሜው መታየት እና በዚያ መሠረት መቀመጥ አለበት።

የቀዳሚው ተግባር ብሉይ ኪዳንን ከአዲስ ኪዳን ጋር ማገናኘት እና የኤልያስ-ተስፋ የመጀመሪያውን ክፍል መፈጸም ነበር። ጌታ ኢየሱስ ከሦስት ደቀ መዛሙርቱ ጋር በደብረ ታቦር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ሙሴና ኤልያስ ተገለጡ (ማቴ. 17:1-12፤ ማር. 9:2-13፤ ሉቃስ 9:28-36)። ሁለቱም ታላላቅ ነቢያቶች ቢገኙም፣ ደቀ መዛሙርቱ ከጊዜ በኋላ ስለ ኤልያስ ብቻ ጠየቁ (ማቴ. 17:10)። ለምን ብለን መጠየቅ አለብን? በእርግጥም፣ መልሱን ከጌታ አፍ በግል እንድንቀበል ነው፦ "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ኤልያስ በእውነት መጀመሪያ ይመጣል፣ ሁሉንም ነገር ያድሳል።" (ቁ. 11)። ይህ መግለጫ በእርግጥም ወደፊት ያለውን ያመለክታል። መጥምቁ ዮሐንስን በተመለከተ፣ ጌታ፦ "...ያ ኤልያስ መጥቶአል፣ አላወቁትምም፣ የወደዱትንም ሁሉ አደረጉበት" (ቁ. 12) አለ።

የእግዚአብሔር ልጆች ልብ አሁን ወደ "የአባቶች እምነት"፣ ወደ መጀመሪያው—ወደ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሳይሆን፣ በግል ቤቶች ወደ ተፈጥሮአዊ አባቶች ሳይሆን፣ ወደ ሐዋርያዊ የእምነት አባቶቻችን አንድ ጊዜ ለቅዱሳን ወደ ተሰጠው (ይሁዳ 3) – በቀጥታ ወደ ክርስቶስ፣ በትምህርትም በተግባርም መመለስ አለበት። ጌታችን የዚያን ጊዜ መልሱን ሰጥቶናል አሁንም ተመሳሳይ መልስ ይሰጠናል። ክርክሮች ዋጋ የላቸውም፣ ምክንያቱም ከአእምሮ አመክንዮ የመጡ ናቸው። ጌታችን የሚለውን መቀበል እና እንደተጻፈው ማመን አለብን። በድነት ዕቅድ መሠረት፣ ሁሉም ነገር አሁን ወደ መጀመሪያው ሁኔታው መመለስ አለበት። ያ ከክርስቶስ መመለስ በፊት ለቤተ ክርስቲያን የተገባ ቃል ኪዳን ነው፤ የሰዓቱ ትእዛዝ ነው። እንዲህም ተጽፏል፣ እናም እንዲህም ይሆናል።

አሁን፣ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት፣ወደ ነበረበት መመለስ በትንቢታዊ አገልግሎት በሙሉ መፈጸም አለበት። እግዚአብሔር እንደገና ታሪክ እየሠራ ነው እና ኤልያስን የመላክ ተስፋው "አዎ" እና "አሜን" ነው እናም ተፈጽሟል። ነገር ግን መጥምቁ ዮሐንስን እንዳደረጉት፣ የዛሬዉንም መልእክተኛ እንደወደዱ አደረጉት። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው በእውነት ማመን የሚችሉ ሁሉ ብፁዓን ናቸው፣ ምክንያቱም ለእነርሱ ብቻ ነው ሊገለጥ የሚችለው። እግዚአብሔር የተናገረውንና የተስፋ ቃሉን ከማያምን ሰው ጋር መነጋገር አይቻልም። በእርሱ አስተሳሰብ እግዚአብሔርን የሚይተላለፍ ሁሉ፣ በመናገርም በስብከትም በአጠቃላይ እርሱን ይተላለፍል። ጌታችን በማርቆስ 12:29-30 ላይ እንደተናገረው እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ፣ እንዲያውም በአእምሮአችን ልንወደው ይገባል። የተናገረውን በእውነት የሚያምን ሁሉ እንዲሁ ያስባል።

ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት፣ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የማደስ እና ቤተ ክርስቲያኑን ወደ መጀመሪያው ሁኔታዋ የመመለስ ዓላማ አለው። ይህ **ጌታ እንዲህ ይላል** ነዉ። ስለ አዳኛችን እንዲህ ተጽፏልና፦ " እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረዉ ፤ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባል።" (ሐዋ. 3:21)። በቁጥር 19 ላይ ተነግሮናል፦ "**...እንዲሁም ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመናት እንዲመጣ፤ እርሱም ቀድሞ የተሰበከላችሁን ኢየሱስ ክርስቶስን ይልካል**።" አሁን ደግሞ ፍጹም ግልጽ ነው፦ መመለስና መጽናናት መጀመሪያ ይመጣሉ፣ ከዚያም ኢየሱስ ይመለሳል። አሜን! ይህ በዘመናችን የእግዚአብሔርን ሙሉ ምክር ማወጅ ነው (ሐዋ. 20:27)! ይህ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ታላቁን ምሥጢር ይፈታል (ኤፌ. 3)! ብዙዎች ስለ መጨረሻው ዘመንና ስለ ዳግም ምጽአት ይናገራሉ፣ ነገር ግን የመመለስን ተስፋ ሳያምኑ እና ፍጻሜውን ሳይጠብቁ፣ ይስታሉ እና እጅግ በጣም ያዝናሉ። በእውነትም ከሁሉም በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ተስፋዎች አንዱ ነው አሁን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተፈጸመ ነው። በኢሳይያስ 28:11 ላይ እንዲህ ይላል፦ "በሌላ አንደበት በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል።" በቁጥር 12 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "...የደከመዉን አሳርፉ ፤ ይህችም ማረፊያ ናት አላቸዉ ፤ እነርሱ ግን መስማትን እንቢ አሉ ።" ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ጥቅስ ጠቅሷል፣ ነገር ግን በሌላ አንደበት መናገርን ብቻ ጠቅሷል (1 ቆሮ. 14:21)። ይህ ከብዓለ ሃምሳ ቀን ጀምሮ ሲከናወን ቆይቷል። ሁለተኛው ክፍል፣ መንፈሳዊ መነቃቃት፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከክርስቶስ መምጣት በፊት (ሐዋ. 3:20-21) ከተስፋው መመለስ ጋር በተያያዘ አቅርቧል። ይህ አሁን እየተከናወነ ነው። በእርሱ ውስጥ ዕድል ያላቸው ሁሉ ብፁዓን ናቸው! የመጨረሻው መንፈሳዊ መነቃቃትና ሂወት መስጠት ከሁሉም ነገሮች ሙሉ በሙሉ መመለስ ጋር አብሮ መሄድ አለበት። የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ነው፣ በትክክል መቀመጥ ብቻ ነው ያለበት።

## እግዚአብሔር ሐሳቡን ያካፍለናል

ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጣበት ጊዜ፣ አስተማሪዎች የራሳቸው ማብራሪያ፣ ትርጓሜና የሚጠብቁት ነገር ነበራቸው። በዚያን ጊዜ 109 ትንቢቶችና ትንበያዎች ከብሉይ ኪዳን የተፈጸሙት

ሃይማኖታዊ መሪዎች እንኳ ሳያውቁት ነበር። እነርሱ በራሳቸው ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ተጠምደው ነበር፣ እነዚህም በጣም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስለው ይታዩ ነበር። ታሪክ በዘመናችንም ይደገም ይሆን?

በብዓለ ሃምሳ ዕለት የአብ ተስፋ (ሐዋ. 1:4) የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ተፈጸመ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የተሰጡት ሁሉም ተስፋዎች እየተፈጸሙ ናቸው። ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል፣ <u>የአማኞች ታላቅ ተስፋና ምኞት የኢየሱስ ክርስቶስ የመመለስ ተስፋ (ዮሐ. 14:1-3) ነው፣ ይህም በሁሉም እውነተኛ አማኞች የሚጠበቅ ታላቅ ክስተት ነው</u>። እግዚአብሔር ተስፋዎቹን ለመፈጸም በተዘጋጀ ቁጥር፣ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገር በምድር ላይ ይከሰታል።

ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር በተያያዘ አብርሃም ጎልቶ ይታያል። እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ተናገረው እና ራሱን ገለጠለት። ይህንንም ዘፍጥረት 12ን ጨምሮ በበርካታ ምዕራፎች ውስጥ ተመዝግቦ እናገኛለን። ጌታ ዘሩ በባዕድ ምድር ተጨቁነዉ ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ ነጻ እንደሚወጡ ቃል ገባለት። <u>ጊዜው ሲፈጸም፣</u> እግዚአብሔር ለሙሴ በተፈጥሮ ባልሆነ እሳት ተገለጠለት፣ ይህም በተፈጥሮ ቁጥቋጦ ውስጥ ነበር (ዘጸ. 3:2)፣ እናም ሕዝቡን ነፃ የማውጣት ተልዕኮ ሰጠው። ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ሁልጊዜ የሚከሰተው እግዚአብሔር ታሪክ በሚሠራበት ቦታ ነው፣ ይህም እዚህ ማለት፣ ከተፈጥሮአችን ጋር በእኛ ግዛት ውስጥ ነው።

"ሙሴም መልሶ እንዲህ አለ፦ እነሆ፣ አያምኑኝም ድምፄንም አይሰሙም፤ እግዚአብሔር አልተገለጠልህም ይላሉና።" (ዘጸ. 4:1)። እንደ ማረጋገጫ፣ ሁለት ምልክቶች ተሰጡት፦ ጌታ በትርህን በምድር ላይ ጣለው ብሎ አዘዘው፣ እናም እባብ ሆነ። እባቡን በጅራቱ በያዘው ጊዜ፣ በእጁ ውስጥ እንደገና በትር ሆነ። ከዚያም ጌታ እጁን በደረቱ ውስጥ እንዲያስገባና እንዲያወጣ ነገረው፣ በለምጽ ነጭ ሆነ። እጁን በደረቱ ውስጥ መልሶ ካስገባ በኋላ፣ ጌታ እንደተናገረው ንጹሕ ሆኖ ወጣ። ለተቺዎች ይህ አጠራጣሪ ጉዳይ ነበር፣ ወደ ጥንቆላ አቅጣጫ። እግዚአብሔር የሰዎችን ሐሳብና አመለካከት ይፈትናል። እግዚአብሔር በሚያዘውና በሚያደርገው ነገር የማይስናከሉ ብፁዓን ናቸው። ጌታ ለሙሴ እንዲህ አለ፦ <u>"…ባያምኑህ የፊተኛይቱን ምልክት ነገር ባይሰሙ፣ የሁለተኛይቱን ምልክት ነገር ያምኑታል</u>።" (ዘጸ. 4:8)።

መጽሐፍ ሁሉ በእግዚአብሔር እስትንፋስ ለትምህርታችን የተሰጠ ነው፣ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም እንዲሆን (2 ጢሞ. 3:14-17)። እግዚአብሔር "የነበርኩኝ" አይደለም፣ ነገር ግን ለዘላለም "እኔ ነኝ" ነዉ። እርሱ በዘመናችንም ታሪክ ይሠራል። ስለዚህ በእርግጥ ስለተፈጸመው ነገር ልንመሰክር እንችላለን። ዊሊያም ብራንሃምን ስጠቅስ፣ ይህን የማደርገው የእርሱ አገልግሎትም ከእግዚአብሔር የመዳን ዕቅድ ጋር እንደተገናኘ በጴጥሮስና በጳውሎስ ላይ እንደምጠቅሰው ሁሉ ነው። እርሱን ከሚክዱትም ሆነ ከሚያከብሩት ወገን አይደለሁም። እግዚአብሔር የሠራውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አነጻጽራለሁ እናም በዚህ መልኩ ማንም ሰው ሊቃወመኝ አይችልም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ትክክል ነው፣ እናም እርሱን የሚያምን ሁሉ ክርክሮችን አይሰማም፣

ምክንያቱም አንድ ዓላማ ብቻ ነው ያላቸው፡ እግዚአብሔር የሠራውን ለማጣጣል እና የራሳቸውን አመለካከት ለማጽደቅ። እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች የሚፈልጉት እግዚአብሔር በቃሉ መሠረት የሚያደርገውን ብቻ ነው፣ ምክንያቱም እነርሱ በእርሱ ዉስጥ ይካፈላሉ።

በጌታችን አገልግሎት ወቅት፣ የሃይማኖት መሪዎች ከዲያብሎስ ነው እናም በክፉ መንፈስ ተይዟል አሉ። በተመሳሳይ ጊዜ በሙሉ ልብ መዝሙሮቻቸውን እየዘመሩ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ይህ በዘመናችንም እየተደገመ ይመስላል። እኔ እንደ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ሌሎች ሐዋርያት በዘመናቸው እንዳደረጉት፣ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር የሠራውን በግል የማውቅና የማየት ልምድ ያለኝ ሰው እንደ መሆኔ ልመሰክር እችላለሁ።

በአዲስ ኪዳን መጀመሪያ ላይ የሰማይ መልእክተኞች ወደ ምድር እንደወረዱ በተለምዶ ይታወቃል። መልአክ ወደ ዘካርያስ መጣ (ሉቃስ 1:8-20)፣ መልአክ ወደ ማርያም መጣ (ሉቃስ 1:26-38)። የእግዚአብሔር ልጅ ሲወለድ፣ የሰማይ መዘምራን ወረዱ፣ ብርሃንም አካባቢውን ሁሉ አበራ፣ እናም መልአክ ማስታወቂያ ተናገረ (ሉቃስ 2:8-15)። መላእክት ኢየሱስን ያገለግሉ ነበር (ማቴ. 4:11)፣ መላእክት ስለ ትንሣኤው መሰከሩ (ማቴ. 28:1-10፣ ማር. 16:1-8፤ ሉቃስ 24:1-12፤ ዮሐ. 20:1-18)። መላእክት ጌታ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ተገለጡ፣ መመለሱን እየተናገሩ (ሐዋ. 1:10-11)። ብሉይና አዲስ ኪዳን የመላእክትን ዘገባዎች በብዛት ይዘዋል፣ እነዚህም <u>የሚያገለግሉ መናፍስት</u> ናቸው፣ ነገር ግን የተላኩት ድነትን ለሚወርሱት ብቻ ጥቅም ነበር (ዕብ. 1:14)። ሁሉም ሌሎች በምንም መልኩ አያምኑም፣ እግዚአብሔርም በዚህ ምክንያት መዘባበቻ መሆን አይፈልግም። በዘመናችን ለዘላለም ሕይወት የተሾሙ ሁሉ የሚከተለውን ዘገባ ያምናሉ።

እ.ኤ.አ. ግንቦት 7 ቀን 1946 ምሽት፣ የሰማይ መልአክ በዩኤስኤ  ግሪንስ ሚል ወደሚባል ትንሽ ስፍራ መጣ፣ ሰባኪውን ዊሊያም ብራንሃምን ለመጎብኘት፣ መለኮታዊ ተልእኮ  እያመጣለት። ዊሊያም ብራንሃም መጽሐፍ ቅዱሱን ለማንበብ በቂ ብርሃን ባለው ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ሳለ፣ ድንገት ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ብርሃን ክፍሉን ሞላው፣ የሰማይ መልአክ ወደ እሱ እየመጣ ነበር። እጅግ ፈርቶ ከመቀመጫው ተነሳ። የሰማይ መልአኩም፡- “አትፍራ። በስህተት የተረዳሃቸዉ መንገዶች እግዚአብሔር የአምላካዊ ፈውስ ስጦታን ለዓለም ሕዝቦች እንድትወስድ እንደላከህ ያመለክቱ ዘንድ እንደነበር ልነግርህ ከሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ፊት ተልኬአለሁ። እውነተኛ ከሆንህና ሰዎች እንዲያምኑህ ካደረግህ፣ ምንም ነገር በጸሎትህ ፊት አይቆምም፣ ካንሰር እንኳ...” መልአኩም አክሎም፡- “ሙሴ ሁለት ምልክቶች እንደተሰጠው አንተም ሁለት ምልክቶች ተሰጥተውሃል...” አለ።

የመጀመሪያው ምልክት፣ ጸሎት የሚፈልገውን ሰው ቀኝ እጅ በግራ እጁ መያዝ ነበረበት። በሽታው፣ ለምሳሌ ዕጢ፣ ካንሰር ወዘተ፣ በእጁ ጀርባ ላይ ይታያል፣ ለበሽተኛው እየታየ። ሰውየው በተፈወሰበት ቅጽበት፣ በሽታው ወዲያውኑ ከእጁ ይጠፋል። መልአኩም፡- “ካንሰር እንኳ በጸሎትህ ፊት ሊቆም አይችልም” በማለት አጽንኦት ሰጥቷል። እናም እንዲሁ ሆነ። አብዛኞቹ የተፈጸሙት ፈውሶች

የካንሰር ጉዳዮች ነበሩ። የሰማይ መልእክተኛዉም አክሎ፡- "የመጀመሪያውን ምልክት ማመን ካልቻሉ፣ ሁለተኛውን ያምናሉ..." ሁለተኛው የመለየትና የመገለጥ ስጦታ ነበር፣ በዚህም ምክንያት ሊጸልይለት ያለውን ሰው የሕይወቱን ዝርዝር ሁኔታዎች በራእይ ለእርሱ ይገለጥለታል እና እንዲያይ ይደረጋ.ል። <u>በዚህም በዚያው ቅጽበት በሽተኞች ጠንካራ እምነትን ተቀብለው ጌታ ራሱ እንደተገኘ ማረጋገጫ አግኝተዉ ፈውሳቸውን ተቀበሉ።</u> ከእነዚህም መካከል ሐኪሞች ተስፋ የቆረጡባቸው ብዙ የካንሰር ጉዳዮች ነበሩ።

ይህ ታላቅ መነቃቃት <u>የጌታችን አገልግሎት በጀመረበት ተመሳሳይ መንገድ ተጀመረ፡</u> አይነ ስዉራን ማየት ቻሉ፣ አንካሶች መሄድ ቻሉ፣ መስማት የተሳናቸዉ መስማት ቻሉ፣ እና ዲዳዎች መናገር ቻሉ። መልአኩም በዮሐ. 1 እና 4 ላይ የተከሰተውን ነገር ገለጸለት፣ የትንቢታዊው ስጦታ <u>"የመሲሑ ምልክ</u>ት" እንደነበረ በመግለጽ፣ በሰው ልጅ ዘመን እንደነበረው። ስለ ፊልጶስና ናትናኤል፣ ስለ እንድርያስና ጴጥሮስ፣ ስለ ሳምራዊቷ ሴት በያዕቆብ የውኃ ጉድጓድ ተናገረ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያገኛቸው፣ <u>ጌታ ኢየሱስ ለእያንዳንዳቸው ስለ ሕይወታቸው ሊያዉቅ የማይችለዉን ነገር ነገራቸው፡ ስሞች፣ ሁኔታዎችና ግንኙነቶች</u>። ባለፈው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ ክፍል በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይህንን የማይሳሳት አገልግሎት ተመልክተዋል፣ በዚህም እግዚአብሔር በዘመናችን አዲስ ጅማሬ አደረገ። በመፈወስ አገልግሎቶች ስብሰባዎች ላይ ያሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ የመጀመሪያዎቹ የተቀዱ መልእክቶች አሁንም ምስክር ናቸው፣ በዚህም ሁሉም የዚህን ዘገባ እውነተኑት እና የተከናወነውን ያልተለመደ አገልግሎት ማረጋገጥ ይችላሉ። በዚህም እግዚአብሔር ራሱ የመጨረሻውን መነቃቃትን ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ አመጣልን፣ እናም ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘመናት ተመለስን።

በኢየሱስ አገልግሎት እንደተከሰተው ሁሉ ነገሮች ተከሰቱ። የሰውነት ፈውስ ዋናው ጉዳይ አልነበረም፣ ትኩረቱ በነፍስ መዳን ላይ ነበር። የሰውነት ፈውስ ጥሩ ነው፣ ከሙታን መነሳት ደግሞ የተሻለ ነው፣ ነገር ግን የተፈወሱትና ከሞት የተነሱት በሆነ ጊዜ እንደገና ይታመሙና በማንኛውም ሁኔታ ይሞታሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር በሰው ውስጥ የሚሠራው ነገር ለዘላለም ይኖራል። ውጫዊው ማረጋገጫ ልቦችን ወደ እግዚአብሔር መንፈስ እንቅስቃሴ ለመክፈት እና ቃሉን ለመቀበል ይመራል።

ኢየሱስ ስብከቱን የጀመረው <u>"ዘመኑ ተፈጽሞአልና የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርቦአል</u>" (ማር. 1:15) በሚሉ ቃላት ነው። እርሱ አገልግሏልና አስተምሯል (ሐዋ. 1:1)። እግዚአብሔር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በጀመረው የድነትና የፈውስ መነቃቃትም እንዲሁ ነበር፣ ምክንያቱም ከድነት ዕቅድ ጋር በቀጥታ የተገናኘ አገልግሎት ነበር። <u>ዘመኑ እንደገና ተፈጽሞአል እናም ከተፈጥሮ በላይ የሆነው በምድር ላይ ከዚህ በፊት ሆኖ በማይታወቅ በብዛት ተከስቷል፣ ነገር ግን በእርግጥም በቅዱስ ጽሑፋዊ ምሳሌ።</u> ዋናው ዓላማው ሁሉን ስህተቶችን ሙሉ በሙሉ የማስተካከል፣ የአቅጣጫ ለውጥ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ከሆኑ ትምህርቶችና ልማዶች ሁሉ መውጣት

እንዲሁም በመጨረሻ ወደ መለኮታዊው መጀመሪያ የመመለስ ነው። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር በራሱ ተጎብኝታለች፣ እርሱም ትሑት ሰውን የሰዓቱን መልእክት ሊያመጣልን አዘዘ። የተገለጠውና ሕያው ቃሉ እንደገና የመጀመሪያው ዘር ሆነ። ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ማረጋገጫ የእግዚአብሔር ሥራ ነበር፣ **በሰው ልጅ** አገልግሎት እንደነበረው። ይህንን የሚንቅና አሁን የማያምን ሁሉ ያን ጊዜም አያምንም ነበር።

## በዘመናችን ያሉ ምስክሮች

የዚህ መጽሐፍ ደራሲ እንደመሆኔ መጠን ይህንን ልዩ አገልግሎት ከመጀመሪያው ደረጃ ጀምሮ የተመለከቱ ብዙ የጊዜዉ ምስክሮችን አውቃለሁ። አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ በዓመታት ዉስጥ በእኛ ትውልድ እግዚአብሔር ላደረገወ ምስክሮች ነበሩ። ከእነዚህም መካከል ሬቨረንድ ጎርደን ሊንሳይ፣ ዴማስ ሻካሪያን፣ ዴቪድ ዱፕሌሲስ እና ሌሎች ብዙ የሰሜን አሜሪካ ወንጌላውያን ይገኙበታል። ለብዙዎቹ ተርጓሚ ሆኜ አገልግያለሁ። በእርግጥም አሁንም በሕይወት ያሉ ብዙዎች ሊጠሩ ይችላሉ። ዓለም አቀፍ ዝና ያተረፉት ወንጌላዊ ሬቨረንድ ቲ. ኤል. ኦስቦርንን ምስክርነታቸዉን እንዲሰጡ እሳቸዉን ለመምረጥ ወስኛለሁ። እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 26፣ 1966፣ ዊሊያም ብራንሃም ወደ ጌታ ከሄደ በኋላ በተደረገው የመታሰቢያ አገልግሎት ላይ የተናገሩት የሚከተለው ነው።

**"ይህ የመጨረሻው ትውልድ ነበር። የሆነ ነገር መከሰት ነበረበት። ያለፉት ትውልዶች እንደሄዱት ሊሄድ አልቻለም። ይህ ነው! ስለዚህም፣ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ምሕረት፣ ከተራው ልክ ባሻገር በሆነ መንገድ በመርገጥ፣ በዚህ ሰዓት ይህን ነቢይ እንደገና ለመላክ አስቀድሞ ወስኖ ነበር።**

**አንዳንዶች እኔ የተቀደሰ ነገር አቃልላለሁ ወይም በዶክትሪን ተሳስቻለሁ ብለው ያስባሉ (እና በእውነትም ምንም አይደለም)፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንደገና በሰው ሥጋ መጣና፡- "እንደገና ማሳየት አለብኝ። እንደገና ማስታወስ አለብኝ። አንድ ጊዜ ተጨማሪ ማየት አለባቸው። አንድ ጊዜ ተጨማሪ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ማወቅ አለባቸው" አለ። <u>እናም ወርዶ ትንሽ ሰው፣ ነቢይ፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ከነቢይ በላይ የሆነ፣ የኢየሱስ ሰው በዚህ ጊዜ ላከ!</u>**

**ኤልያስ ያ አልነበረም። ይህ ካየነው በላይ ነው። ሙሴ ያ አልነበረም፣ ምክንያቱም እሱ በኖረበት የተለየ ሥርዓት ምክንያት፣ ያየነው ሊሆን አይችልም። ከዚያ በላይ! የኢየሱስ ሰው፣ በእግዚአብሔር የተሞላ ሰው፣ ነገር ግን ለትውልድ — ለዚህ ትውልድ ልዩ ምልክት ሆኖ የተላከ። ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ምልክት፣ ያልተለመደ ልክ።**

**<u>ለምን? በፊት ተደርጓል፣ ለምን እንደገና ይደረጋል? ይህንን የመጨረሻ ትውልድ ለማንቃት! አንድ ጊዜ ተጨማሪ ቀዳሚ ለመሆን፤ አንድ ጊዜ ተጨማሪ፣ የተመዘገበዉ ግልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ፣</u> ሰበብ እንደሌለ ለማረጋገጥ፣ እና እግዚአብሔር እንደገና እንዳሳየ ለማረጋገጥ፤ ስህተት ሊኖር እንደማይችል ለማረጋገጥ፣ እና እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል፣ ኢየሱስ ምን እንደነበረ፣ እና እግዚአብሔር በሥጋ ምን እንደሚሠራ እንደገና ለማስታወስ። ንጉሱን የመመለስ ኃላፊነት የተሰጠው**

ይህ ትውልድ ምን እንደሚሆን፣ ምን ሥራ እንደሚሠራ፣ እና አገልጋዩ ምን መሆን እንዳለበት ያለ ጥርጥር እንዲያውቅ። ስለዚህ የእኛ ተልዕኮ ምን እንደሆነ፣ ምስክርነታችን ምን እንደሆነ፣ እንዴት ልንሠራውና ልንፈጽመው እንደምንችል፣ ምን ማድረግ እንዳለብን፣ እና እንዴት እርምጃ መውሰድ እንዳለብን እናውቃለን። አንድ ጊዜ ተጨማሪ ያለ ሰበብ፣ ከልክ በላይ ለሁለተኛው ምጽአቱ ቀዳሚ ለመሆን።

ወንድም ብራንሃም ሲያገለግል ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁትና ያየሁት ምሽት፣ ድምፅ አልሰማሁም፣ ስለ እርሱ እንደተባለ አላውቅም ነበር፣ እናም ከሰማይ የመጣው ድምፅ እነዚህን ቃላት እንደተናገረ አላውቅም ነበር። ምንም አላውቅም ነበር። በእርሱ ከሚያምኑት አገልጋዮች መካከል ከማንም ጋር አልነበርኩም፣ ምክንያቱም ከእኔ ጋር የነበሩት አብዛኞቹ በእርሱ አያምኑም ነበር። ነገር ግን እንደ ድምፅ፣ ሆኖም ግን እንደ ድምፅ ሳይሆን፣ ሰማሁት። አወቅሁት። ወደ እኔ መጣ! "መጥምቁ ዮሐንስ ለመጀመሪያው ምጽአቱ ቀዳሚ ሆኖ እንደተላከ፣ ዊሊያም ብራንሃም ለሁለተኛው ምጽአቱ ቀዳሚ ሆኖ ተልኳል"። ይህንን አውቅ ነበር።

ልምድ የሌለኝ ወጣት ሰባኪ ነበርኩ። የነገረ መለኮት ምሁር አልነበርኩም። ቅዱሳት መጻሕፍትን አላውቅም ነበር። ለምን ይህን እንዳወቅሁ አላውቅም፤ ግን አውቅ ነበር። "እግዚአብሔር ይመስገን፣ መንገዴን አቋርጧል። እግዚአብሔር ይመስገን፣ ተማርኩ። እግዚአብሔር ይመስገን፣ ተረዳሁ" አልኩኝ። አሥር ምሽቶች አልወሰደም፣ አንድ ምሽት ብቻ።

ይህ ትውልድ ምልክት ይፈልጋል፣ ሌላ ምልክት፣ ሌላ እና ሌላ! አንድ በቂ ነው! አንዱ ብዙ ነዉ !

እግዚአብሔር ፈቅዶ፣ የቃል ኪዳኑ አለመለወጥ ዕውቀት እንዳንሳሳት ለማረጋገጥ፣ በሃያኛው ክፍለ ዘመን፣ እርሱን መልሶ የማምጣት ዕድል የተሰጠው ትውልድ፣ እንደገና አደረገው። ይህ ትውልድ ማወቅ አለበት። ይህ ትውልድ ያለ ሰበብ መሆን አለበት፣ ምክንያቱም ለዚህ ትውልድ ይህን የማድረግ ተግባር ተሰጥቷል። ስለዚህም፣ እርሱ ትኩረት ለመሳብ እና ይህ የጠፋ ትውልድ ወደ ላይ እንዲመለከት፣ እንዲያሰላስል፣ እንዲፈልግና እንዲያስብ ከተፈጥሮ በላይ በሆኑ ምልክቶች የተከበበ ልዩ የሰው ዕቃን ላከ።

ስለዚህ፣ ሲወለድ የታየው የብርሃን ሃሎ፣ ኮከቡ፣ መልአኩ፣ መለየቱ፣ ስጦታዎቹ–እነዚህ ሁሉ ለዚያ ዓላማ ተሰጥተዋል። ለምን? እግዚአብሔርን እንደገና ሊያሳየን! ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መልክ ሲመጣ ያሳየንን ለመድገም፤ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስታወስ። እንደ ኢየሱስ፣ ወንድም ብራንሃም እውነተኛው መሲሕ እንደመጣ ሰዎች ያመኑበትን ነገር እንደገና አሳየ።

እርሱ ባለ ራእይ ነበር፤ ያይ ነበር። በሁለቱም ዓለማት፣ በሚታየውና በማይታየው ዓለም በአንድ ጊዜ ይኖር ነበር፣ እናም ሁለቱንም በተግባር ሁልጊዜ ይሻገር ነበር። ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ "አባቴ እስከ አሁን ይሠራል፣ እኔም እሠራለሁ። አብ ሲያደርግ ያየዉን እንጅ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም።"

አሁን ወንድም ብራንሃም በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጥቶ በትክክል ተመሳሳይ ነገር ይሠራል። እግዚአብሔር በሥጋ፣ እንደገና መንገዳችንን ሲያቋርጥ፤ እና ብዙዎች አላወቁም። እግዚብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ብለው በሚጠሩት አካል ውስጥ መንገዳቸውን ሲያቋርጥ እዚህ ቢኖሩ ኖሮ አያውቁትም ነበር! ሰዎች አልተለወጡም። ያኔ የጠየቁት አሁንም ይጠይቃሉ። ያኔ ያላመኑት አሁንም አያምኑም። "አብ ሲያደርግ ያየዉን እንጅ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም ፤ አብ የሚሠራውን ሁሉ ወልድ ደግሞ እንዲሁ ያደርጋልና፤ አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገዉን ሁሉ ያሳየዋል።"

ተአምራቶች ከመከሰታቸው በፊት ያያቸው ነበር። ኢየሱስ ወደ ኩሬው 38 ጊዜ የሄደውን፣ ግን ወደ ውኃው መግባት ያልቻለውን ሽባ ሰው አይቶት ነበር። ኢየሱስ ይህን ሁሉ ከመግባቱ በፊት አይቶ ነበር፣ ከዚያም ቆሞ ተነሥቶ እንዲሄድ ነገረው።

አላዛር ከመነሣቱ በፊት አይቶት ነበር። ከአብ ጋር አስቀድሞ ተስማምቶ ነበር። አስቀድሞ ተለማምዶት ነበር። ፊልጶስ ናትናኤልን ከመጥራቱ በፊት፣ በበለስ ዛፍ ሥር ሳለ፣ ከመለወጣቸው በፊት አይቶት ነበር።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በጎዳናዎች እንዴት እንደሚሄዱ እና ውኃ የሞላበት ማሰሮ የያዘ ሰው እንደሚያገኙ በትክክል ተነበየ። እርሱን እንዲከተሉ እና በዚያ የታሰረች አህያ እንደሚያገኙ፣ እናም እንዲያመጡለትም ነገራቸው። ይህን ሁሉ ከመከሰቱ በፊት አይቶት ነበር።

<u>ይህ የዊሊያም ብራንሃም ሕይወት ነበር ፤በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳነበብነው በትክክል ነበር</u>። ከዚያም ሰዎች ወንድም ብራንሃም ይህን ሲናገር ይሰማሉ፣ እናም "ዛሬ ስህተት ነው" ይላሉ፤ ግን ስህተት አይደለም። ዛሬ አያምኑም፤ ያኔም አያምኑም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እንደገና መጥቷል፣ መንገዳችንን እንደገና አቋርጧል፣ እናም አምላክ-ሰዉ ምን እንደሚመስል፣ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል፣ በሥጋ ምን እንደሚመስል፣ እና አዲሱ ፍጥረት ምን እንደሚመስል እንደገና አሳይቶናል።

ይህ ምን እንደሆነ ታያለህ? ይህ የአዲሱ ፍጥረት ሥራ ነው። እርሱ መለየት የሚችል ነበር፣ ኢየሱስ በጉድጓዱ ላይ ያለችውን ሴትና ሕይወቷን እንደለየው። እና ስንት ጊዜ ተቀምጣችሁ ተደንቃችኋል? ኢየሱስ ያደረጋቸውን ጥቂት ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ስናነብ ካመንን፣ ሌሊት ከሌሊት ተቀምጠን እነዚህን ነገሮች ሲደጋገሙ፣ አንድ ጊዜ ሳይሆን፣ በደርዘን ሚቆጠሩ ጊዜያት ኢየሱስ ባደረገው ፍጹም መንገድ ስናይ ያለ ሰበብ እንዴት ልንሆን እንችላለን? በትክክል! ይህን አይቶ ያላመነ ሰው እንዴት ሊኖር እንደሚችል ለእኔ ከአቅም በላይ ነው።

ወንድም ብራንሃም በሽታዎችን ያውቅ ነበር። ማንም ሳይነግረው በሁሉም ቦታ ያውቃቸው ነበር። ያው አምላክ ሁሉንም ነገር ያውቃል። እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ሆኖ ዕውቀቱን ያሳያል–ምን

**እንደሆነ፣ የተፈጥሮን መሰናክሎች ሁሉ እንዴት እንደሚሻገር፣ እና ምንም ነገር ለእርሱ የማይቻል እንደሌለ።**

**ከእርሱ በጎነት እንደወጣ ያውቅ ነበር። ስንት ሰው ተቀምጦ ወንድም ብራንሃም ሲዞርና "እዚያ አለች"፣ "እዚያ አለ" ሲል ተመልክቷል? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያቺ ትንሽ ሴት ይህን ያየችው። በእርግጥ ከጊዜ በኋላ ሁሉም ስለ ጉዳዩ ሰሙ፣ እናም ሁሉም አገኙት፤ ነገር ግን አንድ ጉዳይ ብቻ በዝርዝር ተቀምጧል። ነገር ግን ዓይኖቼ በደርዘን የሚቆጠሩ ጉዳዮችን አይተዋል፣ እና አንዳንዶቻችሁ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጉዳዮችን አይታችኋል! እንዴት አላምንም?**

**ይህ የአስተምሮት መሰናክሎችን አያመጣብኝም። ይህ በቀላሉ ያኔ የተከሰተው ዛሬም ተመሳሳይ እንደሆነ ይነግረኛል። አምላኬ አልተለወጠም።**

**በእነዚህ ምልክቶች በአምላክ መንፈስ ኃይል በታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች አማካይነት አሕዛብ በቃልና በሥራ ታዛዦች እንደሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመስክሯል። ብዙዎች ድንቅ ሥራዎችን አይተው ኃጢአታቸውን ንስሐ ሲገቡ፣ ለድነት ሲይጣሩ፣ እና የዘላለም ሕይወትን ሲቀበሉ፣ እዚህ ብቻ ሳይሆን በውጭም በአንድ ቀን እስከ 30,000 የሚደርሱ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ለመቀበል ሲቆሙ፣ እግዚአብሔር በሰው ሥጋ መንገዳቸውን አቋርጦ ራሱን ገለጠ?**

**ይህ ምስጢር ነው? ይህ ምስጢር አይደለም፣ ይህ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ነው! ይህ በትምህርት ለመከራከር የሚያቻል ጉዳይ ነው? ይህ በዘመናችን በሥጋ ለተገለጠው አምላካችን ክብር መስጠት ያለብን ጉዳይ ነው። እርሱ በሁላችንም ውስጥ በሥጋ መጥቷል፣ ነገር ግን ለዚህ ትውልድ የእርሱ ነቢይ በሆነው በዚህ ሰው ውስጥ በልዩ ሁኔታ መጥቷል፣ ምክንያቱም እርሱ ዓለምን እንደገና በምልክት ትኩረት እንዲስብ በሚያስችሉ እነዚህ ከተፈጥሮ በላይ በሆኑ ምልክቶች ተከቦአልና።"** እዚህ ላይ "የመጀመሪያው የመነቃቃት ማዕበል" ታላቅ ወንጌላዊ ተብሎ በዓለም ዙሪያ በሚከበረው ሬቨረንድ ቲ. ኤል. ኦስቦርን ምስክርነት እንጨርሳለን።

የእግዚአብሔርን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሥራ ተጽዕኖ በቀጥታ ከተመለከቱት የመጀመሪያዎቹ አንዱ ለሆኑት ለሬቨረንድ ኦስቦርን እጅግ በጣም ጥሩ ምስክርነት በእርግጥም አመስጋኞች ነን። እኔም የዚህ ልዩ አገልግሎት ምስክር በመሆን ተመሳሳይ ዕድል ተሰጥቶኝ ነበር። ከ1955 ዓ.ም. ጀምሮ ወንድም ብራንሃም ወደ አውሮፓ መጥቶ በካርልስሩህ፣ ጀርመን እና በዙሪክ፣ ስዊዘርላንድ በሰበከበት ጊዜ፣ እስከ 1965 ዓ.ም. ወደ ጌታ እስከተወሰደበት ጊዜ ድረስ፣ በበርካታ የብሔራዊና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎቹ ላይ ተካፍያለሁ። ከስብከቱ በኋላ፣ ወንድም ብራንሃም መጀመሪያ ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉትን ጸለየላቸው፣ ከዚያም ለታመሙት ጸለየ። ሬቨረንድ ቲ. ኤል. ኦስቦርን እንደመሰከሩት ነበር። የእግዚአብሔር ሰው የታመሙትን ምን ዓይነት በሽታ እንዳለባቸው ወይም ለምን መጸለይ እንዳለበት አልጠየቀም። ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ብርሃን በሚጸልይለት ሰው ላይ ወረደ እናም በራእይ ታየው፣ **በሰው ልጅ** ትንቢታዊ አገልግሎት እንደነበረው ሁሉ (ዮሐ.

5:19-20)። እርሱ በጸሎት መስመር ውስጥ ላሉት በምን እንደሚሰቃዩ እና የሕይወታቸውን ዝርዝር ጉዳዮችን ነገራቸው። ብዙ ጊዜ በራእይ የሰውየውን ስም፣ የመጡበትን ከተማ፣ የሚኖሩበትን ጎዳና እና እንዲያውም የቤቱን ቁጥር ያይ ነበር። ስለዚህም "ጌታ እንዲህ ይላል" ብሎ በእውነት ሊናገር ይችላል። እግዚአብሔር ብቻ ነው ሁሉንም ሰው የሚያውቀው። ዊሊያም ብራንሃም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው ባለ ራእይ ነበር።

ይህ አገልግሎት በምድር ላይ በጣም ሩቅ  ጥግ የሆነ ቦታ ላይ አልተከሰተም፣ በዓለም ዙሪያ ባሉ በተለያዩ አገሮች ውስጥ በትላልቅ ስብሰባዎች ላይ ተፈጸመ። ወንድም ብራንሃም ቋንቋውን በማይናገርበት ቦታም እንኳ፣ ተርጓሚ በመጠቀም፣ ስለ እያንዳንዱ ሰው የተገለጠው ነገር ሁሉ ትክክል ነበር እና እውነት ሆኖ ተረጋገጠ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በዓለም ዙሪያ የዓይንና የጆሮ ምስክሮች ሆኑ። በእውነትም፣ በዘመናችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በዚያው ሰው አማካይነት <u>የመሲሑን ተመሳሳይ ምልክት</u> ይዞ ገለጠ። ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር እንደነበረው ሁሉ፣ እኛ አንዴ እንደገና ከአንድ ሰው ጋር ያለ ጉዳይ እየተመለከትን ሳይሆን፣ <u>በእግዚአብሔር ከተሾመ የተስፋ አገልግሎት ጋር</u> ነው እየተነጋገርን ያለነው። ስለዚህ ጥያቄው "ብራንሃምን በተመለከተ ምን አቋም አለን?" ሳይሆን፣ "ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን ነገር ለመፈጸም ተፈጥሮአዊ ዕቃን በተጠቀመው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንቆማለን?" የሚለው ነው። <u>አዲስ ኪዳን የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት በተሰጠ የተስፋ አገልግሎት ተጀመረ፣ እናም አዲስ ኪዳን ለሙሽራይቱ ሁሉንም ነገር በሚመልስ የተስፋ አገልግሎት ያበቃል።</u>

## ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ማረጋገጫ ውሳኔን ይጠይቃል

ዊሊያም ብራንሃም በዚህ የመጨረሻዉ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የእግዚአብሔር ነቢይና የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንዲሆን ከልደቱ ጀምሮ ከተሾመ ይህ እዉነት ከሆነና የሚሰራ ከሆነ፣ ያ ሁሉን ቻይ የሆነው የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ውሳኔ ነበር፣ ባለፉት ዘመናት ከሁሉም አገልጋዮቹ ጋር እንደነበረው (ኤር. 1:5) ።

እውነት ከሆነ–እውነትም ነው–እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 6 ቀን 1909 ጠዋት 5:00 ላይ ከተወለደ ከሁለት ሰዓት በኋላ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ብርሃን በተከፈተ መስኮት በኩል መጥቶ፣ በሕፃኑ ላይ ብቻ እየተንሳፈፈ፣ ለወላጆቹና አዋላጅ  ለነበረችዉ ለአያቱ እየታየ ፣ እንዲሁ ማለፍ እንችላለን?

እውነት ከሆነ፣ ወጣት ቢሊ በ7 ዓመቱ ከፍ ካለው የአኻያ ዛፍ አቅጣጫ በሚመጣ ኃያል ድምፅ፦ <u>"መቸም ቢሆን እንዳትጠጣ ወይም እንዳታጨስ ወይም በማነኛዉም መንገድ ሰውነትህን እንዳታረክስ፣ ምክንያቱም ስታድግ የምትሰራዉ ሥራ አለ"</u> ከተባለ፣ እንዲሁ ማለፍ እንችላለን?

እውነት ከሆነ፣ እግዚአብሔር ከልጅነቱ ጀምሮ ራእዮችን አሳይቶታል፣ እነዚህም 100% ትክክል መሆናቸው ከተረጋገጠ፣ ያ በእርግጥ ሰውየዉ ሳይሆን፣ በሰው ውስጥ ያለ እግዚአብሔር ነው፣ ሬቨረንድ ቲ. ኤል. ኦስቦርን እንደተናገሩት።

ከክርስቶስ ሁለተኛ ምጽአት በፊት እንደሚመጣ ቃል በተገባለት በተገለጠው ቃል መልእክት በእዉነት የተላከ ከሆነ ፣ ያን ጊዜ ጆሮ ያለው ሁሉ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን መስማትና መቀበል አለበት።

ሬቨረንድ ጎርደን ሊንድሳይ በመጽሐፋቸው ያሰፈሩት ነገርም እውነት ነው። እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 24፣ 1950፣ በሂዩስተን ኮሊሲየም፣ ቴክሳስ፣ ወደ 8,000 የሚጠጉ ሰዎች በተገኙበት ስብሰባ ላይ ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ብርሃን ወረደ። ከተገኙት መካከል አንዳንዶቹ ብርሃኑ በዊሊያም ብራንሃም ራስ ላይ ሲንሳፈፈ እንደተመለከቱ ነገሩት። እግዚአብሔር ለባሪያዉና ለነቢዩ የመሰክረለት እርሱ ነበር። ይህ ደግሞ በሬቨረንድ ደብሊው ኢ. ቤስት፣ በዘመናችን መለኮታዊ ፈውስን በግልጽ የካደው፣ እና በዊሊያም ብራንሃም የሥራ ባልደረባ በሬቨረንድ ኤፍ. ኤፍ. ቦስዎርዝ፣ ድነትና ፈውስ ሁለቱም የአንድ ቤዛነት ክፍል ናቸው ብሎ ባረጋገጠው መካከል በአደባባይ ከተደረገዉ ክርክር ቀደም ብሎ ነበር። በተጨማሪም ሁለት ወሳኝ ፎቶግራፍ አንሺዎች፣ ሚስተር ጄምስ አየርስ እና ሚስተር ቴድ ኪፐርማን ተገኝተው ነበር፣ እነዚህም በሬቨረንድ ቤስት ትዕዛዝ ፎቶግራፎችን ማንሳት ነበረባቸው። ፊልሞቹን ካሳደጉ በኋላ፣ አንድም ሥዕል አልወጣም፣ ዊሊያም ብራንሃም ወደ መድረክ ሲመጣ ሚስተር ጄ. አየርስ ያነሳው ሥዕል ብቻ ነበር። የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ አለ፦ <u>"እኔ እዚህ ያለሁት እራሴን ለመከላከል አይድለም፣ ያዘዘኝና የላከኝ ጌታ ኢየሱስ ይከላከልልኛል"</u>።" ያ ፎቶግራፉ የተነሳበት ጊዜ ነበር። ነጌቲቮቹ በጄ. አየርስ በግል በዱግላስ ስቱዲዮ በሂዩስተን ተዘጋጁ፣ እና ትክክለኝነታቸው በጆርጅ ጄ. ሌሲ፣ የአጠያያቂ ሰነዶች ፈታሽ ተረጋገጠ። እኛ በመጨረሻ እግዚአብሔር በሠራው ነገር እየተነጋገርን አይደለምን? እኔ፣ የዚህ ብሮሹር ደራሲ፣ በታኅሣሥ 1969 በዋሽንግተን ዲ.ሲ. በሚገኘው የስነ ጥበብ አዳራሽ ውስጥ ብርሃን ያለበትን ዓምድ የያዘውን ሥዕል አይቻለሁ። ስለዚህም ለሕዝብ ተደራሽ እንደሆነ አውቃለሁ። ሥዕሉን ያሳየኝ ሠራተኛ ትርጉሙን አያውቅም ነበር፣ ምክንያቱም ምንም መግለጫ አልተሰጠም ነበር። ሐዘን ተሰማኝና በውስጤ አሰብኩ፦ "የእግዚአብሔርን ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ድርጊቶችንና ዓላማቸውን ማን ያስተውላል?" ጌታ ራሱ ዛሬም ያው እንደሆነ አላረጋገጠምን፣ የእስራኤልን ልጆች 40 ዓመታት በእሳትና በብርሃን ዓምድ የመራው (ዘጸ. 13:21-22፤ ነህ. 9:12-20)? ጳውሎስን ወደ ደማስቆ በሚወስደው መንገድ ላይ ከቀትር ፀሐይ የበለጠ ብርሃን ባለው ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ብርሃን የተገናኘው እና የታወቀውን ተልእኮ የሰጠው እርሱ አይደለምን (ሐዋ. 9)?

እዉነት ከሆነ - እዉነትም ነዉ. እ.ኤ.አ. ፌብሩዋሪ 28 ቀን 1963፣ በዓለታማዋ አሪዞና በፀሐይ መጥለቂያ ተራራ ላይ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ደመና እንደወረደ፣ በውስጡም ሰባት መላእክት–ኪሩቤል–እንደተሸፈኑ፣ ለዊሊያም ብራንሃም በታኅሣሥ 22 ቀን 1962 በራእይ እንደታየው፣ ያ

የተከሰተው የመላዉ አለም ትኩረትን እግዚአብሔር  እየሰራ ወደ ነበረዉ ለመሳብ ነበር። በሰማያዊው ሰማይ ላይ ቀለም ያለው ደመና በመጠን፣ ከፍታ፣ ቅርፅ እና ቀለም እጅግ በጣም ያልተለመደ በመሆኑ፣ ብዙ ተመልካቾች ፎቶግራፉ አንስተውታል። የሜትሮሎጂ ባለሙያው፣ ዶ/ር ጀምስ ኢ. ማክዶናልድ ከቱክሰን "የከባቢ አየር ፊዚክስ ተቋም"፣ የክስተቱን ፎቶግራፎች መርምረው ሳይንሳዊ አመክንዮአዊ ማብራሪያ አላገኙም። በሪፖርቱ መሠረት፣ ምስጢራዊው ደመና ከፀሐይ መጥለቂያ በኋላ 28 ደቂቃዎች በትክክል ዊሊያም ብራንሃም ከነበረበት ቦታ በላይ በርቶ ነበር።

የሳይንስ መጽሔት፣ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 19 ቀን 1963 እትም እና የላይፍ መጽሔት እ.ኤ.አ. ግንቦት 17 ቀን 1963 እትም፣ ሁለቱም በቢሮዬ ውስጥ አሉ፣ በዘገባቸዉ ጉዳዩን ሽፍን  ሰጥተዉት ነበር። አንድ ርዕስ እንዲህ ይነበባል፦ "...እናም የምሥጢር ከፍ ያለ ደመና ቀለበት"። ለማያምኑት በሰማይ ላይ ምስጢራዊ ቀለበት ነበር፤ ለእውነተኛ አማኞች ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ምልክት ነበር፣ የቤተልሔምን አካባቢ በሙሉ ካበራው ከተፈጥሮ በላይ ከሆነው ብርሃን (ሉቃስ 2) ጋር ሊወዳደር ይችላል። ኢየሱስም ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ደመና ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ (ሐዋ. 1:9)። ሲመለስም ንጉስ ሆኖ ሲመጣ፣ በዚያው ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ደመና (ማቴ. 24:30፤ ሉቃስ 21:27፤ ራእይ 1:7-8) ይሆናል፣ ያን ጊዜም ዓይን ሁሉ ያየዋል። እግዚአብሔር በእርግጥ እየተጫወተ አይደለም። እኛ አሁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እየኖርን ነው! ስለዚህ እግዚአብሔር ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ ሲሠራ እንግዳ ሆኖ ሊታየን አይገባም። እግዚአብሔር ባለፉት ጊዜያት ስላደረጋቸው ነገሮች መሰበክ፣ እርሱ በዘመናችን የሠራውን እና ዛሬም እየሰራ ያለዉን ችላ ብንል ለምን ዓላማ ያገለግላል? እርሱ የትላንት አምላክ ነዉ ፣ "የነበርኩ" ነው ወይስ እርሱ ዛሬም ለዘላለምም ያው "እኔ ነኝ" ነው?

እውነት ከሆነ–እውነትም ነው–ወንድም ብራንሃም ይህ ደመና ሲወርድ በዚያ ተራራ ላይ እንደነበረ፣ በውስጡም ሰባት መላእክት በፒራሚድ መልክ እንደተገለጡ፣ እናም በሰባተኛው መልአክ "የሰባቱን ማኅተሞች የምትከፍትበት ጊዜ ደርሷልና  ወደ መጣህበት  ጀፈርሰንቪል ተመለስ" ከተባለ፣ ያ ለእኛ ታላቅ ጠቀሜታ ሊኖረው ይገባል። እ.ኤ.አ ከማርች 17 እስከ 24፣ 1963፣ ዊሊያም ብራንሃም በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ሰባቱ ማኅተሞች ተናገረ። ስለ እነዚህ ነገሮች የሰሜን አሜሪካ ወንጌላውያን፣ ኦራል ሮበርትስ እና ቲ.ኤል. ኦስቦርን እና ሌሎች "የመጀመሪያው ማዕበል" ያውቁ ነበር፣ ነገር ግን ከሕዝብ ደበቁት እና በጭራሽ አልጠቀሱትም። እግዚአብሔር የሚናገረውና የሚያደርገው ነገር ከፕሮግራሞቻቸው ጋር የሚስማማ አይመስልም፣ ምንም እንኳን ያልተለመደውን ተልእኮና አገልግሎት ቢያውቁም እንኳ። ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ብርሃን ዓይኖቻቸውን አሳወራቸው፣ ምክንያቱም እየተቃወሙት ስለነበር? በብርሃን ውስጥ መሄድ አለብን፣ ያኔ ብቻ ነው ቃሉ ለመንገዳችን ብርሃን የሚሆነው።

አሁን የምንኖረው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይም በራእይ መጽሐፍ የተጻፉ ነገሮች ፍጻሜያቸውን በሚያገኙበት ዘመን ነው። የይሁዳ  አንበሳ አሸንፏል፣ በጉም መጽሐፉን ወስዶ

ማኅተሞቹን ከፍቷል። መጽሐፉ ለዘላለም የታተመ እንዲሆን አልተፈለገም፣ እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ብቻ ነበር (ዳን. 12:4+9)። አሁን የምንኖረው በዚያ ዘመን ነው። ዘመኑ በተፈጸመ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በቃሉ የተደበቀውን ሁሉ ገለጠ። ይህ ለሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያን ሕያው እውነት ነው። እግዚአብሔር ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን አድርጓል እናም ሕዝቡ ስለ ጉዳዩ ሊነገራቸው ይገባል።

እ.ኤ.አ. በ1946 ዓለም ሌሎች ወንጌላውያንን አላውቅም ነበር። በሚቀጥሉት ዓመታት፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰባኪዎች በብራንሃም ስብሰባ ላይ ተመስጠው ነበር፣ የእግዚአብሔርን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሥራ በዓይናቸው ሲያዩ። እንደ ኦራል ሮበርትስ፣ ቲ. ኤል. ኦስቦርን፣ ቶሚ ሂክስ፣ ሞሪስ ሴሩሎ እና ሌሎች ብዙዎች ከእነርሱ መካከል ነበሩ። በ1950፣ ሬቨረንድ ጎርደን ሊንሳይ "ዊሊያም ብራንሃም—ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው" የሚል መጽሐፍ አሳተመ። እርሱ በ1946 እስከ 1950 መጀመሪያ ድረስ በተለያዩ አገሮች ውስጥ ስለተካሄዱት ያልተለመዱ ስብሰባዎች ጽፏል። ለበርካታ ዓመታት፣ ያው ደራሲ "የፈውስ ድምፅ" በሚለው ጽሑፉ፣ እና ከጊዜ በኋላ "ክርስቶስ ለሐገራት"፣ በዚህ ያልተለመደ አገልግሎት አማካይነት ስለተከሰቱት ነገሮች ለአንባቢዎች አሳውቋል፤ ሌሎች አሳታሚዎችም ተመሳሳይ ነገር አደረጉ። ነገር ግን እስከዚህ ቀን ድረስ፣ ከዚህ አገልግሎት ጋር የተገናኘውን እውነተኛ ዓላማ ማንም የሚጠይቅ አይመስልም። ነገር ግን ያ የእኛ ጉዳይ መሆን አለበት። ይህ ሁሉ ስለዚያ ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ሁሉም ወንጌላውያን በድሮዉ ክርስትናቸው መቆየት እና በመለኮታዊ ፈውስ ላይ ብቻ ማተኮር ይመርጣሉ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ስብከት ላይ አይደለም። በዓይናቸው ያዩት ታላላቅ ነገሮች ቢኖሩም እንኳ፣ እግዚአብሔር በቃሉ መሠረት በሕዝቡ መካከል በአሁኑ ጊዜ የሚሠራውን መለኮታዊ ዓላማ አይገነዘቡም።

ወንጌላውያን፣ በተለይም "የመጀመሪያው ማዕበል" (1946-1965)፣ የእግዚአብሔርን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሥራ ሲያዩ መነቃቃት ያገኙት፣ ታላቅ ኃላፊነት ወስደዋል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በዘመናችን በእርግጥ የሠራውን ከሕዝብ ደበቁት። ጉዳዩ ሰው ሳይሆን፣ በሉዓላዊነቱ ተልእኮውን የሰጠ እና ነቢይ-መልእክተኛውን የላከው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን መገንዘብ አለብን። ከተፈጥሮ በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሥራ ነው—አንድ ሰው ሊሠራው የሚችለው ነገር አይደለም—የሰዎችን ትኩረት ወደ እርሱ ሊናገረው ወዳለው ነገር ለመሳብ ነው።ጌታችን በዮሐ. 14:12 ላይ የተናገረው ተፈጽሟል፦ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ እርሱ ደግሞ ይሠራል፣ ከዚህም የሚበልጥ ሥራ ይሠራል..."

## ምልክቶች ወደ ግብ ያመለክታሉ

አሁን ትኩረቱ በንጹሁ የእግዚአብሔር መልእክት፣ በዘለአለማዊው ወንጌል ላይ ነው። ሙሴ ማረጋገጫ የሆኑ ምልክቶች ብቻ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለእስራኤል "ሕዝቤ ያገለግለኝ ዘንድ ፤ ህዝቤን ልቀቅ!" የሚል የእግዚአብሔር መልእክት ነበረው፣ እናም ከግብፅ የመውጣት ተግባር ተከናወነ። መጥምቁ ዮሐንስ የሙሽራው ወዳጅ እንደመሆኑ መጠን ሙሽራይቱን ለመጥራት

መልእክት ነበረው (ዮሐ. 3:28-36)። ሐዋርያው ጴጥሮስ እውነተኛው መልእክት ነበረው፣ ሐዋርያው ጳውሎስም እንዲሁ። ጳውሎስ ራሱን በክርስቶስ ስም መልእክተኛ ብሎ ጠርቷል። "እኛ የክርስቶስ አምባሳደሮች ነን" ብሏል። ዊልያም ብራንሃም እንደዚያ አይነት ቀጥተኛ አምባሳደር – ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው – ነበር። በምስክርነቱ፣ ሬቨረንድ ቲ. ኤል. ኦስቦርን አገልግሎቱን ከሙሴ ወይም ከኤልያስ አገልግሎት የላቀ አድርጎ ገምቶታል። በመጀመሪያ፣ ሌሎች ዓለም አቀፍ ዝነኛ ወንጌላውያን ሁሉ እንደዚሁ አደረጉ። በትምህርታቸዉ ስለጸኑ ነዉ ፤ በእግዚአብሔር ቃል ከተመሰረተዉ  አዋጅ ጋር መስማማት ያልቻሉት እና እራሰቸዉን ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ እያገለሉ የሄዱት? በሕዝቡ ፊት አጣጣሉትና ይልቁንም ስለ እርሱ ልዩ ልዩ ነገር ማዉራት ጀመሩ ፤በተለይ ወደ ጌታ ከተወሰደ በኋላ። እናም ይህ ልዩ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ማረጋገጫ ቢኖርም፣ እስከ ዛሬም ድረስ የሚያምኑበት! በእግዚአብሔር ብቻ ሊከናወን እንደሚችል ያውቃሉ፣ ነገር ግን በተዛባው ባህላዊ ክርስትና ትምህርቶቻቸዉ ውስጥ ቀሩ።

ታዲያ የመጨረሻው ዘመን ላይ መንገድ ሊያሳየን የሚገባው ትክክለኛው የመጀመሪያ መልእክት ምንድን ነው? በእኛ ትውልድ ሌላ ሰው እንዲመጣ መጠበቅ አለብን? በእግዚአብሔር ቀጥተኛ ትዕዛዝ በክርስቶስ ስም እንዲናገር በመለኮት የተጠራ እና የተላከ የተላከበትን የዚያን ቀን፤ቦታ እና ጊዜ የሚያረጋግጥ ሌላ ሰዉ አለ? አይ፣ የለም፣ አለበለዚያ እንሰማ ነበር። ከእግዚአብሔር በቀጥታ ከተላከው ሰው አፍ ብቻ እውነተኛው፣ ያልተበላሸው የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ወጣ።

በታህሳስ 1965፣ ዊልያም ብራንሃም ወደ ክብር ሲወሰድ፣ ለእኛ የእግዚአብሔርን መልእክት፣ ከመጀመሪያው እስከ ራዕይ ድረስ የተገለጠውን የቃሉን ሚስጥር ትቶልን ሄደ። የቃሉ የተደበቁ ሚስጥራት ሁሉ ተገለጡ። ዓለም አቀፍ ዝነኛ ወንጌላውያን በፈውስ አገልግሎት ተደስተው ነበር፣ ነገር ግን የቃሉ መልእክት የተላከዉ ሁሉንም ነገር ወደ ትክክለኛ ቦታዉ ለመመለስ እና ሙሉ በሙሉ ወደ ነበረበት ለመመለስ መሆኑን አልተረዱም ነበር ። አሁን ስለ "ሦስተኛው የመነቃቃት ማዕበል" እየተነገረን ነው፣ ነገር ግን መለኮታዊው ዓላማ የትም ቦታ ግልጽ አልሆነም። እያንዳንዱ ወንጌላዊ እና ካሪዝማቲክ ተናጋሪ የየራሱን ትምህርት የሚያቀርበው፣ በሚኖርበት ቤተ እምነት መሠረት አይደለምን? አንዳንዶች ሰዓቱን ተጠቅመው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የራሳቸውን ሚሊዮን እና ቢሊዮን ዶላር መንግስታት አልገነቡም? ግን ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን የት እና እንዴት ይገነባል? በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶቻቸው፣ ሰባኪ ሴሚናሪዎቻቸው እና እንዲያውም ዩኒቨርሲቲዎቻቸው ስኬታማ አይድሉምን? ሁሉም የየራሳቸውን ዓለም አቀፍ አውታረ መረብ እየገነቡ ፕሮግራሞቻቸውን አያስተዋውቁምን? በእነሱ ላይ ጥገኛ የሆኑ ሁሉ በእንደዚህ ዓይነት ማህበራት ውስጥ አይታሰሩምን? ሁልጊዜም ጉጉትን ለመፍጠር የበለጠ አስደናቂ ነገር ማቅረብ የሚቻል ይመስላል። በእርግጥ፣ ልዩ ትኩረት በፈውስ እና ምልክቶች ላይ ይደረጋል። በዚያ መንገድ የሚሰቃዩ ሰዎችን ወደ ስብሰባዎቻቸው መሳብ ቀላል ይሆንላቸዋል። ሁሉም ለእግዚአብሔር ታላቅ አገልግሎት እየሰሩ እንደሆነ ያምናሉ፣ ምንም እንኳን በእርሱ ፈቃድ ዉስጥ ባይሆኑም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆንም ለእግዚአብሔር "የራስን" አገልግሎት መስጠት ይቻላል።

በአጠቃላይ፣ ሰዎች አሁንም በተለይ በካቶሊክ አገሮች ተአምራትን ያምናሉ። ስታቲስቲክስ እንደሚያረጋግጠው፣ በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች የሐጅ ቦታዎችን ይጎበኛሉ። ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ እንኳ በተደጋጋሚ ወደ ፋጢማ የሐጅ ጉዞ ያደርጋሉ፣ "ጥይቱን በተአምራዊ ሁኔታ የመራችውን" ማርያምን ለማመስገን። ግን መጠየቅ አለብን፣ "እውነተኛውን ቃል፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ ምክር የሚሰብከው ማነው?" በትላልቅ ዘመቻዎች ላይ ጴጥሮስና ጳውሎስ የሰበኩትን ወንጌል የሚሰብከው ማነው? እነሱ ያስተማሩትን የሚያስተምረው ማነው? እነሱ እንዳጠመቁ የሚያጠምቀው ማነው?

የእምነት የመጀመሪያ እርምጃዎች ለመዳን ለሚፈልጉ ሰዎች በመጀመሪያው የባእለ ሃምሳ ቀን ስብከት ላይ ተገለጡ። በሐዋርያው በተሰበከው ስብከት ተጽዕኖ ስር ብዙ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነኩ። አድማጮች አንድ ጥያቄ ብቻ ጠየቁ እና በጣም ግልጽ የሆነ መልስ አገኙ። "ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፤ <u>ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያትን ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሏቸው። ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤</u> የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ..." (ሐዋ. 2:37-40)። ታሪኮችን አልሰሙም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ልብ የሚነካ ስብከት ነበር፣ እናም የመዳን መንገድ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ ታያቸው። ወዲያውኑም የእምነትን የመጀመሪያ እርምጃ በመውሰድ ተከተሉት። <u>"ቃሉን በደስታ የተቀበሉትም ተጠመቁ፤</u> በዚያም ቀን ሦስት ሺህ ያህል ነፍሳት ተጨመሩ።" (ቁ. 41)።

ስብከቱ የአድማጮችን ልብ ወጋው እና የእግዚአብሔር መንፈስ በጸጋ ንስሃን አሰራ። ዛሬም እውነተኛ ለውጥ የሚከናወነው በዚህ መንገድ ነው። በእውነት የሚያምኑ እና የሚድኑ ሰዎች፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት በውሃ ይጠመቃሉ፣ እናም መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ስርዓት ሲሆን ዛሬም ድረስ ትክክለኛ ነው። ሁሉም ሌሎች በሰዎች የተዋወቁ የውሸት ልምምዶች ናቸው፣ በነዚህም ሰዎች ስሜታዊ ልምዶችን ያገኛሉ፣ ነገር ግን ነፍሳቸው አልዳነም። ይቀባሉ፣ ግን ዳግም አልተወለዱም። ብዙ ነገሮች ለጥሩ ሁኔታ የታሰቡ ናቸዉ ፣ ነገር ግን ከመጻህፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር ካልተነፃፀሩ፣ አሳሳች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። እንደገናም ከመጀመሪያዉ እንደ ነበረዉ ጠባብ በር እና ቀጥተኛ መንገድ አሳዩን። ያልተስተካከለ ነገር ሁሉ መስተካከል አለበት እንዲሁም ስህተት የሆነ ነገር ሁሉ። <u>ዘመኑ ተፈጽሟል፣ የመጨረሻው ጥሪ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘለአለማዊ ወንጌል እውነተኛ አዋጅ ይወጣል</u> (ማቴ. 24:14፤ ራዕ. 14:6)።

ቅዱስ መጻህፍ በሁሉም ነገር መፈጸም አለበት፣ ኢያኔስና ኢያንብሬስ እንዳደረጉት ምልክቶችንና ተአምራትን በሚያደርጉ ሰዎች ላይም ቢሆን፣ ነገር ግን <u>በእኛ ዘመን በተላከው የእግዚአብሔር ሰው የተሰበከውን የእውነት ቃል በሚቃወሙትም ላይ</u>። ጳውሎስ የመጨረሻውን ዘመን በመንፈስ ያየው፣ እንደሚሆን ተንብዮ ነበር። ስለ አምላክ፣ የውሃ ጥምቀት፣ የጌታ እራት፣ ውድቀት እና ስሌሎች

ርዕሰ ጉዳዮች እዉነተኛ ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት  በአጠቃላይ የተሳሳቱ እንደሆኑ ይገለጻሉ እና ባህላዊ የቤተክርስቲያን ትምህርቶች ትክክል እንደሆኑ ይቆጠራሉ። ስለ እግዚአብሔርነት ያላቸውን የእምነት መግለጫ ወዘተ በ "ኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ" መጀመሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል፣ ነገር ግን ይዘቱ በጉባኤዎች ላይ የተወሰነ ሲሆን፣ ሐዋርያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሰጡት ጋር አይስማማም። እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ከዚህ አይነት የሃይማኖት መግለጫ ጋር ምን የሚያመሳስለው ነገር አለ? ሐዋርያዊው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ብቸኛው እውነተኛ የእምነት ቃል ነው። ሁላችንም በሃይማኖታዊ ውሸቶች ውስጥ ተወልደናል፣ ግን ለምን በውስጣቸው እንቆያለን፣ አሮጌውን አሳዛኝ ሁኔታ ለማራዘም ብቻ?

እግዚአብሔር ለአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የሚናገረው ነገር ቀድሞውኑ ተጽፏል እና የተሟላ ነው፣ ምንም ሊጨመር ወይም ሊቀየር አይችልም (ገላ. 3:15፤ ራዕ. 22)። የእውነት ሰዓት ደርሷል እናም እንደ ነብዩ ኢሳይያስ በምዕራፍ 21 ላይ "ጠባቂ ሆይ፥ ከሌሊቱ ስንት ነው?" ብለን እንጠይቃለን። መልሱም "ጥዋት ይመጣል፥ ሌሊትም እንዲሁ።" እኛ በመዳን ቀን ምሽት ላይ አይደለንም፣ ነገር ግን እኩለ ሌሊት ላይ ደርሰናል። የእኩለ ሌሊት ጩኸት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይሄዳል፣ "እነሆ፥ ሙሽራው ይመጣል፤ ልትቀበሉት ውጡ።" (ማቴ. 25)። አሁን መብራቶቻችንን ለማቃጠል ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እና የመንፈስ ቅዱስ አቅርቦት ያስፈልገናል። እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን አሁን ከሁሉም ሰው ሰራሽ፣ ከመጻህፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ስርዓቶች ተጠርታ ከሐሰቶች ተለያይታ የቃል ሙሽራ ለመሆን፣ ልክ ቃል በሙሽራው ውስጥ ሥጋ እንደሆነ።

<u>የእግዚአብሔር ልጆች እምነት አሁን ወደ ሐዋርያዊ አባቶቻችን እምነት እየተመለሰ ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንደሆንን እና ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ በእግዚአብሔር የመዳን እቅድ መሰረት በሚያደርገው ነገር ለመካፈል የምንችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።</u> እግዚአብሔር – ቢታመን ወይም ባይታመን፣ ቢቀበል ወይም ቢጠላ – በእኛ ዘመን ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ ተንቀሳቅሷል። የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች ትኩረት አሁን በቃሉ መሰረት በሚያደርገው ነገር ላይ እየተሳበ ነው። ትንሽ ትምህርት ያለው ትሁት ሰው ነበረ፣ ነገር ግን እንደ ኤልያስ አይነቶች። ደጋግሞ ወደ ዮሐ. 5:19+20 ይጠቅሳል፣ በእግዚአብሔር ላይ የተመሰረተ ስለነበር። የዚህ ሰው ምሳሌ የሰው ልጅ በትንቢታዊ አገልግሎቱ ነበር። "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወልድ ከአብ ሲያይ በቀር ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ እንዲሁ ያደርጋልና።" (ዮሐ. 5:19)።

ያ እውነተኛ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ነው! ያ እውነተኛ፣ ትንቢታዊ አገልግሎት ነው! ብዙ ሊነገር እና ብዙ መጽሐፍት ሊሞሉ ይችላሉ። ፈቃደኛ ልብ ያላቸው ሁሉ ጆሮ ይስጡ እና መንፈስ ለቤተክርስቲያናት የሚናገረውን ያዳምጡ። ዊልያም ብራንሃም የመጀመሪያ ጥምቀቱ ላይ ከ4,000 የሚጠጉ ምስክሮች ፊት የተነገረው በክርስቶስ የፍርድ ወንበር እውነት ይሆናል። ወንጌልን ከሰበከ በኋላ፣ እሁድ፣ ሰኔ 11 ቀን 1933፣ ኢንዲያና፣ ጄፈርሰንቪል በሚገኘው ኦሃዮ ወንዝ ውስጥ

በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አጠመቀ። 17ኛውን ሰው ሊያጠምቅ ሲል ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ጸለየ። ያኔ ነበር ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ደመና ልክ እንደ ኃይለኛ ኮከብ በ2:00 ከሰዓት አካባቢ የወረደው፣ ለሁሉም የሚታይ፣ እናም ድምፅ እንዲህ አለው፣ "መጥምቁ ዮሐንስ የክርስቶስን የመጀመሪያ መምጣት ለማስቀደም እንደተላከ፣ የተሰጠህ መልእክት የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ቀዳሚ ይሆናል።" ቄስ ቲ. ኤል. ኦስቦርን ይህን ያውቃል፣ ከምስክርነቱ እንደምንረዳው፤ ሌሎች ብዙዎችም እንዲሁ።

## ምልክቶቹ

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተነበየው፣ ወደ መድረኩ የመጡ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች በመኖራቸው፣ በቅዱሳት መጻሕፍት መሰረት የትክክለኛ ነቢይ ምልክቶችን ማገላት አስፈላጊ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፦

በእግዚአብሔር በቀጥታ ተጠርተዋል።

በእርሱ በቀጥታ ታዘዋል።

በእርሱ በቀጥታ ተልከዋል።

ቃሉን በቀጥታ ተቀብለዋል።

የታዩት በእግዚአብሔር ትእዛዝ ብቻ ነበር።

እነሱም ባለ ራእዮች ነበሩ፣ ራእዮችን  ይመለከቱ ነበር።

እግዚአብሔር የተናገረውን ብቻ ተናገሩ።

እርሱ የሰጣቸውን ትእዛዝ ብቻ አደረጉ።

ሁልጊዜም ውድቅ ይደረጉ እና ይሰደዱ ነበር።

የሚያገለግሉትን አንድ አምላክ ብቻ ያውቁ ነበር።

እነዚህ ሁሉ ምልክቶች በሐሰተኛ ነቢያት ዘንድ የሉም። ቀጥተኛ ጥሪ ወይም መለኮታዊ ተልእኮ የላቸውም። በእግዚአብሔር አልተላኩም፣ የመጀመሪያውን ቃል አያወጁም፣ ይልቁንም የራሳቸውን ትርጓሜዎች ያወጁና የራሳቸውን ፕሮግራሞች ይከታተላሉ፣ ለእግዚአብሔር የመዳን እቅድ ሳይገዙ። ምልክቶችና ድንቆች ብቻቸውን <u>መለኮታዊ ህጋዊነትን</u> አይመሰርቱም። የሚከተሉት ቅዱሳት መጻሕፍት በዚህ አስፈላጊ ጉዳይ ላይ ብርሃን ያበራሉ እና ያብራሩታል።

" በመካከልህም ነቢይ ወይም ህልም አላሚ ቢነሣ፤ ምልክትም ተአምራም ቢሰጥህ <u>፤እንደ ነገረህም ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም ፤</u> እርሱም ፦ ሄደን የማታዉቃቸዉን <u>ሌሎች አማልክት እንከተል</u>

እናምልካቸዉም ቢልህ፤ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹምም ትወድዱት እንደሆነ ያዉቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነዉና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ ፡፡**አምላካችሁ እግዚአብሔርን ተከተሉ ፤እርሱንም ፍሩ፤ትእዛዙንም ጠብቁ፤ቃሉንም ስሙ፤እርሱንም አምልኩ፤ ከእርሱም ጋር ተጣበቁ፡፡** አምላክህ እግዚአብሔር ትሄድባት ዘንድ ከአዘዘህ መንገድ ሊያወጣህ፤ከግብጽ ምድር ካወጣችሁ ከባርነት ቤት ካዳናችሁ ከአምላካችሁ ከእግዚአብሄር ሊያስታችሁ ተናግሯልና ያ ነቢይ ወይም ያ ህልም አላሚ ይገደል፤ እንዲሁም ክፉዉን ነገር ከመካከልህ አርቅ ” (ዘዳ. 13:1-5)፡፡

በነብዩ ሚክያስ ዘመን፣ “ነቢዩ” ሴዴቅያስ የብረት ቀንድ ለራሱ አበጀና፣ “ጌታ እንዲህ ይላል፦ በእነዚህ ሶርያን እስከሚጠፉ ድረስ ትወጋለህ አለ፡፡ ነቢያትም ሁሉ ፡- ጌታ በንጉሱ እጅ አሳልፎ ይሰጣታል እና ወደ ሬማት ዘገለዓድ ሂድና ተከናወን ሕያት እንዲሁ ትንቢት ይናገሩ ነበር ” (2 ዜና. 18:10ለ-11)፡፡ ነገር ግን ያ “ሴዴቅያስ እንዲህ ይላል!” እንጂ “ጌታ እንዲህ ይላል” አልነበረም፡፡ ሴዴቅያስና አራት መቶዎቹ ነቢያት በውሸት መንፈስ ተታለዉ ነበር፡፡ በሙሉ በብሉይ ኪዳን ወስጥ ሁልጊዜ አንድ እውነተኛ ነቢይ እና ብዙ በተሳሳት መንፈስ ተጽእኖ ስር የነበሩ ሐሰተኛ ነቢያት ነበሩ፡፡ ኤርምያስ 23 እና ሕዝቅኤል 13ን በተለይ ማንበብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በእውነተኛው ነቢይ ኤርምያስ በኩል ጌታ ሐሰተኛ ነቢያትን እየተናገረ፣ እየገሰጸ፣ “... በበኣል ትንቢት ተናገሩ፥ ሕዝቤንም እስራኤልን አሳሳቱ፡፡ ...

የሠራዊት ጌታ እንዲህ ይላል፦ ትንቢት የሚናገሩላችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ፡፡ እነርሱ ከራሳቸው ልብ ራእይ ይናገራሉ እንጂ ከአፌ አይደለም ፤ ከንቱነትን ያስተምሯችኋል፡፡ ...እኔ አልላክኋቸውም እነርሱ ግን ሮጡ፤ እኔ አልተናገርኋቸውም እነርሱ ግን ትንቢት ተናገሩ፡፡ በምክሬም ቆመው ቢሆን ኖሮ፥ ቃሌንም ለሕዝቤ ባሰሙ ነበር፥ ከክፉ መንገዳቸው ከክፉ ሥራቸውም ይመልሷቸው ነበር፡፡ ....

.. እስከ መቼ በውሸት ትንቢት በሚናገሩ ነቢያት ልብ ውስጥ ይሆናል? አዎን፥ እነርሱ ከራሳቸው ልብ ማታለል ትንቢት ይናገራሉ፤ አባቶቻቸውም ስለ በኣል ስሜን እንደረሱት፥ እያንዳንዱ ለባልንጀራዉ በሚናገራት ሕልማቸዉ ሕዝቤ ስሜን ለማስረሳት ያስባሉ” (ኤር. 23:13-32)፡፡

ጌታ እንዲህ ይላል “የሰው ልጅ ሆይ፥ ከራሳቸው ልብ ትንቢት በሚናገሩ ነቢያት ላይ ትንቢት ተናገር፤ **የጌታን ቃል ስሙ፤** ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ምንም ሳያዩ የገዛ መንፈሳቸዉን ለሚከተሉ ለሰነፎች ነቢያት ወዮላቸዉ! ... ከንቱነትንና የውሸት ምዋርትን አይተዋል፥ “ጌታ አለ” ይላሉ፡፡ ጌታ ግን አልላካቸውም፤ ቃሉን ያጸናላቸው ዘንድ ተስፋ አድርገው ነበር፡፡ ከንቱ ራእይ አላያችሁምን? የውሸት ምዋርትስ አልተናገራችሁምን? “ጌታ አለ” ስትሉ፥ ሆኖም ግ እኔ ግን አልተናገርኩም?

ስለዚህ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እናንተ ከንቱ ነገር ስለተናገራችሁ ውሸትም ስላያችሁ፥ እነሆ፥ እኔ በእናንተ ላይ ነኝ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። እጄም ከንቱ ነገር በሚያዩና የውሸት ምዋርትን በሚናገሩ ነቢያት ላይ ትሆናለች፤ በሕዝቤም ጉባኤ አይሆኑም። ...ሰላምም ሳይኖር "ሰላም" እያሉ ሕዝቤን ስላሳቱ..." (ሕዝ. 13:2-10)።

እውነተኛ "ጌታ እንዲህ ይላል" የሚለውን፣ በእውነተኛ ነቢያት የቀረበውን፣ በልቡ የሚቀበል ማንኛውም ሰው፣ እነዚያዉ አሳሳች መናፍስት ዛሬም እየሰሩ እንዳሉ እና ያው ማታለያዎች አሁንም እየተከናወኑ እንዳሉ በፍጥነት ይገነዘባል። መልካም ዓላማ ያላቸው የሚመስሉ ውሸቶች እየተነገሩ ነው፣ መልካም ዓላማ ካለው ከሚመስለዉ የጥንቆላ ትንቢት ጋር እየተቀላቀሉ፣ እንዲያውም የታሰቡ ራእዮች ይታያሉ። በሕዝቡ ፊት ስለ መዳን ይናገራሉ፣ ነገር ግን በእውነት በእግዚአብሔር ውስጥ ያለው በክርስቶስ መዳን የለም። ብዙዎች ለራሳቸው መንፈስ ይሰጣሉ። እግዚአብሔርን መርዳት ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን የልባቸውን ሀሳቦችን እየተነበዩ ነው። ሰዎች "ጌታ እንዲህ ይላል" የሚለዉን ሲሰሙ በጣም ይደሰታሉ፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ እነርሱ ተጭበርብረዋል እና "የሙሉ ወንጌል" ብለው በሚጠሩት ሐሰተኛ ክርስትና ውስጥ ይኖራሉ።

ከዚያም ጌታ በቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉ ትንቢት በሚናገሩ ሴቶች ላይ ይነሳል፣ እነሱም እንደ ምናባቸው ትንቢት ይናገራሉ። ብዙ ጊዜ "ጌታ ለአንተ ቃል ሰጥቶኛል! የሆነ ነገር አሳይቶኛል" ይላሉ። ይህ ያለምንም ጥርጥር መልካም ዓላማ ያለው ነው የሚመስለዉ፣ ነገር ግን በራሳቸው የተፈበረከ ነው። ለእነሱም "ወዮ!" ብሎ ተናገረ፣ ነፍሳትን ለማደን "ለመጠኑ የሚገጥሙ" ትንቢቶቻቸውን በመጥቀስ። ከዚያም ጌታ "ሴቶች" ብሎ በሚጠራቸው ነቢይ ሴቶች ላይ ልዩ ትኩረት ያደርጋል – እንደ ሴቲቷ ኤላዛቤል ነቢይት ሆና እንደሠራችው – እና ፍርዱን ያውጃል። "ስለዚህ ከንቱነትን አታዩም፥ ምዋርትንም አትናገሩም፤ ሕዝቤን ከእጃችሁ አድናለሁና፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ታውቃላችሁ።" (ቁ. 23)።

ሰባኪዎችን እና አብያተ ክርስቲያናትን በቁጥጥር ስር ያዋላቸዉ ሌላ መንፈሳዊ ስጦታ የለም-- ከፍ የተደረገ፣ አዋራጅ እና የተጭበረበረ - እንደ ተመሰለዉ የትንቢት ስጦታ። እውነተኛ አገልግሎቶችና ስጦታዎች ሁልጊዜ ቤተክርስቲያንን ከፍ ለማድረግ ያገለግላሉ፤ ፈጽሞ ለማሳሳት ወይም ለማጥፋት አይደለም። ሁሉም ይህን እርማት አይቀበልም፣ ነገር ግን ጌታ የራሱን ያውቃል። እርሱ ይጠራቸዋል፣ ይለያቸዋል፣ ያነጻቸዋል፣ እናም ሐሰተኛ ነቢያትና ነቢይ ሴቶች ከእንግዲህ በእነርሱ ላይ አይገዙም። ሐሰተኛ ትንቢቶችን የሚያዳምጥ ሰው የእውነተኛ ትንቢትን ቃል ሊያዳምጥ አይችልም። በቃሉና በቅዱስ ቃሉ ትንቢት ውስጥ የሚቆዩ ብቻ የሐሰተኛ ትንቢቶችን ቅዱስነት የጎደለው ማታለል ያመልጣሉ።

እንደገናም የእውነተኛ ነቢይ ምልክቶችን ልንጠቁም እንወዳለን፦ እያንዳንዱ እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይና አገልጋይ በቀጥታ የሾመዉን የእግዚአብሔርን ድምፅ በግልጽ ሰምቷል። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ነቢይ ቃሉን ከጌታ በቀጥታ ተቀብሎ ለህዝቡ የእግዚአብሔር ድምፅ ሆነ።

የእግዚአብሔር እውነተኛ ነቢያትና ሐዋርያት በእርሱ እንደ አገልጋዮች ይጠራሉ፣ ምክንያቱም በቀጥታ በእርሱ አገልግሎት ውስጥ ስላሉ፣ በእርሱ ስለተላኩ፣ እናም ጌታን በግል ያውቁታል።

ሚክያስ፣ እውነተኛው ነቢይ እንዲህ አለ "እግዚአብሔር ህያው ነው፣ አምላኬ የሚለውን እኔ እናገራለሁ... ደግሞም እንዲህ አለ፦ እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ እግዚአብሔርን በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁት፣ ሰማያዊውም ሠራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመዉ ነበር። ...እንግዲህ እግዚአብሔር በእነዚህ በነቢያትህ አፍ የውሸት መንፈስ አድርጓል፣ እግዚአብሔርም በአንተ ላይ ክፉ ተናግሯል" (2 ዜና. 18:12-13፤ 18፤ 22፤ 27)። ሚክያስ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘረዘሩት አራት መቶዎቹ ግን በራሳቸው የተሾሙ ነቢያት ነበሩ፣ በውሸት መንፈስ የተታለሉ ነበሩ። ልዩነቱን ልብ ይበሉ!

ኢዮሣፍጥ እንዲህ አለ፦ "እናንተ የይሁዳ ሰው ሁሉ፥ እናንተም የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች፥ ስሙኝ። በአምላካችሁ በእግዚአብሔር እመኑ፥ ጸንታችሁም ትኖራላችሁ፤ **በነቢያቱም እመኑ፥** ይሳካላችሁማል።" (2 ነገ. 20:20) ። "... በነቢያቱም እመኑ..." – ምክኒያቱም ነቢያቱ የተገለጠው ቃሉ እና የተገለጠው ፈቃዱ አላቸው።

## በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው አገልግሎት

ሐዋርያት ለዓመታት ፤ከትንሳኤው በኋላም ለአርባ ቀናት ያህል በጌታ እና በአለቃ የመማር ልዩ እድል ነበራቸው። ጳውሎስ እርሱን ከዕርገቱ በኋላ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ብርሃን አይቶ ድምፁንም በዕብራይስጥ በገዛ ቋንቋዉ ሰማ። "**...ስለዚህም እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና። የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ ፤ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይኖቻቸዉን ትከፍት ዘንድ ፤ ከሕዝቡና ወደ እርሱ ከምልክህ ከአህዛብ አድንሃለሁ** ..." (ሐዋ. 26:12-23)። ከመዳን እቅድ ጋር የተገናኘ መለኮታዊ ጥሪና ተልእኮ ይኸን ያክል ትክክል ነው! ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን ነቢያትንና መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸውን ሰዎችም ጭምር ተናግሯል። ዋናው ትኩረቱ የራሱን አስተያየት ማሰራጨት ሳይሆን ጌታ ያዘዘውን ማሰራጨት ነበር። "ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ ነኝ ብሎ ቢያስብ፣ የምጽፍላችሁ የጌታ ትእዛዝ መሆኑን ይውቅ። ነገር ግን ማንም የማያውቅ ከሆነ፣ አይውቅ።" (1 ቆሮ. 14:37-38)።

መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ፣ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ቃል ነው። በነቢያቱና በሐዋርያቱ አማካኝነት ጌታ ራሱ ተናግሯል። እነርሱም በቀጥታ ትእዛዙን ተቀብለው ተገበሩ። ጳውሎስ "ይህን በጌታ ቃል እንነግራችኋለን..." (1 ተሰ. 4:15) ብሎ ሊጽፍ ችሏል። የእግዚአብሔር ሰዎች በቀጥታ ትእዛዝ የተናገሩትን በትክክል የምንናገር ከሆነ ብቻ፣ እግዚአብሔር በእውነት የተናገረውን እንገልፃለን። ያኔ ብቻ አድማጮች "አሁን አንተ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆንህ፣ በአፍህም ያለው የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደ ሆነ አወቅሁ።" (1 ነገ. 17:24) በማለት

ማረጋገጥ ይችላሉ:: ከብዙዎቹ ቤተ እምነቶች ውስጥ ዛሬ የማን ነዉ፤ የእግዚአብሔር ቃል በእነርሱ በሚያዉጁት አፍ ዉስጥ እስካሁን የመጀመሪያዉ  እውነት ነው ሊባል የሚችለው? <u>ሐዋርያት እንዳደረጉት የሚያስተምርና የሚያጠምቅ ብቻ ነው በትክክል የሚያስተምረውና የሚያጠምቀው::</u> በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ስርአት ከመጀመሪያው ጀምሮ ተመስርቶ ነበር:: የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ከኢየሩሳሌም ወደ ዓለም ሁሉ ወጣ:: አሁን በእውነተኛው፣ ነገሮች ወደ ነበሩበት በተመለሱበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ትምህርቶችና ተግባሮች በመጀመሪያ እንደነበሩት መሆን አለባቸው::

ሐዋርያው ጳውሎስ ከተለወጠ ከሦስት ዓመታት በኋላ ከጴጥሮስ ጋር ለመነጋገር የመጀመሪያ ጉዞዉን ወደ ኢየሩሳሌም አደረገ:: በአስራ አምስት ቀናት ቆይታው ጳውሎስ ከጴጥሮስ መንፈሳዊ ጅማሬዎችን ሁሉ ሰማ:: የጌታችን ወንድምን ያዕቆብንም አገኘው:: ከአሥራ አራት ዓመታት በኋላ፣ ያው ጳውሎስ ከበርናባስና ከቲቶ ጋር በመሆን በመለኮታዊ ትእዛዝ ሌላ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም አደረገ:: በዚህ ጊዜ ዓላማው መረጃ ለመሰብሰብ ሳይሆን፣ <u>ትምህርቱና ስብከቱ ትክክል መሆኑን ወይም ሥራው ሁሉ በከንቱ እንዳይሆን ለማረጋገጥ ነበር </u>(ገላ. 1:18 — 2:2) ::

<u>በዚህም ምክንያት ሁሉም ሰባኪዎች፣ ወንጌላውያን፣ አስተማሪዎች፣ ነቢያት፣ ሁሉም አገልጋዮች በመንፈስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲጓዝ እና የሚያስተምሩትና የሚተገብሩት ነገር ከተጻፈው ቃል ጋር ይስማማ እንደሆነ በትክክል እና በሐቀኝነት ለማነፃፀር ተጋብዘዋል</u>:: ንፅፅሩ ሁልጊዜ ከመጀመሪያው ጋር መደረግ አለበት:: ነገሮች መጀመሪያ ላይ ምንም ይሁኑ ምን እና እንዴትም ቢሆኑ ፣ አሁን በመጨረሻውም እንዲሁ መሆን አለባቸው – ሙሽራዋ ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር እና ከቃሉ ጋር ኢየሱስ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ሙሉ በሙሉ መጣጣም አለባት:: ወደ መጻህፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች እና ሐዋርያዊ ተግባራት ሙሉ በሙሉ መመለስ የሰዓቱ ትእዛዝ እና መልእክት ነው::

ማጭበርበሮችና የተሳሳቱ ትርጓሜዎች በኃጢአት ሰው ቀድመው ተጀምረው ከእውነተኛው ትምህርት ታላቅ መለየት አስከትለዋል:: የመጀመሪያ ከፍታቸውን ያገኙት እ.ኤ.አ በ325 ዓ.ም በኒቂያ ጉባኤ በተጀመረው የመጀመሪያው የተደራጀ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር:: ሌሎች የቤተክርስቲያን ጉባኤዎች በ381 እና በ441 ተከተሉ፣ ከዚያም የመካከለኛው ዘመን መጣ፣ የጨለማው ዘመን ተብሎም ይታወቃል፣ በዚህም የቃሉ ብርሃን ከሞላ ጎደል ታፍኖ ነበር:: በመጨረሻም፣ ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ፣ በተሃድሶዉ በኩል አዲስ ግኝት መጣ፣ ከዚያም ባለፉት መቶ ዘመናት የተለያዩ መነቃቃቶች ተከሰቱ፣ በዚህም የመጻህፍ ቅዱስ እውነቶች የበለጠ ወደ ነበሩበት እየተመለሱ ሄዱ:: የሚያሳዝነው፣ የድሮ ባህሎች ቀጥለዋል፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በመንፈስ ቅዱስ  ኃይለኛ እንቅስቃሴ በተጀመሩት መነቃቃቶች ወቅትም ቢሆን:: ጠላት የእግዚአብሔር መንፈስ በሚሰራበት ቦታ እንኳን ማሳሳቱን ቀጠለ እና ትክክለኛውን የተሳሳተ፣ የተሳሳተውንም ትክክል የማለት እቅዱን በተሳካ ሁኔታ አከናውኗል:: እስከ ዛሬ ድረስ፣ አሮጌ እርሾ ሁልጊዜ አዲሱን ሊጥ አበላሽቷል:: የተደራጁ ቤተክርስቲያኖች ተፈጠሩ እና አሮጌውን አሳዛኝ ሁኔታ ቀጠሉ::

ጌታችን ለሃይማኖተኞች አይሁዶች የተናገረው ነገር ታማኝ ላልሆነው ክርስትናም ይሠራል፦ "ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው። የሰውም ስርአት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ተብሎ እንደ ተጻፈ በእዉነት ትንቢት ተናገረ ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁና። ...ደግሞም። የገዛ ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችሁታል።" (ማር. 7:6-9)።

ጌታ እንደተናገረው፣ የሰው ትምህርቶችና ትእዛዛት በእግዚአብሔር ቃል ፋንታ በሚታመንበት ጊዜ፣ ሁሉም አምልኮ፣ በካሪዝማቲክ ስብሰባዎች ውስጥ ያለው ምስጋናም እንኳ ከንቱ ነው። ኢየሱስ ጌታችን ይህን ሁኔታ አስቀድሞ አስቀመጠ፣ **"በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ..."** (ዮሐ. 7:38)። ጌታ የእግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት መመለክን ይሻል (ዮሐ. 4:24)። የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አማኞችን የሚመራበትና የሚይቀድስበት እውነት ነው።

አሁን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ቅርብ በሆነበት ጊዜ፣ የትንቢታዊው ክፍልም ያስፈልገናል፣ ጴጥሮስም በመልእክቱ እጅግ በሚያስገርም መንገድ እንዳስረዳው፦ "የእርሱን ግርማ አይተን እንጅ በብልሃት የተፈጠረዉን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታውቀናችሁ።" (2 ጴጥ. 1:16)። ሐዋርያው በመለወጥ ተራራ ላይ ለሆነው ክብር የተሞላ ተሞክሮ ምስክር ነበር። በመጨረሻው ማረጋገጫም እንደዚህ ብሎ ሊጽፍ ችሏል "እኛም ከዚህ የበለጠ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ቀኑ እስኪወጣ ድረስ፥ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪበራ ድረስ፥ በጨለማ ስፍራ እንደሚበራ መብራት አድርጋችሁ ለእርሱ መልካም ታደርጋላችሁ" (ቁ. 19)።

በዛሬው ጊዜ፣ የትንቢታዊው ቃል ትክክለኛ ባለቤት ነኝ በእውነት ማን ሊል ይችላል፣ ትርጓሜውን ሳይሆን፣ ነገር ግን እውን መሆኑን? ምክንያቱም የዚያን ጊዜ ብቻ ነው እንደ ደማቅ ብርሃን የሚያበራው። ዛሬ ብዙዎች በራሳቸው ትንቢቶች ተጠምደዋል እና ሁልጊዜ የሚያቀርቡት አዲስ ነገር አላቸው፣ ስለዚህ ወደ ተጻፈው ትንቢታዊ ቃል እንኳን የመሳብ ስሜት የላቸዉም። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ምንም የግል ትርጓሜ አይፈቅድም እና በምንም አይነት በራሳቸው በተሰሩ ትንቢቶች ምክንያት ትክክለኛነቱን አያጣም። በተቃራኒው፣ በሰዎች የተፈጠሩት ትንቢቶች በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ውድቅ እና ባዶ ይሆናሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ሁልጊዜም ከተስፋዎች ጋር የተገናኙ ናቸው፣ እነዚህም በፍጻሜያቸው ትክክለኛነታቸውን ያገኛሉ።

በዚህ ነጥብ ላይ መለኮታዊ ህጋዊነትን ካልተከተልን፣ ማብራሪያዉ ዓላማውን ያከሽፋል። "ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፥ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤ መንገዱንም ያስተምረናል፥ በጎዳናዉም እንሄዳለን፤ ሕግ ከጽዮን፣ የጌታም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና።" (ኢሳ. 2:3ለ)። እውነተኛው ቃል ከኢየሩሳሌም ወጣ። እዚያ ነቢያት አገለገሉ፣ ጌታችንና ሐዋርያትም እንዲሁ። እዚያም የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን መሠረት ተጣለ። እዚያም ተፈጠረች፤ እዚያም በትምህርትና በተግባር ወደ ነበረችበት መመለስ አለባት።

# ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች

አሁን በሃይማኖታዊው ዓለም ታላቁን ማታለል እያየን ነው። በማቴ. 24 ኢየሱስ ተንብዮ ነበር፣ “ብዙ ሐሰተኛ ነቢያትም ይነሣሉ፥ ብዙዎችንም ያስታሉ።” (ቁ. 11)። የሁሉም ሃይማኖቶችና ቤተ እምነቶች፣ አብያተ ክርስቲያናትና ማኅበራት ተወካዮች በተፈጥሮ ራሳቸውን ትክክል እንደሆኑ ያቀርባሉ። በውጭ ብዙ ማስዋቢያዎችን ከመጻህፍ ቅዱስ ጥቅስ ጋር እናያለን፣ ነገር ግን ጌታ ውስጡን አይቶ እንዲህ ይላል **“ከሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ...”** (ማቴ. 7:15) ። ይህን ማስጠንቀቂያ ከልባችን መውሰድ አለብን፣ ምክንያቱም ሁሉም በሌላ ቦታ እንዳሉ ቢጠረጠሩም፣ እዚህ የምንነጋገረው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት፣ ስለ አማኞች፣ ስለ ቤተክርስቲያን ነው። ሰይጣን ራሱ ያምናል፣ <u>መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው</u> ሳይሆን በራሱ መንገድ ። በዓለም ሃይማኖቶች እና በክርስትና ውስጥም ብዙዎች እንደፈለጉ ያምናሉ። ምድር በሙሉ በእንደዚህ አይነት አማኞች ተሞልታለች። በተሃድሶዉ ዘመን የሐሰተኛው ነቢይና የክርስቶስ ተቃዋሚ ማን ነዉ የሚለው ጥያቄ ተነስቶ ነበር። በዚያ በነበረዉ ማጠቃለያም ሁሉም ተሐድሶ አድራጊዎች፣ በሌሎች ልዩነቶች ቢኖራቸዉም፣ አንድ ሆነው ነበር። በዚህ ማብራሪያ ምዕራፍ ውስጥ የእኛ ትኩረት ስለ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች ነው።

ሐሰተኛ ነቢያት እነማን ናቸው? በእውነት እነማን እንደሆኑ እንዴት ሊታወቁ ይችላሉ? <u>መጻሕፍ ቅዱስ ራሱ እንዲናገር እንፈቅዳለን።</u> ምክንያቱም የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ምክርን የሚሰጥ ወይም ሊያስተምር የሚችል የሥነ መለኮት ፋኩልቲ፣ በምድር ላይ የሰባኪዎች ሴሚናር የለምና። ከተገለጠው የእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ለመድረስ፣ እንደ ነቢያትና ሐዋርያት ምሳሌ መለኮታዊ ሥልጣን የሚሰጥ መለኮታዊ ተልእኮ ያስፈልጋል። ሁሉን አዋቂው አምላክ፣ አሳዛኙን ክስተቶች አስቀድሞ የተመለከተው፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ መጨረሻውን የሚያውቀው፣ የተናገረውን ለእኛ ትተውልናል።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ እያንዳንዱ ማጭበርበር ከመጀመሪያው ጋር በተቻለ መጠን የተቀራረበ መሆን አለበት ወደሚል ምክንያታዊ መደምደሚያ መድረስ አለብን። የውሸት የዶላር ወረቀት ከመጀመሪያው ጋር በጣም ተመሳሳይ መሆን አለበት፣ በዚህም ተራ ሰው ልዩነቱን አይለይም። ይህን ሳስብ አንድ የግል ልምዴ ትዝ አለኝ። ከብዙ ዓመታት በፊት፣ በ “ባንክ ኦፍ ኮሜርስ” ሂሳብ ውስጥ ገንዘብ አስቀምጬ ነበር። በድንገት፣ ጸሐፊው አንድ የ100 ዲኤም ወረቀት አንስቶ፣ “ይህ የውሸት ገንዘብ ነው፣ የፖሊስ የወንጀል ክፍልን መጥራት አለብኝ” አለ። <u>ለተራ ሰው በፍፁም የማይታይ፣ አጠራጣሪ ያልሆነ፣ ነገር ግን በባለሙያው እጅና ዓይን ወዲያውኑ ታወቀ።</u> ይህ ለእኔ በጣም ጠቃሚ ትምህርት ነበር። እኔ አጭበርባሪ አልነበርኩም፣ ብዙዎቹም ያውን ገንዘብ ለሌሎች የሰጡ ሰዎች አጭበርባሪ አልነበሩም። ብዙዎች የውሸት፣ “ክርስቲያናዊ” የሚባሉ ትምህርቶችን እያስተላለፉ ነው፣ እነሱም ማጭበርበሮችን እያስተላለፉ መሆናቸውን ሳያውቁ። የመጀመሪያውን አያውቁም፣ ስለዚህ አስመሳዮችን ማወቅ አይችሉም።

የዛሬዎቹ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች አስመሳዮቹ አይደሉም፣ ነገር ግን ሳያውቁት ማጭበርበሮችን ለሌሎች ያስተላልፋሉ። ሁሉም የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር፣ እውቅና ባለው፣ መሪ ቦታ ላይ መሆናቸው ነው፣ ነገር ግን ሌሎችን ያሳስታሉ፣ ይሳሳታሉ፣ ያታልላሉ፣ እነርሱም እንደተታለሉ (2 ጢሞ. 3:13)። በማቴ. 24:4 ጌታችን አጥብቆ እንዲህ አለ፣ "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች በስሜ ይመጣሉና፣ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ..." (ማቴ. 24:4-5) – "ልዩ ቅባት አለኝ!" ጦርነቶችንና ሁሉንም የተፈጥሮ አደጋዎችን ከተነበየ በኋላ፣ ብዙዎች በሐሰተኛ ነቢያት እንደሚታለሉ ድጋሚ አጽንዖት ሰጠ (ማቴ. 24:11)።

ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች ትምህርታቸውን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አያወዳድሩም። ነገር ግን እውነተኛ ይመስላሉ፣ ስለዚህ የቃሉ መለኮታዊ ባለሙያ ብቻ አስመሳዮችን ሊያውቅ ይችላል። የግሪክ ቃል "ክርስቶስ" እና ተመጣጣኝ የዕብራይስጥ ቃል "መሲሕ" ለኛ "ክርስቶስ" ወይም "ቅቡዓን" በመባል ይታወቃሉ። በብሉይ ኪዳን ነገሥታትና ካህናት ይቀቡ ነበር። ንጉሥ ሳኦል ተቀባ፣ ንጉሥ ዳዊት ተቀባ፣ አሮንም ከወንዶች ልጆቹ ጋር ተቀቡ። **እውነተኛዎቹ ነቢያት "በእግዚአብሔር የተቀቡ" ተብለው ይጠሩ ነበር**። ጌታ ራሱ **"የቀባኋቸዉን አትዳስሱ፤በነቢያቶቼም ክፉ አታድርጉ።"** (መዝ. 105:15) ይላል። **ኢየሱስ የተቀባ፣ ክርስቶስ ነበር።** እንደ ሉቃስ 4:17-19፣ ከነብዩ ኢሳይያስ ምዕራፍ 61 እንዲህ ሲል አነበበ፦ "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ **ቀብቶኛልና**..." (ሉቃስ 4:18)።

ሐዋርያው ጴጥሮስ አረጋግጦ እንዲህ አለ፦ "እግዚአብሔርም በአንደበታቸው ተናግሮ፣ ክርስቶስ እንደሚሰቃይ አስቀድሞ የነገረው ሁሉ፣ እንዲሁ አድርጎ ፈጽሟል።" (ሐዋ. 3:18)።

"...እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስና በኃይል እንዴት እንደ **ቀባው**፤ እርሱም መልካምን እያደረገ፥ በዲያብሎስ የተጨነቁትንም ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና።" (ሐዋ. 10:38)።

ጌታችን ስለ ሐሰተኛ የተቀቡት ያስጠነቅቀናል። ሊቀቡ ይችላሉ፣ ግን ሐሰተኛ ናቸው። አንድ ምልክት ለሁሉም የተሳሳቱ ሰዎች ይሠራል፦ ሁልጊዜ ከትክክለኛው ሰው ጋር ይቃወማሉ፣ እናም በዚህም ምክንያት በጌታና በተቀባዉ ላይ ይቃወማሉ (ሐዋ. 4:24-31)። ግብፃውያን፣ ኢያኔስና ያምብሬስ ብቻ ሳይሆኑ፣ ከራሳቸው መካከልም ቢሆን፣ መሪ ወንድሞች በእርሱ ላይ ተነሱ፣ እነርሱም ዳታን፣ ቆሬና ሌሎችም ነበሩ (ዘኍ. 16)። ተባብረው ተደራጅተው ሴራ አደረጉ፣ በእግዚአብሔርና በእውነተኛው ነቢዩ በሙሴ ላይ ቀጥተኛ ተቃውሞ።

እንደገናም፣ በማቴ. 24፣ ጌታችን ወደ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች ይጠቅሳል እና ይህን ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ "ሐሰተኛ ክርስቶሶች እና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሳሉና፣ ትላልቅ ምልክቶችና ድንቆችም ያሳያሉ፣ ስለዚህም ቢቻል የተመረጡትን እንኳ **ያስታሉ**።" (ቁ. 24)። እንዲያውም ያው፦ ሐሰተኛና ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች! ይህን ማን ሊረዳ ይችላል? በፍፁም አብሮ መሆን የለበትም እና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መሆን የለበትም። ነገር ግን እንደ ዳታንና ቆሬ፣ እነርሱ

የቤተክርስቲያን ናቸው፣ ግን በሐሰተኛ መነሳሳትና በሐሰተኛ ትምህርቶች ስር ናቸው። በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ጌታ ብቻ የተለያዩ አገልግሎቶችን የመሾም መብት አለው። ሁሉም ሰው እንደፈለገው ማድረግ አይችልም፣ ምክንያቱም ያ ወደ ውድቀት ይመራል፣ እንደ ሉሲፈር፣ ቅቡዕ መልአክ እንደሆነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሐሰተኛ ወንድሞች አስጠንቅቆናል። እነርሱ በእውነት ወንድሞች ናቸው፣ ግን ሐሰተኛ ናቸው። ዛሬ፣ ጌታችን እንደተነበየው፣ ብዙ እንደዚህ አይነት ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ቅቡዓን አለን።

ምልክቶችንና ድንቆችን እንደ ህጋዊነታቸው ሊያቀርቡ ይችላሉ። በዚህም ልባቸው እውነተኛ የሆኑ፣ ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተመሰረቱ አማኞችን ያሳስታሉ። እነርሱ አምላክ የለሽ ሰዎች አይደሉም፣ ትክክለኛዎቹ አስመሳይ አይደሉም፣ በራሳቸው መንገድ ያምናሉ። ወዳጃዊ ናቸው እና የሙሉ ወንጌል ሰባኪዎች እንደሆኑ ይናገራሉ እና አሳማኝ ገጽታ አላቸው። ከጌታ ታላቅ ተልእኮ ጋር በተያያዘ የተoбeሆኑ ምልክቶችም አሏቸው። አጠቃላይ ምስሉ እውነተኛና ጥሩ ይመስላል። ስብሰባዎቻቸው ሰዎችን ከሁሉም ቤተ እምነቶች ይስባሉ፣ እና ሁሉም ይደነቃሉ እና ይገረማሉ። ጌታ ራሱ፣ ቢቻል ኖሮ የተመረጡትም እንኳ **ይታለሉ** ነበር ብሏል። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፣ ያ የማይቻል ነው። ነገር ግን ቅጂው ከእውነተኛው ነገር ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው፣ ስለዚህም የመጀመሪያውን የሚያውቁ እና ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚለው በእውነት የሚያምኑ ብቻ ልዩነቱን ያስተውላሉ እና ውጫዊውን ገጽታ ያዩታል። የተመረጡት ምልክቶችንና ድንቆችን አይከተሉም፣ ጌታቸውንና አዳኛቸውን ይከተላሉ። ሁሉንም ትምህርቶች፣ ትንቢቶች እና አጠቃላይ ስብከቱን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያረጋግጣሉ እና ሊወሰዱ አይፈቅዱም፣ ነገር ግን በሐዋርያት ትምህርቶች ይቆያሉ (ሐዋ. 2:42፤ ኤፌ. 2:20፤ 2 ጴጥ. 3:2 ወዘተ)።

ሁልጊዜም በጌታ የተላኩ ነበሩ፣ እና በራሳቸው ፍላጎት ወደ ትዕይንቱ የመጡ አይነቶች። ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶችም ከእግዚአብሔር ነጻ ሆነው ግን በመንግሥቱ ውስጥ ይወጣሉ። ሆን ብለው አያታልሉም፣ አያውቁትም እንኳ። <u>እነርሱ አስመሳይ አይደሉም፣ ነገር ግን የተጭበረበረውን ያስተላልፋሉ። ሐቀኛ ናቸው፣ ግን የተሳሳቱ ናቸው፣ እራሳቸው በሃይማኖታዊ ማታለል ውስጥ ተወልደዋል</u>። ይህ እድገት በሐዋርያትም ተተንብዮ ነበር። ሁሉም ማጭበርበሮች ረጅም ወግ አላቸው። ትክክል ያልሆነው ነገር ሁሉ፣ ማለትም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማው፣ በራስ-ሰር የተሳሳተ ነው። ይህን ማስጠንቀቂያ በጣም በቁም ነገር መውሰድ አለብን እና መጠየቅ አለብን፦

ዛሬ እነማን ናቸዉ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ አስተማሪዎች፣ የሚያስወቅስ ኑፋቄዎችን የሚያመጡ፣ ስለ እነሱ ሐዋርያው ጴጥሮስ <u>ስለ እውነት መንገድ</u> ክፉ እንደሚናገሩ ያስጠነቀቀው (2 ጴጥ. 2:1-3)?

ዛሬ እነማን ናቸዉ <u>ትክክለኛውን መንገድ ትተው</u> የዓመፃን ዋጋ የወደደው የበለዓም መንገድ የሄዱት (2 ጴጥ. 2: 12-19 )?

ዛሬ ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ እነርሱ የጻፈዉ ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች እነማን ናቸው (1 ዮሐ. 2:18-20)? ዛሬ ወደ ዓለም የወጡ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት እነማን ናቸው (1 ዮሐ. 4:1)?

ዛሬ ጳውሎስ ያላቸዉ ሰዎች እነማን ናቸው፣ ከቤተክርስቲያን ውስጥ ራሳቸው ወጥተው የሐሰት ትምህርቶችን የሚያስተምሩ፣ ደቀ መዛሙርትንም እንዲከተሉ የሚያታልሉ (ሐዋ. 20:26-32)?

ዛሬ ሌላ ኢየሱስን የሚሰብኩ፣ ሌላ ወንጌልን የሚያውጁ እና በሌላ መንፈስ ተጽዕኖ ስር የሆኑት እነማን ናቸው (2 ቆሮ. 11:4)?

ዛሬ የክርስቶስ ሐዋርያት እንደሆኑ ራሳቸውን የሚያቀርቡ፣ የመልአክ ብርሃን መልክ ያላቸው፣ ግን አታላይ ሠራተኞች የሆኑት እነማን ናቸው (2 ቆሮ. 11:10-15) ?

ዛሬ የእግዚአብሔር መንፈስ በኋለኛው ዘመን እንደሚታዩ፣ አሳሳች መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርቶች እንደሚሰሙ የተናገራቸው እነማን ናቸው (1 ጢሞ. 4:1-3) ?

ከእግዚአብሔር ያልመጣው ሁሉ ከሰይጣን የመጣ ነው:: ምንም ዓይነት ማጭበርበር፣ ምንም ዓይነት ውሸት ከእውነት ሊመጣ አይችልም (1 ዮሐ. 2:21) :: በእርግጥም፣ በባህላዊው ክርስትና ውስጥ የሆነው ነገር አሳዛኝ ነው እና ሰዎች አያዩትም፣ ምክንያቱም ትክክለኛው በተሳሳተው ተተክቶ ነበር:: ርዕስ ጉዳዮቹ ይቀራሉ፣ ግን ይዘቱ ተቀይሯል::

## አሁን ሁሉም ነገር ሊፈተን ይገባል!

## የሚነገረዉ የእምነት ቃል (confession) እውነተኛ መሆን አለበት እና ትምህርቱ ትክክል መሆን አለበት::

በመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን ከሐዋርያት ትምህርት ያፈነገጡ ሰዎች ሐሰተኛ እንደሆኑ ተጋለጡ (ራዕ. 2:2):: ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ስህተቱ በሐሰት ተጽእኖ እየሰራ ትክክለኛዉን ነገር እያሸነፈዉ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በሰው ቃል ተተካ፣ እስከ መጨረሻም ጌታችን የተናገረው እውነት ሆነ:: “አትፍራ፤ አንተ ታናሽ መንጋ፤ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና::” (ሉቃስ 12:32):: በተመረጠው ቅሬታ በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ዘመናት እንደዚያ ነበር (ሮሜ 11:5):: ስለዚህ፣ በሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመን መልእክቶች ውስጥ ያሉት ቃል የተገቡት ነገሮች ለአሸናፊዎች ብቻ ነበሩ (ራዕ. 2 + 3):: ገና ከመጀመሪያዉ ጀምሮ በእስራኤል ልጆች ላይ ወጥመድ የጣለዉን የበላዓምን ትምህርት የተከተሉ አማኞች ነበሩ ፤ እንዲሁም ራሳቸዉን ከአማኞች በላይ ከፍ ያደረጉ የኒቆላዊያንን ትምህርት የተከተሉም ነበሩ(ራዕ. 2:14-16):: “ኤልዛቤል” የምትባል ሴትም ነብይትና አስተማሪ ነኝ እያለች የራሷን መንገድ ተከትላ አንዳንድ የእግዚአብሄር አገልጋዮችን አሳሳተች(ራዕ. 2:20-21):: ከመጀመሪያው ጀምሮ አሳዛኝ ሁኔታዎችን እና ከእግዚአብሔር፣ ከቃሉ እና ከእውነተኛው እምነት እየተለዩ መሄድን ማየት እንችላለን፣ እናም ብዙ ልዩነቶችን እና ማጭበርበሮችን ማግኘት እንችላለን:: ገና ቀደም ብሎ፣ ሰዎች በቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች

የተሳሳተ ትርጓሜዎች ተሳስተው ነበር። በኂላም፣ በተለያዩ ጉባኤዎች ውስጥ፣ ከእነዚያ ትምህርቶች አንዳንዶቹ እንደ እምነት መግለጫዎች እና ቀኖና ተብለው ታወጁ።

በእውነት በተቀባ እና በሐሰተኛው መካከል ያለው ልዩነት የሚከተለው ነው፦ በእግዚአብሔር የተላኩት እውነተኛ ሰዎች ቃሉን ይሰብካሉ ጌታም በሚከተሉ ምልክቶችና ተአምራት ያረጋግጠዋል። በራሳቸው ፍላጎት ወደ መድረኩ የሚመጡ ሰዎች ታሪኮችን ይናገራሉ፣ ስለ ምልክቶችና ድንቆች ይሰብካሉ እንዲሁም ቃሉን በመተላለፍ ሰዎችን ወደ ጥፋት ይመራሉ። አንድ ሰው በቃሉ ውስጥ ከቆየ ብቻ በእግዚአብሔር ውስጥ ይኖራል። ነገር ግን መጀመሪያ በቃሉ ዉሥጥ ለመኖር ቃሉን መቀበል አለብን።

የሰዓቱ ትእዛዝ ማን ሐሰተኛ ክርስቶስ፣ ሐሰተኛ ነቢይ ወይም ሁለቱም እንደሆነ፣ በመጻህፍ ቅዱስ ዉስጥ ያለዉን ምስክርነት በመጠቀም መለየት ነው። ቃሉ ሁልጊዜ ወደ እውነተኛ ነቢያት መጣ። ሐሰተኛ ነቢያት ሁልጊዜ የራሳቸው የቃሉ ትርጓሜዎች ነበሯቸው፣ ግን መቸም የመጀመሪያው ቃል አልነበራቸውም። ይኸም ለሐሰተኛ ለተቀቡትም ይሠራል። እነርሱ የክርስቶስና የሐዋርያት እውነተኛ ትምህርቶች የሏቸውም፣ በቤተክርስቲያን ታሪክ ሂደት ውስጥ የገቡ የራሳቸው የአስተምህሮ አመለካከቶች አሏቸው። በእውነተኛ ነቢያት አማካኝነት እግዚአብሔር ራሱ ተናገረ፣ ሐሰተኛ ነቢያት ስለ እርሱ እንደ እራሳቸው አመለካከት ይናገራሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና በሥጋ እንደ ተገለጠ የሚደረገው ምስክርነት(confession) በሁሉም ክርስትና ዘንድ፣ በሐሰተኛ ነቢያትና በሐሰተኛ ክርስቶሶችም እንኳ ይደረጋል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ጋር ሲነፃፀር ትርጉሙ ከተቀየረ፣ እውነተኛ የእምነት ቃል(confession) አይደለም። ለምሳሌ፣ የክርስትና ሥነ-መለኮት አንዱ ትምህርት፣ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፣ ወልድ በእግዚአብሔር የፈጠራ ሥራ "የመጀመሪያው" ሆኖ በሰማይ ተፈጠረ የሚለው ነው። ሌላው ደግሞ፣ ዓለም ከመፈጠሩ በፊትም በዘላለም በእግዚአብሔር ተወለደ የሚለው ነው። በኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ ላይ "**እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር፣ ብርሃን ከብርሃን፣ እውነተኛ አምላክ ከእውነተኛ አምላክ...**" ይላል። እንደዚያ ከሆነ፣ ሁለት አምላክ የሆኑ፣ ሁለት ብርሃን የሆኑ ወዘተ ይኖሩናል። ሦስተኛው ትምህርት፣ ወልድ በብሉይ ኪዳን የመላእክት አለቃ ሚካኤል ነበር የሚለው ነው። እና አሁንም ሁሉም ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክራሉ(confess)። ከመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ጋር የማይስማሙ ሌሎች ቅጅዎችም አሉ፣ ነገር ግን የሰው አእምሮ ነጸብራቅ እና በቅዠት የተፈጠሩ ናቸው።

በብሉይ ኪዳን **እርሱ ጌታ**፣ **ያህዌ**(YAHWEH)፣ **እኔ ነኝ**(the I AM) – ሎጎስ፣ ቃል፣ የማይታየው የእግዚአብሔር የሚታይ፣ የሚሰራ፣ የሚራመድ መገለጥ ነው፣ እርሱ ራሱ መንፈስ ነው (ዮሐ. 4:24)፣ ማንም ሰዉ አይቶት አያዉቅም (1 ጢሞ. 6:16፤ 1 ዮሐ. 4:12)። በዔድን ገነት የተራመደዉ፣ ለአብርሃም የተናገረው፣ ሙሴን ያዘዘው እና በነቢያት በኩል የተናገረው፣ ያዉ ጌታ ፣ በቤተልሔም በረት ውስጥ በምድር ላይ የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ወደ ሰው ዘር

የመጣው እንደሆነ እናውቃለን። "ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት ተወልዶላችኋል እርሱም <u>ክርስቶስ ጌታ ነው።</u>" (ሉቃስ 2:11)። ሰማያዊው ልጅ በምድር ላይ ልጅ አልሆነም፣ ነገር ግን ቃል ሥጋ ሆነ፣ ጌታ አገልጋይ ሆነ። ጳውሎስ የተናገረው አሁንም ትክክለል ነው፦ ማንም ሰው <u>ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት በእውነት ሊሰጥ አይችልም፣ በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር</u> (1 ቆሮ. 12:3)። ሁሉም ሰው መደበኛ የእምነት ቃል(confession) ሊደግም ይችላል። አጋንንትም እንኳ "...የናዝሬቱ ኢየሱስ ከአንተ ጋር ምን አለን?" ብለው ጮኹና "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ።" (ሉቃስ 4:34 + 41) ብለው ተናገሩ(confessed)። የአጋንንት መናገር(confession) በእርግጥ አላጸደቃቸውም እናም ምንም እንኳን ቢመሰክሩም እንደ ሁልጊዜው እንደነበሩት ናቸዉ። በመናገራቸዉ (confession) ምክንያት ክርስቲያኖች ወይም እውነተኛ አማኞች አልሆኑም።

እንደ ጴጥሮስ፣ ሁሉም ሰው የግል መገለጥ ያስፈልገዋል (ማቴ. 16)። ሌላው ሁሉ የአእምሮ ነጸብራቅ ነው፣ ይኸም እየተደጋገመ ያለ እና በእግዚአብሔር ፊት ምንም ዋጋ የሌለዉ ነዉ። ጌታ እንዲህ ይላልና፦ "...ወልድ ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፥ አብም ማን እንደ ሆነ ከወልድ በቀር የሚያውቅ የለም፥ ወልድም ሊገለጥለት ከፈቀደለት በቀር።" (ሉቃስ 10:22)። አብ በወልድ እንደተገለጠ ሁሉ፣ ለእያንዳንዱ ሰው በግል መገለጥ አለበት። እያንዳንዱ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተቃዋሚም ቢሆን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በአፉ ሊመሰክር ይችላል፣ ግን አሁንም የመጻህፍ ቅዱስ ቃል በትክክል ከሚለው ፍጹም የተለየ ነገር ማለቱ ሊሆን ይችላል። በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ከሌለ፣ የአእምሮ ምሁራዊ አስተሳሰብ ብቻ ሆኖ ይቀራል። የሐዋርያት ምስክርነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ሊገኝ ይችላል። ጳውሎስ በ1 ጢሞ. 3:16 ጠቅለል አድርጎ ያስቀምጣል። በእውነት፣ ያለዉ አንድ አምላክ ብቻ ነው፣ አንድ ፈጣሪ፣ በወልድ ውስጥ የተገለጠ አንድ አባት ብቻ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት፣ አንድ እውነተኛ ጥምቀት (ኤፌ. 4:4-6)።

<u>እያንዳንዱ ትምህርት፣ እያንዳንዱ የሚደረግ የእምነት ቃል፣ ከመጀመሪያው የሐዋርያት ክርስትና ጋር የማይጣጣም ማንኛውም ነገር ሐሰት ነው። የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን እስከ መጨረሻው ድረስም የሚጸና ምሳሌ ናት። አሁን ሁሉም ሰው እና ሁሉም ነገር የቃሉን ፈተና መቋቋም አለበት። መለኪያ ሊሆን የሚችለዉ የማይሳሳተው፣ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነዉ።</u>

በማቴ. 7:15 ጌታችን እንዲህ አለ፦ <u>"ከሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ፤</u> ወደ እናንተ የበግ ለምድ ለብሰው ይመጣሉ፥ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ናቸው።" አዎን፣ "ተጠንቀቁ!" ለማለት ቀላል ነው፣ ነገር ግን የበግ ቆዳ የተኩላውን አዳኝ ባህሪ ይሸፍናል። እዚህ ላይ ቁልፍ ቃል "ነጣቂዎች" ነው። መንጋውን በቃሉ አረንጓዴ መስክ አይመግቡም፣ ይልቁንም "የብልጽግና ወንጌልን" በመስበክ በጎቹን ይበዘብዛሉ፣ በዚህም ራሳቸውን ያበለጽጋሉ። በቁጥር 21 እስከ 22 ላይ ስለእነርሱ ትንሽ ተጨማሪ እንማራለን፦ "ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ

አይደለም፥ <u>በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ።</u> በዚያ ቀን ብዙዎች፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ <u>በስምህ ትንቢት</u> አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ <u>ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?</u> ይሉኛል።" ይህ መግለጫ በእውነት የትኛዉን መነቃቃት(ሪቫይቫል) እንቅስቃሴ ይመለከታል? ይህ በእኛ ዘመን ተአምራት የሚያደርጉትን  እንደሚመለከት መጠየቅ የለብንም? ከታላላቅ ወንጌላውያንና ከካሪዝማቲክ ሰዎች መካከል አይገኙምን? በመጀመሪያ እነዚያ "የእምነት ግዙፎች" ለጌታ በስሙ ያደረጉትን ይነግሩታል። "በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፣ አጋንንትን አላወጣንምን ወዘተ?" ይህ አሳማኝ ዘገባ አይደለምን? ነገር ግን ጌታ በፍፁም አይደነቅም እና እንዲህ ይላል፦ "ያኔም እኔ ፈጽሞ አላውቃችሁም፤ እናንተ ኃጢአት የምትሰሩ ከእኔ ራቁ እላቸዋለሁ።" (ቁ. 23)።

<u>"ይህን ሁሉ አላደረግንምን?"</u> የሚለው አባባል በጣም ትኩረት የሚስብ ነው። ለጌታ ክብርን አልሰጡም፣ ነገር ግን ለራሳቸው እና ኩራት ተሰምቷቸው ነበር፣ ምክንያቱም የራሳቸው ስም ክብርን አገኝቷል። እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መዳን፣ ፈውስ እና ሁሉም በረከቶች ከእግዚአብሔር እንደሚመጡ ያውቃሉ እናም  "የሚመካ በጌታ ይመካ።" (1 ቆሮ. 1:31፤ 2 ቆሮ. 10:17-18) የሚለዉን ቅዱስ ቃል ይከተላሉ። የእግዚአብሔር ልጅ ራሱ በትህትና "የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገርም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ያደርጋል።" (ዮሐ. 14:10ለ) አለ። ጴጥሮስና ዮሐንስ ሽባው ሰው ስለተፈወሰበት ክብር አልወሰዱም፣ ነገር ግን በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ኃይሉ ለተገለጠዉ ጌታ ሰጡት። እግዚአብሔር ሥራውን በክርስቶስ እንደሰራ ሁሉ፣ ክርስቶስም ሥራውን በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች በኩል ይሰራል። ቤተክርስቲያን ሕያው አካል ናት፣ የሞተ ሃይማኖታዊ ድርጅት አይደለችም።

እውነተኛ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች የእግዚአብሔር ልጅ አእምሮ አላቸው እና በሙሉ ልባቸው እንዲህ ብለው ያምናሉ፦ "...የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጅ።" (ሉቃስ 22:42)። ጌታችን እንዲህ አለ፦ "ከሰማይ የወረድኩት የራሴን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ነው።" (ዮሐ. 6:38፤ 4:34)። "...ፈቃድህንም ላደርግ፥ አቤቱ አምላክ ሆይ።" (ዕብ. 10:7)። <u>"የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜና እኅቴ እና እናቴ ነው።"</u> (ማር. 3:35)። <u>በዚህ ፈቃድ የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች ሁሉ ለአንዴና ለዘላለም ተቀድሰዋል</u> (ዕብ. 10:10)።

የእግዚአብሔር ፈቃድ በእግዚአብሔር ልጅ ሙሉ ታዛዥነት፣ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ተፈጽሟል። ከዚህ በተቃራኒ የሉሲፈር የራስ-ፈቃድ ቆሟል። <u>መጀመሪያ በሰማይ በተቀባው የነበረዉ የራስ ፈቃድ በምድር ላይ ባሉት ሐሰተኛ በተቀቡት ሁሉ የራስ-ፈቃድ ሆኖ ቀጥሏል፣ እና አሁንም ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ እና ዓመፅ ነው</u>። ቅዱሳት መጻሕፍት አጽንዖት ይሰጣሉ፦ "ዐመፅ እንደ ምዋርት ኃጢአት ነውና፥ እምቢተኝነትም እንደ ኃጢአትና እንደ ጣዖት አምልኮ ነው።" (1 ሳሙ. 15:23)። አሁን በምልክቶችና ድንቆች ላይ አጽንኦት የሚሰጡ እና የራሳቸውን የወንጌል ቅጅ የሚሰብኩ ሁሉ ያኔ ይደነቃሉ። እነርሱም "ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን!..."

የሚለዉን የጌታ ጸሎት ከሚደግሙ ክርስቲያኖች ሁሉ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ይቆማሉ ፤ ነገር ግን ከዚያ በኋላ እንደተለመደዉ የራሳቸዉን ስራ ይሰራሉ ፤በአንድ ቤተ እምነት ፤ቤተ ክርስቲያን ሕብረት ፈቃድ ዉስጥ ፤ እንዲያዉም በራሳቸዉ ፈቃድ ዉስጥ ይኖራሉ ።

በማቴ. 7 መሠረት በጌታችን የሚገሰጹት ሰዎች ሙሉ በሙሉ የራሳቸዉን ሥራ በመሥራት የተጠመዱ ናቸዉ ፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ቦታቸውን አይይዙም፣ እነርሱም የዓመጻ ሰራተኞች ተብለዉ ተመድበዋል፡፡ብዙ ጊዜ ሰዎች በስብሰባዎች ላይ በጋለ ስሜት "ጌታ ነው፣ ጌታ ነው..." ብለው ይዘምራሉ፣ ነገር ግን በእውነቱ የጌታ/አገልጋይ ግንኙነት የላቸዉም። ሰዎች በንግግር፣ በዝማሬ፣ በትንቢት እና በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ይተላለፋሉ። ሐሰተኛ ቅቡዓን እና ሐሰተኛ ነቢያት ለዚህ ጊዜ ስለ ተሰጠዉ ዋናው ተስፋ ግድ የላቸውም፤ አይጨነቁም፣ እንዲሁም ታላቁ የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሄር ነቢይን እንደላከ መስማት አይፈልጉም (ሚል. 4:5-6) ።

## የማታለሉ ደረጃ ጫፍ የደረሰበት

የማታለል መንፈስ የዓመፅን መስፈሪያ ሊይሞላና ሊይፈስ ደርሷል። በጌታችን ወይም በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ ፈጽሞ ያልተከሰቱ ነገሮች እየተዘገቡ ነው። ስብሰባዎች በአጠቃላይ በጣም እንግዳ ባህሪን እየያዙ ነው። የአካባቢዉ አየር በዘመናዊ ሙዚቃ ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ እየተፈጠረ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ አይደለም፣ የእግዚአብሔር ቀጥተኛ ሥራ አይደለም፣ ይልቁንም ሆን ተብሎ በአንድ በተወሰነ "ካሪዝማቲክ ሰው" ወይም "ተአምር ሰሪ" እና በእርሱ ልዩ ባህሪያት ላይ ያተኮረ ስብሰባ ነው። አስገራሚ ነገሮች እየተዘገቡ ነው፣ እንዲያውም ሰዎች ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ በጥርሳቸው ውስጥ የ24 ካራት ወርቅ ሙሌት እንደተቀበሉ ጭምር። በቅርብ ጊዜያት፣ በሰማይ ከሚገኙት የወርቅ ጎዳናዎች የተገኘው አቧራ በሰማይ በሚጋልበዉ ነጭ ፈረስ ተነስቶ ከሰባኪው ጥቁር ሸሚዝ ላይ እንደወደቀ እየተነገረ ነዉ። ፈረሰኛው በግራ እጁ በትር፣ በቀኝ እጁም ሰይፍ ይዞ እንደነበር ተዘግቧል! እነዚህን የመሰሉ መጻህፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ነገሮች እየተሰበኩ ሲሆን ይህ ደግሞ "ሦስተኛው የመነቃቃት ማዕበል" እንደሆነ ይታሰባል።

በካሪዝማቲክ ስብሰባዎች ውስጥ ከሚታዩት ሁሉም እንግዳ ነገሮች መካከል፣ በጸሎት ጊዜ ወደ ኋላ መውደቅ በጣም ልዩ ነው። ይህ "በመንፈስ መውደቅ" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን እንደ ልዩ መንፈሳዊ ተሞክሮ ቀርቧል። <u>መጻህፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደሚል እንስማ።</u> እነርሱ ኢሳይያስ 28:13 ይጠቅሳሉ፣ ነገር ግን ያ በእርግጥ እንደ ማስፈራሪያ ነው ፣ "...ሄደዉ ወደ ኋላ ይወድቁ ዘንድ ፤ ይሰበሩም ዘንድ ፤ይጠመዱም ዘንድ ፤ ይያዙም ዘንድ።" ሊሰሙ ስላልፈለጉና ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ስላልገቡ (ቁ. 12)፣ ወደ ኋላ እንደሚወድቁ ማስፈራሪያ ተሰጣቸው። መጀመሪያ ጌታ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በእውነቱ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ያሳያል እና ይከሳቸዋል፣ "ካህኑና ነቢዩ በጠንካራ መጠጥ ተሳስተዋል፤ በወይን ጠጅ ተዉጠዋል፤በጠንካራ መጠጥ መንገድ ስተዋል ፤ ራእይ በማየት ይሳሳታሉ፤ በፍርድም ይሰናከላሉ።" (ኢሳ. 28:7)።

ይህ መግለጫ የባቢሎንን ጽዋ ለሚጠጡና በዚህም ምክኒያት መንፈሳዊ አቅጣጫቸውን ላጡ ሁሉ በትክክል ይሠራል (ኤር. 51:7፤ ራዕ. 17:2)። ጌታ እንዲህ ይላልና፦ "ጠረጴዛዎች ሁሉ በትዉከት በርኩሰት ተሞልተዋልና፥ ንጹሕ ስፍራም የለም።" (ኢሳ. 28:8)። አንድ ጠረጴዛ ብቻ አይደለም፣ አንድ ቤተክርስቲያን ብቻ አይደለም፣ አንድ ቤተ እምነት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ሁሉም ጠረጴዛዎች በአገልጋዮች አፍ በሚቀርበው በተጭበረበረው ቃል ተበክለዋል።

ይህን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የሚከተለው ጥያቄ ተገቢ ነው፦ " እውቀትን ለማን ያስተምረዋል? ወይስ ትምህርት ማስተዋልን ለማን ይሰጣል?..." (ቁ. 9)። ጠረጴዛዎቹ በቆሻሻ በተበከሉበት ቦታ፣ እውነተኛ እውቀትን ወይም ትክክለኛ ትምህርቶችን ማስተላለፍ አይቻልም፣ እውነተኛ መገለጥን መቀበልም የባሰ አስቸጋሪ ነው። እነርሱም እንዲህ ማለታቸውን ይቀጥላሉ፦ "ትእዛዝ በትእዛዝ ላይ ፤ ትእዛዝ በትእዛዝ ላይ ፤ መስመር በመስመር ላይ ፤ መስመር በመስመር ላይ ፤ ትንሽ እዚህ ፤ ትንሽ እዚያ..." (ቁ. 10)።እነዚሁ ሰዎች እንዲህ ይላሉ "...ሞልቶ የሚፈሰዉ መቅሰፈት ሲያልፍ ወደ እኛ አይመጣና..." ይላሉ። ሁሉም በራሳቸው በጣም እርግጠኞች ናቸው፣ "...ውሸትን መጠጊያችን አድርገናልና፤ በሐሰትም ተሸሽግናል።" (ቁ. 15)። በራሳቸው መንገድ እንደሚሄዱና የራሳቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች እንደሚያስተላልፉ አይገነዘቡም። የራሳቸውን ምናባዊ ሕንፃ፣ በሃይማኖታዊ ውሸቶች ያጌጠውን፣ መጠጊያቸው እንዳደረጉ አላውቁም። ነገር ግን ጌታ እንዲህ ይላልና፦ "ለገመድ ፍርድን ለቱንቢም ጽድቅን አደርጋለሁ ፤ በረዶም የውሸትን መጠጊያ ይጠርጋል ፤ውኃም መሸሸጊያውን ያሰጥማል።" (ቁ. 17)።

የውሸት መጠጊያው በእውነት ቃል መዶሻ ከተመታ፣ ሰዎች ትኩረት ሰጥተው ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለባቸው። ለጉዞአችን በእግዚአብሔር የተሰጠን አንድ ትክክለኛ መመሪያ ብቻ አለ። ጳውሎስ ለባልደረባው ጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "አንተ ግን ትምህርቴን፥ አካሄዴን፥ አሳቤን፥ እምነቴን፥ ትዕግሥቴን፥ ፍቅሬን፥ ጽናቴን ፈጽመህ አውቀሃልና..." (2 ጢሞ. 3:10)። ዛሬ የሐዋርያትን ትምህርትና ሕይወት ምሳሌ አድርጎ ለመውሰድ ማን ዝግጁ ነው? ማንም ሊሳሳት አይገባም ፡- እግዚአብሔር ለዘላለም እንዲዘበትበት አይፈቅድም። በመንግሥቱና በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ቃሉ ብቻ ነው ትክክለኛ። የሰው ቃል በሰው ተቋማት ዉስጥ ነው፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ምትክ አይድለም። ያ ድርብ ኃጢአት ነው፦ ቃሉን መተው እና የአንድን ሰዉ ሕሊና በሰው ቃል በመተካት ማረጋጋት (ኤር. 2:13)። በዓለም ዙሪያ ባሉ ቤተ እምነቶች ውስጥ ያለዉ ሁኔታ ይህ ነው፣ ማንም ሳያስተዉለዉ።

ነጻ መውጣትና ነፃነትን የሚያውጁ ሰዎች ሰዎችን በመረባቸው ይይዛሉ እና አዲሱ ድርጅታቸው ከአሮጌው እስር ቤቶች ጋር ይመሳሰላል። በእውነቱ፣ ነገሮች በነበሩበት ይቀራሉ፣ ምክንያቱም ጌታ እንዲህ ይላልና፦ "ይህ ግን የተበዘበዘና የተዘረፈ ሕዝብ ነው፤ ሁላቸዉ በዋሻ ዉስጥ ተጠምደዋል፥ በእስር ቤቶችም ውስጥ ተሰውረዋል፤ ለብዝበዛ ተሰጥተዋል፥ የሚያድናቸውም የለም፤ ምርኮም ሆነዋል፥ "መልሱ" የሚልም የለም። ከእናንተ መካከል ይህን የሚያዳምጥ፤ ወደፊትም ለሚመጣው

ዘመን የሚያዳምጥና የሚሰማስ ማን ነው?" (ኢሳ. 42:22-23)። ነገር ግን በየትኛውም ቦታ የተመረጡ ሰዎች አሉ፣ ይህን በልባቸው የሚይዙ እና ጌታ ከሁሉም መንፈሳዊ እስር ቤቶች የሚጠራቸው፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት፦ "ሕዝቤ ሆይ፥ ከመካከላቸው ውጡ፥ ተለዩም ይላል ጌታ፥ ርኩስ ነገርንም አትንኩ..." (2 ቆሮ. 6:16-18፤ ራዕ. 18:4 ወዘተ)።

በእግዚአብሔር ፊት ማንም ሰው በጸሎት ጊዜ ወደ ኋላ ወድቆ አያውቅም፣ ይልቁንም በጉልበቱና በፊቱ ነበር፦ አብርሃም (ዘፍ. 17:17)፣ ኤሊዓዘር (ዘፍ. 24:48)፣ ሙሴ (ዘጸ. 34:8)፣ ኢያሱ (ምዕ. 5:14)፣ ዳንኤል (ምዕ. 8:17) እና ጌታችንም በጌትሴማኒ (ማቴ. 26:39)። ነቢያትና የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ በፊታቸው ወደቁ፣ "የእስራኤልም ልጆች ሁሉ እሳቱ ሲወርድ፥ የእግዚአብሔርም ክብር በቤቱ ላይ ሲሆን ባዩ ጊዜ፥ <u>በድንጋይ ላይ በፊታቸው ወደ ምድር ዝቅ አሉ፥ ሰገዱም፥ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት</u>..." (2 ዜና. 7:3)። አረማዊው ንጉሥ ናቡከደነፆርም ቢሆን እግዚአብሔር ያደረገውን ካየ በኋላ እንዲሁ አደረገ (ዳን. 2:46)። <u>መንፈስ ቅዱስ በትንቢት ስጦታ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሁሉ፣ ሰዎች በፊታቸው ይወድቃሉ</u> (1 ቆሮ. 14:25)፣ እና በተዘጋጁት "የእሳት ስብሰባዎች" ላይ እንደሚደረገው ወደ ኋላ አይወድቁም። በአዲስ ኪዳንም ቢሆን፣ በጌታ ፊት በአክብሮት ሁሉም በፊታቸው ወደቁ። ከሦስቱ ጥበበኞች ጀመሮ፣ አዲስ የተወለደውን ክርስቶስን ለማምለክ ከመጡት (ማቴ. 2:11-12)፣ እስከ ሐዋርያው ዮሐንስ በፓጥሞስ ደሴት።

በሁሉም የመነቃቃት ስብሰባዎችና የወንጌል ዘመቻዎች ሰዎች ስብከቱን ለመስማት ይሰበሰባሉ፣ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ናፍቆት ስላላቸው ነው። ነገር ግን ጌታችን በማቴ. 22:14 የተናገረውም ይሠራል፦ "ብዙዎች ተጠርተዋልና፥ ጥቂቶች ግን ተመርጠዋል።" የተመረጡት ብቻ ድምፁን ይሰማሉ፣ ይወጣሉ፣ ይዘጋጃሉ እና ያለ ማቋረጥ በጌታ መንገዶች ይሄዳሉ። ሌሎቹ ወደ ልምዶቻቸው ይጠቁማሉ እና በራሳቸው መንገድ ይቀጥላሉ።

አሁን እየሆኑ ያሉ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን የሚታዩበትና በግልጽ የሚመረመሩበት ጊዜ ደርሷል። ጌታ በተለይ ተአምራት አድራጊዎችን "ከእኔ ራቁ!" በሚለው መግለጫ ሲያናግር፣ ይህ ጉዳይ በቁም ነገር ሊታይ ይገባል። ብዙዎች ስሙን አላግባብ ይጠቀማሉ፣ ትንቢት ይናገራሉ፣ አጋንንትን ያስወጣሉ እና ተአምራትን ያደርጋሉ። በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት ይከበራሉ። ከእነርሱና ከሚያደርጉት ነገር ጋር ምን ስህተት አለ? ሁሉም ነገር በጣም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይመስላል! እነርሱ ራሳቸው በትምህርታቸውና በትንቢታቸው የተሳሳቱ ናቸው፣ ምክንያቱም እውነተኛውን የሐዋርያት ትምህርቶችና እውነተኛውን የትንቢት ቃል ችላ ይላሉ።

የእግዚአብሔር ኃይል በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውጤታማ በሆነ መንገድ ይሠራል፣ ሰባኪው ትክክል ቢሆንም ወይም የተሳሳተ ቢሆንም፣ ምክንያቱም ከሚያምኑት እምነት ጋር ብቻ የተገናኘ ነው፣ ከሰባኪው ሕይወት ወይም ትምህርቶች ጋር አይደለም። ጌታችን እንዲህ አለ፦ "የሚያምኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል..." (ማር. 16:17-18)። ደግሞም ተጽፏል፦ "...እርሱ ፀሐዩን

በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ያወጣልና፥ ዝናብንም በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ያዘንባል።" (ማቴ. 5:45)።

እውነት አሁንም አለ እና የጌታችን ተስፋ አለን፦ "ስለዚህ ደግሞ የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ አለች ፦ ነቢያትንና ሐዋርያትን እሰድድላቸዋለሁ..." (ሉቃስ 11:49) አለች። ጌታ ራሱ ለሚልካቸው ሰዎች እንዲህ ይላል "እነሆ፥ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ..." (ማቴ. 10:16) ። ነገር ግን፣ "የሚቀበላችሁ እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይቀበላል..." (ማቴ. 10:40-41)።

ይህ እግዚአብሔር የሰጠው ታላቅ ተስፋ ነው፣እርሱ በቀጥታ የላካቸውን መልእክተኞቹን ለሚቀበሉ ሰዎች ዋጋ ለመስጠት! ጌታም ደግሞ አጽንዖት ሰጥቶ እንዲህ አለ፦ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የምልከው የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።" (ዮሐ. 13:20)። "ኢየሱስም ደግሞ፦ ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔም እልካችኋለሁ።" (ዮሐ. 20:21)። እግዚአብሔር የሚልከው እያንዳንዱ ሰው የተጠራበትን ቀን፣ ቦታ እና የተቀበለውን መለኮታዊ ትእዛዝ ትክክለኛ ቃላት ያውቃል።

## ዋናዎቹ መመዘኛዎች

የትክክለኛ እና የስህተት ትምህርት ልዩነቱ ምንድን ነው?በትክክል ምን እየተደረገ እንዳለ እና ትክክል እንዳልሆነ እንዴት እንገነዘባለን ? በዚህ ጉዳይ ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ? የራሳችንን አስተያየት ለራሳችን ብንይዘው ይሻላል፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ምንም ዋጋ የለውምና።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች የእምነት መግለጫዎች ከመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ያፈነግጣሉ። ስለ አምላክነት፣ ስለ ጥምቀት ወዘተ ያላቸው ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ከሐዋርያት ጋር አይስማሙም። ይህን እውነታ ሳያውቁ፣ አብዛኛው ሰዎች በብዙ በረከቶች ቢኖሩም፣ በተለምዷዊ የተሳሳተ ክርስትና ውስጥ ይኖራሉ። ይህ ደግሞ በጸጋው ዘመን መጨረሻ ላይ ያለው አሳዛኝ ታሪክ ነው። በእግዚአብሔር የተላኩ ነቢያት፣ ሐዋርያትና አስተማሪዎች፣ ለምሳሌ፣ አንድ እውነተኛ አምላክን ብቻ ነው የሚያውቁት፣ ሦስት አካል ያለው አምላክን አይደለም። "ኢየሱስ ብቻ" የሚለውን አስተምህሮም አያውቁም ነበር። እግዚአብሔር ራሱን በተለያዩ መንገዶች እንደገለጠ ያውቁ ነበር። የሦስት እኩል አካላት ያሉት ሥላሴ አስተምህሮ፣ ከዘላለም የነበሩ ናቸው የሚባለው፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነና በጣም ጥንታዊ የሆነ አረማዊ ጽንሰ-ሐሳብ ነው፣ ይህም ዛሬም በቡድሂዝም ውስጥ ይገኛል።

የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን እድገት ከእስራኤል ጋር ተመሳሳይነት አለው። "ሕዝቡም ሙሴ ከኮረብታው ሲወርድ እንደዘገየ ባዩ ጊዜ፣ ሕዝቡ በአሮን ላይ ተሰበሰቡና፦ ሂድና በፊት ለፊታችን የሚሄዱልን አማልክት ሥራ ..." (ዘፀ. 32: 1) አሉት። እሱም ተስማምቶ የወርቅ ጥጃ ሠራ፣

ምክንያቱም በግብፅ በሬውን ያመልኩ ነበር። ከዚያም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፦ "…እነዚህም ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው፣ እስራኤል ሆይ!" (ቁ. 4)። ትዕይንቱን መገመት ያስፈልጋል፡ የእስራኤል አምላክ በተራራው ላይ ወርዶ ለሙሴ ሲናገር፦ "እግዚአብሔርም ይህን ቃል ሁሉ ተናገረ እንዲህም አለ፦– እኔ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑብህ። የተቀረጸ ምስል አታድርግ …" (ዘፀ. 20: 1-4) – በተመሳሳይ ጊዜ አሮን ከሕዝቡ ጋር ለጥሩ ዓላማ በሚመስል ጣዖት አምልኮን እየፈጸመ ጥጃውን "አምላክ" ብሎ ጠራው።

የጌታችን የመመለስ የተስፋ ቃሉ ለመፈጸም የዘገየ ሲመስል ፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም እንዲሁ አደረጉ፡ በአረማዊው አብነት ሦስት ራስ ያለው፣ ሦስት ቅርጽ ያለው አምላክ ፈጥረው እንዲህ አሉ፦ "ይህ አምላካችሁ ነው፣ ክርስትና ሆይ።" ይህን ምስል የሚነካ ሁሉ እጅግ ቅዱስ ቅዱሳንን እንደሰደበ ይቆጠራል። ታዲያ የትኛው እምነት ነው ትክክለኛው? ሐዋርያው ጳውሎስ ትክክለኛውን ትምህርት በታላቅ አጽንዖት ሲናገር፣ "…አንድ አምላክ ነውና …" (ሮሜ 3: 30) እንዲሁም ሲል፣ "መካከለኛውም አንድ አይደለም፣ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።" (ገላ. 3: 20) ብሎ ገልጿል። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ "ሦስት አካል ያለው አምላክ" ወይም "ሥላሴ" የሚለው ቃል አንድም ጊዜ አይገኝም፣ እንዲሁም "ሰማያዊ" ወይም "ዘላለማዊ ልጅ" የሚልም ፈጽሞ የለም። በዚህ መንገድ "የተሠራው" አምላክ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን አይታወቅም። ለነቢያትና ለሐዋርያት ፈጽሞ ባዕድ ነው። ንጹህ አእምሮ ያለው ሰው በሰማይ የሚገዙ ሦስት እንዳሉ እና እነዚህ ሦስት አካላት ተስማምተው ሥላሴን እንደሚመሰረቱ በማመን ፈጽሞ የእግዚአብሔርን ቃል ሊጋፈጥ አይችልም። በሰማይ ሥላሴ በእውነት ቢኖር ኖሮ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ይመዘገብ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ቦታ ስለማይገኝ፣ በሰማይ ሊኖር አይችልም።

አንዳንዶች ደግሞ ነገሩን አጋነው፣ "አሁን ቅዱስ ሥላሴን እንጋብዛለን!" ብለው ይጮኻሉ። ከዚያም አስታዋቂው አብን ይጋብዛል፣ ሁሉም በደስታ ያጨበጭባሉ። ከዚያም ወልድን ይጋብዛል፣ ሁሉም በጋለ ስሜት ይወሰዳሉ። በመጨረሻም፣ መንፈስ ቅዱስም በመካከላቸው እንዲመጣ ይጋበዛል፡ መላው ጉባኤ ያጨበጭባል። አንድ ሰው በእውነት ሦስት ዘላለማዊ፣ ሦስት ሁሉን ቻይ እና ሦስት በሁሉም ቦታ የሚገኙ እንዳሉ ያምናል? ያ እንግዲያውስ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረዉ አንድ እና ብቸኛ አምላክ አይደለም። ሦስት የተለያዩ አካላት ሦስት አማልክት ናቸው እንጂ አንድ አምላክ አይደሉም፣ ቃላት ትርጉም እንዲሰጡ። በዚህ ውስጥ በሐዋርያው ጳውሎስ የተተነበየውን ታላቅ ክህደት እናያለን። ይህ የሆነው ክርስትና የአይሁድን የመገለጥ መሠረት ሲተው ነው።

በብሉይ ኪዳን ክህደት ሁልጊዜ ከአንድ እውነተኛ አምላክ ዞር ብሎ ወደ ሌሎች አማልክት መመለስን ያመለክታል። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ከአንድ እውነተኛ አምላክ ወደ ሥላሴ-አምላክነት መመለስ የ"ታላቁ ክህደት" መጀመሪያ ነበር። ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንዲህ ሲል ጻፈ፦ "በክርስቶስ ጸጋ ከጠራችሁት ወደ ሌላ ወንጌል እንዲህ በፍጥነት ስለተመለሳችሁ እደነቃለሁ…" (ገላ.

1: 6)። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ሌላ ወንጌልን ለሚሰብኩ ሰዎች እርግማንን ተናገረ። በኋላም እንዲህ ሲል ጠየቀ፡- "…አዚም ማን አደረገባችሁ…" (3: 1)።

ለጥምቀት የሥላሴ ቀመርን የሚጠቀሙ ሁሉ በዚሁ ክስ መከሰስ አለባቸው። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ፣ ሁሉም አማኞች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቀዋል፣ ጴጥሮስ በብዓለ ሃምሳ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በመጀመሪያ ስብከቱ ላይ እንደገለጸው (ሐዋ. 2: 38)። ብዙዎች ከቤተ ክርስቲያን ወግ ጋር ይስማማሉ እንጂ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አይደለም።

የኢየሱስን ስም በታላቅ ኃይል የሚጠቀሙት እነዚህ ሰዎች፣ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ እና ሌሎች ሐዋርያት፣ ከጌታ ራሱ ትእዛዝን የሰሙ፣ ያዘዙትና ያደረጉትን፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመጠመቅ በግልጽ እምቢ ይላሉ። ነገር ግን ይህ ብቻ አያረካቸውም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተመዘገበው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተደረገውን እውነተኛ ጥምቀት እንደ መናፍቅነት ይቆጥራሉ። ይህንንም በንግግራቸውና በጽሑፎቻቸው ይገልጹታል። በእነዚህ ነገሮች ላይ ማሰላሰል ተገቢ ነው። ዛሬ መናፍቅነትን የሚሰብኩ ሰዎች፣ በዚህም የሰማይ መንግሥት ቁልፎች የነበሩት ጴጥሮስ፣ እና በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሥልጣን የነበረው ጳውሎስ፣ በተሳሳተ መንገድ አስተምረዋል እና አጥምቀዋል፣ ስለዚህም በመጀመሪያው ክርስትና የመጀመሪያዎቹን አማኞች አታልለዋል ብለው ያመለክታሉ። እነርሱ ራሳቸው ጌታ የሰጠውን ትእዛዝ አይፈጽሙም፣ ሐዋርያት እንዳደረጉት፣ ማቴ.28: 19ን እንደ አስማት ቀመር ይደግሙታል። በእነዚህ "ሦስት ታላላቅ ማዕረጎች" በአሮጌው "ክርስቲያናዊ" አህጉር ላይ ምን እንደሚደረግ በአጠቃላይ አይታወቅምን? አስማት፣ ጥንቆላ፣ መናፍስታዊነት፣ ጠረጴዛ ማዞር፣ የእጅ መዳፍ ንባብ፣ የወደፊት ትንበያ፣ ሁሉንም ዓይነት ድብቅ ጥበብ እና መናፍስታዊ ድርጊቶች በእዚያ ቀመር ይፈጸማሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ወሳኝ ጥናት እንደሚያረጋግጠው፣ በማቴዎስ 28: 19 ላይ ያለው ጽሑፍ በመጀመሪያዎቹ የእጅ ጽሑፎች ውስጥ "en to onomati mou" – "በስሜ" የሚል ነበር፣ ይህም የቤተ ክርስቲያን አባት የሆኑት ዩሴቢየስም ያረጋገጡት ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ገለጻ፣ በመጀመሪያዎቹ መቶ ክፍለ ዘመናት ጥምቀት የተፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነበር። ለውጡ የተከሰተው ሰዎች የራሳቸውን ስላሴያዊ ሀሳቦች ካመጡ በኋላ ብቻ ነው። በአንዳንድ ትርጉሞች ላይ፣ በየአህጉሩ በሚነበበው የኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው፣ የማይታመን ተጨማሪ ቁጥር አሁንም በ1ኛ ዮሐንስ 5: 7 ላይ ይገኛል፡- "በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት አሉና፣ አብ፣ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስም …"። የመጀመሪያ ሴሚስተር የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ሁሉ እንደሚያዉቀዉ ይህ ቁጥር በመጀመሪያዎቹ የእጅ ጽሑፎች ውስጥ ፈጽሞ የለም። በዕብራይስጥ ጽሑፍም አይገኝም፣ በግሪክኛ የቃላት ፍቺም ሆነ በጀርመን የሉተር ትርጉም ወይም በሌላ በየትኛውም የጀርመን መጽሐፍ ቅዱስ እትም አይገኝም፣ ከዝዊንግሊ ጊዜ ጀምሮ ባለው የዙሪክ እትምም አይገኝም፣ በጄ. ኤን. ዳርቢ የፈረንሳይኛ እትምም አይገኝም፣ በላምሳም ሆነ በሌሎች

ብዙዎቹም አይገኝም። በጀርመን ስኮፊልድ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም፣ የእንግሊዝኛው ስኮፊልድ ደግሞ እንዲህ የሚል የግርጌ ማስታወሻ አለው፡- **"ይህ ቁጥር ምንም የእጅ ጽሑፍ ምንጭ እንደሌለው እና እንደተጨመረ በአጠቃላይ ይታመናል።"** ነገር ግን በተወረሰ ባህል ምክንያት፣ የተሻለ እውቀት እያለ፣ በዚያው ቀርቷል፣ ፓስተሮችም ስለእሱ ይሰብካሉ። አፖክሪፋም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ አዳኙ ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ቃልም በሰው እጅ ወደቀ – እንዴት ያለ አሳዛኝ ክስተት ነው! ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ ከጌታ ጸሎት ላይ ምስጋና ተጨምሯል፣ በቅርቡ ደግሞ "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" የሚለው ቀመር ከእሱ በኋላ እየተነበበ ነው። በተለያዩ ቋንቋዎች ባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ውስጥ ያሉት ልዩነቶችም በአንዳንድ ክፍሎች ከባድ ናቸው፣ ለምሳሌ በጌታ ጸሎት ላይ። የመጀመሪያው የአራማይክ ስሪት እንዲህ ይላል፡- "...**እኛን ወደ ፈተና እንዳትመራን**..."። እግዚአብሔር እኛን ወደ ፈተና አይመራንም (ያዕ. 1: 13) እኛ ብዙውን ጊዜ እንደምንጸልየው አይደለም።

የመጀመሪያዉ እውነት እንዲታወቅ እነዚህ ነገሮች አንድ ጊዜ መነገር አለባቸው። ሁሉም አሰቃቂ የመስቀል ጦርነቶች፣ ሁሉም የጠንቋይ መከራዎች፣ እንጨት ላይ ማቃጠል፣ መላው ምርመራ፣ ሁሉም ስደቶች፣ የአይሁድ እና የሌሎች አማኞች ግድያ የተፈጸሙት በቀሳውስት ባርኮት፡- "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም"። እንዲሁም በፈረንሳይ የሠላሳ ሺህ ሁጉኖቶችን ለማረድ፣ ለወንጀለኞች የሥላሴ "ባርኮት" ከመንበሮች ተሰጥቷል። እስከ ዛሬ ድረስ፣ ወደ አንድ የተወሰነ ሥርዓት የሚገቡ ሁሉ ስእለታቸውን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መናገር አለባቸው – እ ወደ ነፃ ሜሶን ማኅበር አባልነት የሚገቡ አይሁዶችም ቢሆኑ።

ከሂትለር ዋፈን-ኤስኤስ የውስጥ ክበብ አባላት የሆኑ ሁሉ (ጥቁር ዩኒፎርም የለበሱ እና በቀኝ ክንዳቸው ላይ ንቅሳት ያላቸው፣ በቀበቷቸውም ላይ "Blut und Ehre" = "ደም እና ክብር" የሚል ጽሑፍ ያለበት፣ እና በራሳቸው ላይ የራስ ቅል ምልክት የነበራቸው) "ለራይክ እና ፉህረር" በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መሐላ መግባት ነበረባቸው። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሂደት ውስጥ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በዚህ ቀመር ሥር ታርደዋል፣ አንዳንዶቹም በአሰቃቂ ሁኔታ ተሰቃይተዋል። ከአውሽዊትዝ የተረፉ አይሁዶች፣ የቀድሞውን የሞት ካምፕ በጎበኙሁበት ጊዜ በግላቸው እንደ ነገሩኝ፣ እንዲሁም "የሆሎኮስት መታሰቢያ ቀን" ላይ በቴሌቪዥን ቃለ ምልልስ በይፋ እንደ መሰከሩት፣ ጥቁር ዩኒፎርም የለበሱት እነዚህ ገዳዮች በካምፑ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የካቶሊክን ቅዳሴ በየጊዜው ይካፈሉ ነበር። በጋዝ ክፍሎች ውስጥ የሞቱት ሰዎች ጭስ ወደ ሰማይ ሲወጣ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ዕጣንም ወደ ጣሪያው ይወጣ ነበር፣ ጸሎቶችም በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይነበቡ ነበር።

ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ታሪክን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው የሥላሴ አስተሳሰብ እና የሥላሴ ቀመር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁት በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. መሆኑን ያውቃል። ፖሊካርፕ እና ኢሬኔዎስ ስለ ክርስቶስ ምንም ዓይነት ክርክር አያውቁም ነበር። ክርስቶስን ሐዋርያት

እንደሰበኩት ያዉቁት ነበር። እነዚህ የዶክትሪን ክርክሮች ጉዳይ የሆኑት በኒቂያ ጉባኤ (325) ብቻ ሲሆን ከዚያም በ381 ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ ቀጥለው ተዘጋጁ። እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙት በ441 ዓ.ም. በጳጳስ ሊዮ 1ኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው!

በሥላሴ እናት ቤተ ክርስቲያን በሰማዕትነት የሞቱት 50 ሚሊዮን ወይም 60 ሚሊዮን ቢሆኑም፣ የታሪክ ጸሐፊዎች ሊስማሙበት አይችሉም። ነገር ግን በተለየ መንገድ ለሚያምኑት እና በተለይም "የክርስቶስ ገዳዮች እና በእግዚአብሔር የተጣሉ" ተብለው የተወገዙት አይሁዶች፣ የሥላሴን አምላክ እምነት እንዲቀበሉ እና በሥላሴ ጥምቀት እንዲጠመቁ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸዉ መሆኑ የታወቀ ነው። በተለይም ለማንኛውም ኦርቶዶክስ አይሁዳዊ ይህ አማራጭ አልነበረም፣ ምክንያቱም የነፍሱ ዋጋ ማለት ነውና፣ በዚህም በእግዚአብሔር ራሱ የተሰጠውን የመጀመሪያውን እና እጅግ ቅዱስ ትእዛዝ ይጥስ ነበርና፡- "እስራኤል ሆይ ስማ፡ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ጌታ ነው!" (ዘዳ. 6: 4)። የእነዚህ ሰማዕታት ነፍሳት በቀልን ይጮሃሉ፣ እንደ ራእይ 6: 9-10። "አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለያዙት ምስክርነት የታረዱትን ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ። <u>በታላቅ ድምፅም፡- ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፣ በምድር ላይ በሚኖሩት ላይ ደማችንን እስከ መቼ አትፈርድም አትበቀልም? አሉ"</u> አሁን እግዚአብሔር ተጠያቂ የሚያደርገዉ ይህ ተቋም ማን እንደሆነ መጠየቅ አለብን። በሚከተሉት የቅዱሳት መጻሕፍት ማጣቀሻዎች ሊታሰብ የሚችለው ማን ነው?

> "የቅዱሳንንና የነቢያትን ደም አፍስሰዋልና…" (ራእይ 16: 6)።
>
> "ሴቲቱንም በቅዱሳን ደም በኢየሱስም ምስክሮች ደም ሰክራ አየሁ…" (ራእይ 17: 6)።
>
> "ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትገዛ ታላቂቱ ከተማ ናት።" (ራእይ 17: 18)።
>
> "በእርስዋም የነቢያትና የቅዱሳን ደም በምድርም ላይ የታረዱ ሁሉ ደም ተገኘ።"(ራእይ 18: 24)።

የእውነት ሰዓት ደርሷል። ሁሉም ነገር – ሁሉም ትምህርቶች፣ ሁሉም ልምዶዶች፣ መላው እምነት፣ ሁሉም በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ሊመረመሩ ይገባል። ከዚህ በኋላ፣ በዚህ ውስብስብ ርዕስ ላይ እውቀት አለዎት። ማንኛውም ሰው ተጠያቂ ሳይሆን የመጨረሻውን ፍርድ ሊያመልጥ ይችላል? እኛ በመንፈሳዊ እና በአስተመህሮ በክርስቶስ ደም የተገዛች ቤተ ክርስቲያን፣ የብኩር ልጆች ቤተ ክርስቲያን (ዕብ. 12: 22-23) አባል ነን ወይስ ወይም የደም እድፍ ያለባት ቤተ ክርስቲያን፣ በሴት ልጆቿ  እናት ተብላ የምትጠቀሰው እና "ምስጢር ባቢሎን ታላቂቱ" (ራእይ 17: 1-6) የምትባለው ቤተ ክርስቲያን አባል እንደሆንን እራሳችንን መጠየቅ የለብንም? ሁሉም ሰው አሁን የት እንዳለ ማወቅ ይችላል።

ከተሐድሶ መንፈሳዊ ግኝት ጀምሮ፣ ጌታ ሕዝቡን ደረጃ በደረጃ መጻህፍ ቅዱሳዊ ካልሆነው ነገር ሁሉ ወደ ኋላ እንዲወጡ እየጠራ ነው፣ ቤተ ክርስቲያኑ በሐዋርያትና በነቢያት ወደ ተመሰረተዉ

ሙሉ በሙሉ እስክትመለስ ድረስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስም ዋነኛው የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ። (ኤፌ. 2: 20)።

ሰባኪዎች፣ ወንድሞች፣ የዋናዉ የክርስትና ጉዞ ወዴት እንደሚያመራ አትረዱምን? አንዳንዶቻችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ሴሚናሮችን አቋቁማችኋል፣ ሌሎችን ታስተምራላችሁ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትምህርቶች ራሳችሁ ትቀበላላችሁ? አንድ እውነተኛ አምላክ ለእኛ መዳን በአዲስ ኪዳን <u>በሰማይ አባታችን</u>፣ በምድርም <u>በወልድ</u>፣ በቤተ ክርስቲያኑ <u>በመንፈስ ቅዱስ</u> እራሱን እንደገለጠ አትገነዘቡም? ይህ የሆነው በአንድ፣ ልዩ በሆነው በአዲስ ኪዳን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የቃል ኪዳን ስም ነው፣ በእርሱም ብቻ ሁሉም መለኮታዊ መዳን አለ፣ አማኞችም የሚጠመቁበት።

በብሉይ ኪዳን፣ ማንም "በሰማይ የምትኖር አባታችን" ብሎ አይጸልይም ነበር፣ ነገር ግን ለጌታ ለእግዚአብሔር ነበር። ይህ የቃላት አገባብ እዚያ 6,700 ጊዜ ይገኛል። አንድም ነቢይ ስለ "በሰማይ ያለ ዘላለማዊ ልጅ" ምንም አያውቅም ወይም አልጠራም። ያ አዲሱ ለመረዳት የማይቻል፤ሊገለጽ የማይቻል ሚስጥር፤በብሉ ኪዳን የተተነበየው እና ተስፍ የተገባለት ፡ የእግዚአብሔር በክርስቶስ መገለጥ ነው (2ኛ ቆሮ. 4: 6፤ ቆላ. 2: 2-3፤ 1ኛ ጢሞ. 3: 16 እና ሌሎች)።

ይህ መገለጥ የሌለው ማንኛውም ሰው ቃሉን በተሳሳተ መንገድ <u>ይረዳል</u>፣ <u>ይሳሳታል</u> እንዲሁም <u>በስህተት ያስቀምጣል።</u> በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ <u>ስም(ነጠላ)</u> እንድናጠምቅ የታዘዝንበት፣ በእርግጥም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የዕብራይስጥ ቃል ያሹዋ "ያህዌ-አዳኝ" ማለት ነው፣ እንደ እማኑኤል "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ማለት ነው። የብሉይ ኪዳን ጌታ/ያህዌ በአዲስ ኪዳን ጌታ ኢየሱስ ነው። ያ መለኮታዊ እውነት ነው። የአብ ስም የወልድም ስም ነው (መዝ. 22: 23)፣ በእርሱም ራሱን ገልጿል። ሁሉም ሰባኪዎች፣ ወንጌላውያን፣ የካሪዝማቲክ ስብዕናዎች እና ሁሉም በዚህ ያሉ አማኞች በሐዋርያት ዘመን እና በቀጣይ በነበሩ 200 ዓመታት ውስጥ ምንም ዓይነት መጻሕፍ ቅዱሳዊ ተግባር ወይም ጸሎት በሥላሴ ቀመር ተከናውኖ እንደማያውቅ እንዲቀበሉ ግድ ይባላሉ።

የመጀመሪያው ሰዓት ሰው የሆነው ጴጥሮስ፣ የተነሳው ጌታ ደቀ መዛሙርቱን እንዲያደርጉ ያዘዛቸዉን በትክክል ታዘዘ፦ "...እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው..." (ማቴ. 28: 20)። ከትንሣኤ በኋላ ለአርባ ቀናት ያህል፣ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ተናገረ፣ <u>እርሱም በግል አስተማራቸው</u> (ሐዋ. 1: 1-3)። በዚያን ጊዜ ነበር ታላቁን ተልእኮ የሰጠው፣ ይህም በትክክል ተፈጽሟል።<u>የክርስቶስ ትምህርት የእግዚአብሔር ትምህርት ነበር እና አሁንም ነው</u>። "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ትምህርቴ የእኔ አይደለም፣ ነገር ግን የላከኝ የእርሱ ነው። የእርሱን ፈቃድ ሊያደርግ የሚወድ ማንም ቢኖር፣ ትምህርቱ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ወይም እኔ ከራሴ እንደምነገር ያውቃል።" (ዮሐ. 7: 16-17)። <u>የሐዋርያትም ትምህርት የክርስቶስ ትምህርት ነበር</u>። "ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር እግዚአብሔር የለውም። በክርስቶስ ትምህርት የሚኖር እርሱ አብም ወልድም አሉት። ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ

ይህንም ትምህርት የማያመጣ ቢኖር በቤታችሁ አትቀበሉት፣ ሰላምታም አትስጡት፤ ሰላምታ የሚሰጠው የክፉ ሥራው ተካፋይ ነውና።" (2ኛ ዮሐ. 9-11)።

## ፈተናው

"ለሚናገረው እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ፤ እነዚያ በምድር ላስረዳቸዉ እምቢ ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፤ ከሰማይ ከመጣዉ ፊቀቅ የምንል እኛስ እንዴት እናመልጣለን…" (ዕብ. 12: 25)። አሁን ጥያቄው ይነሳል፦ መንፈሳዊ መሪዎች ዛሬም ቢሆን፣ ልክ ክርስቶስ በመጀመሪያ ሲመጣ እንደሆነው፣ እግዚአብሔር ምንም እንዳልሰራ አድርገዉ፣ በባህላዊ መንገዳቸው ይቀጥላሉ? ኦ እናንተ የመጀመሪው የመነቃቃት ማዕበል ወንጌላውያን፣ እግዚአብሔር በእኛ ዘመን ያደረጋቸውን ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ቀጥተኛ እዉቀት ነበራችሁ። በእግዚአብሔር የተሾመ ትንቢታዊና የማስተማር አገልግሎት ባይኖር ኖሮ፤ ወንጌላዊ አገልግሎታችሁ ፈጽሞ አይኖርም ነበር። በአንድ በኩል እንዲህ ትላላችሁ "ዊልያም ብራንሃም ታላቅ ነቢይ ነበር! እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ገለጠለት!" ሬቨረንድ ቲ..ኤል ኦስቦርን እንደመሰከረዉ ፤በሌላ በኩል ደግሞ "ትምህርቱ ስህተት ነበር!" ትላላችሁ። ይህ እንዴት ሊገጥም ይችላል? "እግዚአብሔር ከማንም በላይ ታይቶ የማይታወቅ፣ ሊወዳደር የማይችል አገልግሎትን በመለኮታዊ ማረጋገጫ ሰጠው" ትላላችሁ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት የሚቀድመውን እና ትክክለኛውን መንገድ የሚያሳየንን በጌታ ስም ያመጣውን መልእክት ትተላለፋላችሁ። በዚህም ፈጽሞ ሊጠፋ የማይችል ታላቅ በደል በራሳችሁ ላይ እየጫናችሁ ነው። የሰዓቱ ሰዎች እንደሆናችሁ ራሳችሁን ታቀርባላችሁ። ግን በተመሳሳይ ጊዜ፣ በእኛ ዘመን ልዩ የሆነውን እና ያልተለመደውን የእግዚአብሔርን ተጽዕኖ ለመግደል ሁሉንም ነገር እንዳደረጋችሁ፣ የእግዚአብሔርን አገልጋይና ነቢይ ስብዕና በማጥፋት ወንጀል ተጠያቂ አይደላችሁም? የተመረጡትን እስከ መጨረሻው ድረስ ማስቀረት አትችሉም፣ ምክንያቱም እነሱ – እውነተኛዎቹ በጎች – የመልካሙን እረኛ ጥሪ ያዳምጣሉ። የእግዚአብሔር ቃል ለዘላለም ሂወት ለተሾሙትን ሁሉ በእኛ ዘመን የተላከለትን ያከናውናል!

የዚያን ጊዜ ጸሐፍት እንዳደረጉት፣ የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ በራሳችሁ የመካድ ተግባር እየሠራችሁ አይደለምን (ሉቃስ 7: 29-30)፣ ጳውሎስ ራሱ እንዲህ እንደተጠመቀ ቢመሰክርም (ሮሜ 6: 3)፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ ለመጠመቅ ፈቃደኛ አልሆናችሁም? የእውቀትን ቁልፍ አልወሰዳችሁም እና ሌሎችንም እንዳይገቡ ወደ ኋላ አልጎተታችሁም(ሉቃስ 11: 52)? ጳውሎስ ያስተማረው እና በብራንሃም እንደገና እንደ አዲስ የቀረበው መለኮታዊዉን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ በላቀ ፈገግታ ችላ ብላችሁ በራሳችሁ መንገድ ትቀጥላላችሁ።

"እነዚህ የብራንሃም ትምህርቶች ናቸው፦ ስለ አምላክነት(Godhead)፣ ስለ ውድቀት፣ ስለ ጥምቀት፣ በመጻህፍ ቅዱስ ሴት ቦታ ወዘተ" ብላችሁ ታረጋግጣላችሁ። በእርግጥ? የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች አይደሉምን? ጌታ ራሱ ዛሬ ማን ላይ ነው በሰባት እጥፍ "ወዮ!" ብሎ የሚወነጅለው፣

ያን ጊዜ መንፈሳዊ መሪዎችን እንዳደረገው (ማቴ. 23: 13-33)? እግዚአብሔር ሕዝቡን ራሳቸውን ከሚመግቡ እረኞች ሁሉ ይጠይቃል፤ ከሁሉም ሰው እምነትንና ታዛዥነትን ይፈልጋል።

በማቴዎስ 24 ላይ ጌታችን የሚናገረው ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ስላሉት ሁኔታዎች ብቻ አይደለም፣ ከጠቅላላው መመለስ ጋር የተገናኘውን እና አሁን ፍጻሜውን እያገኘ ያለውን ክፍልም ይጠቅሳል፦"**እንኪያስ ምግባቸዉን በጊዜዉ ይሰጣቸዉ ዘንድ** ጌታዉ በቤተ ሰዎች ላይ የሾመዉ ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነዉ? እንግዲህ ጌታው በመጣ ጊዜ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ታማኝና ልባም ባሪያ ብፁዕ ነው። እውነት እላችኋለሁ፥ በንብረቱ ሁሉ ላይ ይሾመዋል።" (ቁ. 45-47)። አሁን ሙሉው አዋጅ፣ ሙሉው ቃል፣ ሁሉም መንፈሳዊ ንብረቶች መቅረብ አለባቸው። በኃይል፤ትእዛዛዊ በሆነ፤ዘልቆ በሚገባ የጌታ ድምጽ እ.ኤ.አ ሚያዝያ 2፣ 1962 ቃሉን እንድሰብክ በቀጥታ በተሰጠኝ ትእዛዝ መሰረት እንደ ጳዉሎስ በእግዚአብሄር ፊት ታላቅ ኃላፊነት ተሸክሜአለሁ። የመጨረሻዉን መልእክት በእዉነት በአለም ላይ በሙሉ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ማወጅ አለብኝ ። እግዚአብሔር ባሪያዉን እና ነቢዩን ከእርሱ ጋር እንዲሆን ወስዶታል፤ነገር ግን ለእርሱ የተገለጠዉ ቃል ከእኛ ጋር እንደ መንፈሳዊ ምግብ አለ፤እግዚአብሔር በሚልከዉ ታላቁ የቃሉ እርሃብ ለህዝቡ እንደ ትኩስ መና የሚሆን (አሞስ 8:11)። ቃሉ ለዘላለም ይኖራል፤ እና ማንም ከእግዚአብሔር የተወለደ ቃሉን ይሰማል። ነብዩ ሐጌ የጻፈዉ ዛሬም ይሰራል "…የሕዝቡም ቅሬታ የአምላካቸውን የጌታቸውን ድምፅ እና የነቢዩን የሐጌን ቃል ሰሙ፣ <u>አምላካቸውም ጌታ እንደ ላከው፣ ሕዝቡም በጌታ ፊት ፈሩ</u> "(ሐጌ 1:12)።

እኛ አሁንም እየኖርን ያለነዉ በፀጋዉ ዘመን ነዉ እና እያንዳንዱ መንገዱን ቀይሮ ከእግዚአብሔር ጋር ለመቆም እድል አለዉ። አሁን፣ ለመጨረሻ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ መዳንና ትምህርት፣ እና ቅዱሳት መጻሕፍት ወደሚያሳዩት መንገድ ለመመለስ ወደ እኛ እየቀረበ ነው። ያው ቃል የማይታዘዙትን ሁሉ ይፈርድባቸዋል (ዮሐ. 12: 48)። ለሁሉም ሰው የሚከተለው ምክር ይሠራል፦ "ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን አታደንድኑ።" (ዕብ. 4: 7)። እያንዳንዱን ግለሰብ እንዲህ ሲል ያነጋግራቸዋል፦ " ለሰላምሽ የሚሆነዉን በዚህ ቀን አንቺስ እንኳ ብታዉቂ ፤አሁን ግን ከአይንሽ ተሰዉሯል!" (ሉቃስ 19: 42)።

ጠላት፣ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ በሰማይም ሆነ በምድር ታላቅ ጉዳት አድርሷል። ውሸቱን በየቦታው አሰራጭቷል፣ የእግዚአብሔርን እውነቶች አጣመሞ ሰዎች እንዲያምኑ አድርጓል። ነገር ግን ቃሉ በመጀመሪያ ስለነበር፣ ያው ቃል እስከ መጨረሻው እውነት ሆኖ ይኖራል። አሁን በጸጋው ዘመን መጨረሻ ላይ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች በእውነት እየተቀደሱ ነው (ዮሐ. 17: 17)። በዓለም ዙሪያ እግዚአብሔር ሊፈውሰን፣ ከስህተት ሁሉና ከሁከት ሁሉ ሊያወጣን ቃሉን እንደላከ ይገነዘባሉ። በዚህ የመጨረሻ መነቃቃት፣ የሙሽራዋ ቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑት እውነተኛ አማኞች ሁሉ ከስህተትና ከመምታታት ሁሉ ይወጣሉ። የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ በጸጋ የጠላትን ሁሉንም ተንኮለኛ ተግባራት የመጨረሻውን እና ኃይለኛውን ድል በቅርቡ ትቀዳጃለች።

ለእነርሱ የሚከተሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ይሠራሉ፦ “እነርሱም በበጉ ደም፣ በምስክራቸው ቃልም ድል ነሱት፤ ሕይወታቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።” (ራእይ 12: 11)።

“የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራሳዋን ስለዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሴትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ። ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድተጎናጸፈ ተሰጥቶአታል ። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነዉና ። እርሱም ፦ ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብጹዓን ናቸዉ ብለህ ጻፍ አለኝ ። ደግሞም ፦ ይህ የእግዚአብሔር እዉነተኛ ቃል ነዉ አለኝ።” (ራእይ 19: 7-9)።

ይህ ሙሉ ማብራሪያ ለእያንዳንደ በቃሉ አማካኝነት የተናገረዉ የእግዚአብሔር በጎ መመሪያ ተደርጎ ተቀባይነት እንደሚያገኝ አምናለሁ ። የእግዚአብሔር ጸጋ እና ሰላሙ እና በረከቱ በጣም ዉድ በሆነዉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከሁላችሁም ጋር ይሁን።

“እርሱም፦ የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል አትዝጋው አለኝ፤ ጊዜው ቀርቧልና… እነሆም፣ ቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው እመልስለት ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር ነው። እነዚህን ነገሮች የመሰከረው፦ በእርግጥ ቶሎ እመጣለሁ አለ። አሜን። ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን።” (ራእይ 22: 10, 12; 20-21) ።

ይኸው ደራሲ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለሚናገሩባቸው በጣም ጠቃሚ ርዕስ ጉዳዮችን ተመለክቷል። እነዚህ ብሩሹሮች በዓለም ዙሪያ በብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች ታትመው ለብዙ ሰዎች ዘላቂ በረከት ሆነዋል።

እኛም በዚህ የሚሲዮን ማዕከል 21 የዊልያም ብራንሃምን የተስተካከሉ ስብከቶች አሳትመናል፤ እነዚህም እንዲላኩላቸው ለሚፈልጉ ሁሉ በጠየቁት ጊዜ ሊላኩ ይችላሉ። ያሉትን የሕትመቶች ዝርዝር ማቅረብ ይቻላል።

ውዱ ጌታችንና መድኃኒታችን ለራሱ ወገኖች ምን ዓይነት መንፈሳዊ ምግብ እንዳዘጋጀ ስታውቁ ትገረማላችሁ።

ፍላጎት ካላችሁ፣ ከዚህ በታች በተዘረዘረው አድራሻ መጻፍ ትችላላችሁ፡-


የሚሲዮን ማዕከል

ፖ.ሳ. ቁጥር 100707

47707 ክሬፌልድ፣ጀርመን

ኢሜል፡ volksmission@gmx.de ወይም

E.Frank@freie-volksmission.de

ድህረ-ገፅ፡ http://www.freie-volksmission.de